ኢፕድ
# አዲስ ዘመን
እሁድ 83 ዓመት ቁጥር 272 ሰኔ 2 ቀን 2016 ዓ.ም ዋጋ 10:00
ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!

eccs
የኢትዮጵያ የግንባታ ግብዓቶች አቅራቢ ኃ/የተ/የግል ኩባንያ
ETHIOPIAN CONSTRUCTION COMMODITIES SUPPLY PLC.
የአርማታ ብረት እና ሌሎች ብረታብረቶች አከፋፋይ
Mob. 0911 225057/ 0989 343434
አድራሻ፡ ከሜክሲኮ አደባባይ ወደ መርካቶ በሚወስደው መንገድ ከዲ-አፍሪክ ሆቴል ፊት ለፊት

# ኪነ-ጥበብን በመጠቀም በልኩ ያልታወቀውን የኢትዮጵያን ታሪክና ባህል በአግባቡ ማስተዋወቅ ይገባል

ጌትነት ተስፋማርያም

<u>አዲስ አበባ</u>፡- ኪነ-ጥበብን በመጠቀም በልኩ ያልታወቀውን የኢትዮጵያን ታሪክና ባህል በአግባቡ ማስተዋወቅ ይገባል ሲሉ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) ተናገሩ።

በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ያሬድ የሙዚቃ ትምህርት ቤት በዕውቁ የሙዚቃ ባለሙያ ፕሮፌሰር አሸናፊ ከበደ ስም ያስገነባውን የሙዚቃዊ ጥበባት ማዕከል ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) ትናንት መርቀው ከፍተዋል።

በወቅቱ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ ባደረጉት ንግግር፤

ኪነ-ጥበብን በመጠቀም...ወደ ገጽ 4 ዞሯል



ፀደይ ባንክ (አ.ማ)
TSEDEY BANK (S.C)
የሁሉም ባንክ
Bank for all !
የብዙዎችን ተስፋ ያለመለመ!
በፋይናንስ አቅርቦት በተግባር የተፈተነ እንዲሁም ሰፊና ጽኑ መሰረት ያለው ባንክ በአነስተኛ የፋይናንስ አገልግሎት ዘርፍ በአገለገለባቸው 25 ዓመታት አለም አቀፍ ዕውቅናዎችን ሲያገኝ የቆየው አማራ ብድርና ቁጠባ ተቋም ወደ ፀደይ ባንክ ተሸጋግሮ የተሟላ አገልግሎት በመስጠት ላይ ይገኛል።
Tel: +251 115 58 12 70/011 551 73 48/011 558 99 98
P.O.Box: 9630
E-mail: mekonnenyelewemwessen@tsedeybank-sc.com
Web: www.tsedeybank.org.et
Addis Ababa, Ethiopia

Medhin Decor
የተንጣለለ ድንቅ የሰርግ አዳራሽ ከነ ሙሉ የውበት ስራ
የተሟላ የምግብ ዝግጅት ከሙሉ መስተንግዶ ጋር
Medhin Decor
ለሠርግ ለልደት እንዲሁም ለልዩ ልዩ ዝግጅቶች
አድራሻ 1ኛ በሌ ጌቱ ኮሜርሻል ጀርባ
2ኛ ከቃሊቲ ማሰልጠኛ አለፍ
ብሎ ቆርኪና ጣሳ ፋብሪካ ገባ ብሎ
Contact Us 0911222993/ 0911208918

## የአክሱም አውሮፕላን ማረፊያ ጥገናው ተጠናቆ ዛሬ መደበኛ ሥራውን ይጀምራል

ሔርሞን ፍቃዱ

<u>አዲስ አበባ</u>፡- ለአራት ዓመታት አገልግሎቱ ተቋርጦ የቆየው የአክሱም አውሮፕላን ማረፊያ (ኤርፖርት) ጥገናው ተጠናቆ ሰኔ 2 ቀን 2016 ዓ.ም መደበኛ ሥራውን እንደሚጀምር የአክሱም ከተማ ከንቲባ አቶ አበበ ብርሃነ አስታወቁ፡፡

የከተማዋ ከንቲባ አቶ አበበ ብርሃነ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንዳሉት፤ የአፄ ዮሐንስ አራተኛ የአክሱም አውሮፕላን ማረፊያ በሰሜኑ ጦርነቱ ምክንያት ጉዳት ደርሶበታል ፡፡ ይህን ጉዳት ጠግኖ ወደ ሥራ ለማስገባት በፌዴራል መንግሥት እና በአጋር አካላት ዕቅድ ተይዞ ወደ ትግበራ ተገብቷል፡፡

የአክሱም ኤርፖርት ለከተማዋ ገቢ፣ ቱሪዝምና ንግድ እንቅስቃሴ የጀርባ አጥንት መሆኑን ገልጸው፤ ኤርፖርቱ ለአራት ዓመታት ሥራውን በማቆሙ ምክንያት ለከተማዋ ከባድ ማህበራዊ ቀውስ ፈጥሮ

የአክሱም አውሮፕላን...ወደ ገጽ 4 ዞሯል



## በክልሉ ከአምስት ሺህ 800 ቶን በላይ የሻይ ምርት ወደ ማዕከላዊ ገበያ ተልኳል

- በቀጣዩ መኸር ወቅት የሚተከል ከአንድ ሚሊዮን በላይ የሻይ ችግኝ ተዘጋጀ

ገጽ 4

## በሜዲካል ኮሌጁ ለ400 ታካሚዎች የሥነ ልሳን ህክምና ተሰጠ

ዮርዳኖስ ፍቅሩ

<u>አዲስ አበባ</u>፡- ለ400 ታካዎች የሥነ ልሳን ህክምና መስጠቱን የካቲት 12 ሆስፒታል ሜዲካል ኮሌጅ አስታወቀ፡፡

በሆስፒታሉ የሥነ ልሳን ህክምና ባለሙያ ዶ/ር አካሉ አሰፋ፣ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንዳስታወቁት ሆስፒታሉ ባለፉት 11 ወራት ለ400 ህጻናትና አዋቂ ታካሚዎች የሥነ ልሳን ህክምና (Speech Therapy) ሰጥቷል፡፡

ህክምና ያገኙ ታካሚዎች ቁጥር ካለው የባለሙያ ቁጥር አንጻር ትንሽ የሚባል ባይሆንም፣ ህክምናውን ማግኘት ካለባቸው ታካሚዎች አንጻር ግን አነስተኛ መሆኑን ነው የተናገሩት፡፡

ህክምናው አጭር በሆነ የጊዜ ገደብ ውስጥ የሚሰጥ አለመሆኑ ከሌሎች የህክምና ሂደቶች የተለየ እንደሚያደርገው ያነሱት ዶ/ር አካሉ፤ የሥነ ልሳን ህክምና

በሜዲካል ኮሌጁ...ወደ ገጽ 4 ዞሯል

ኤኤምጂ ብረታ ብረት ፋብሪካ
AMG Steel Factory
Tel:- 0940 505050 – 0940 606060 – 0940 909090 – 0940 808080 -0920 656565

ዜና



# የእንሰት አጠውልግ በሽታን ለመከላከል የተቀናጀ ርብርብ ይፈልጋል

## -135 የእንሰት ዝርያዎችን በመለየት የማባዛት ሥራ እየተሠራ ነው

**ሞገስ ጸጋዬ**

አዲስ አበባ፡- የእንሰት አጠውልግ በሽታን ለመከላከል የተቀናጀ ርብርብ እንደሚያስፈልግ ተገለጸ። 135 የእንሰት ዝርያዎችን በመለየት የማባዛት ሥራ እየተሠራ መሆኑን በኢትዮጵያ ግብርና ምርምር ኢንስቲትዩት የወልቂጤ ግብርና ምርምር ማዕከል አስታወቀ።

በኢትዮጵያ ግብርና ምርምር ኢንስቲትዩት የወልቂጤ ግብርና ምርምር ማዕከል ተመራማሪና ዳይሬክተር አቶ ቤተል ነክር እንደገለፁት፣ በጉራጌ ዞን የእንሰት ተክል የምግብ ዋስትናን ከማረጋገጥ ባሻገር የገቢ ምንጭም ነው። ይሁን እንጂ የእንሰት አጠውልግ በሽታ በአርሶ አደሮች ላይ ችግር ደቅኗል፡፡በዚህ ምክንያት አርሶ አደሩም የእንሰት ተመጋቢነትን እየቀነሰ በመሆኑ ችግሩን ለመፍታት አፋጣኝ ርብርብ ያስፈልጋል።

ለእንሰት በሽታ መፍትሄ ለማምጣት በተቀናጀ መልኩ ሁሉም የድርሻውን ሊወጣ ይገባል ያሉት ዳይሬክተሩ፣ ለችግሩ መፍትሄ ሊያመጣ በሚችልና ኑሮውን በእንሰት ላይ ያደረገ ማህበረሰብን ሊደግፍ በሚችል መልኩ ሥራዎች መሠራት እንዳለባቸው አሳስበዋል።

እንሰትን በተመለከተ በተለያዩ ዩኒቨርሲቲዎችና የምርምር ማእከላት የተጀመሩ ሥራዎች አሉ ያሉት አቶ ቤተል፣ ይሁን እንጂ የአርሶ አደሮችን ችግር በሚቀርፍ ደረጃ መፍትሄ ያመጣ አካል የለም። በምርምር የተገኙ ቴክኖሎጂዎችን ለተጠቃሚ ማስተላለፍ ላይ ችግሮች ይታያሉ ብለዋል።

እንደ ዳይሬክተሩ ገለጻ ፤ የእንሰት ተክል እንደ ሀገር ትኩረት ቢያገኝና በተቀናጀ መልኩ ቢሠራ ውጤት ማምጣት ይቻላል። በእንሰት አጠውልግ በሽታ ምክንያት ከተለያዩ ዩኒቨርሲቲዎች፣ የምርምር ማእከሎችና ተቋማት ጋር ውይይት ተደርጓል፣ የውይይት ውጤቶችን ለፖሊሲ አውጪዎች በማቅረብ ለችግሮች መፍትሄ ለማምጣት መሥራት ይጠበቅባቸዋል።

ቀደም ሲል ቡናና ዝንጅብ ላይ መሰል ችግር አጋጥሞ ነበር ያሉት ዳይሬክተሩ፣ ነገር ግን ትልቅ ትኩረት ተሰጥቶት በምርምር በመታገዝ መፍትሄ ተገኝቶለታል። የእንሰት ተክል የሚያጋጥመውን ችግሩር ለማስወገድ እንደ ሀገር ትኩረት ተሰጥቶት ከተሰራ ከሀገር ፍጆታ አልፎ ከፍተኛ የውጭ ምንዛሬ ማስገኘት እንደሚቻል ገልጸዋል።

የእንሰት ተክል ትኩረት እንዲያገኝ በማድረግ ለተጋረጠበት አደጋ መፍትሄ መስጠት ያስፈልጋል ያሉት አቶ ቤተል፣ የእንሰት አጠውልግ በሽታን ለመካከል ፍቱን የሚባል መድሃኒት እንደሌለ ጠቁመው፤ በሽታው ወደ ሌላው አካባቢ እንዳይዛመት ጉዳት የደረሰበትን እንሰት በማስወገድ በሽታውን የመቆጣጠር ሥራ እየተሠራ ነው፣ይህም ውጤትም ማምጣቱን አመልክተዋል፡፡

የወልቂጤ የግብር ምርምር ማእከል በሽታው እንዳይስፋፋ ለአርሶ አደሮች የግንዛቤ ማስጨበጥ ሥራ በስፋት እየሠራ መሆኑን አብራርተዋል።

እንደ ዳይሬክተሩ ገለጻ፣ እንሰት በተፈጥሮው ከፍተኛ ፍግ ይፈልጋል፣ ነገር ግን የእንስሳት ቁጥር እየቀነሰ በመምጣቱ የእንሰት ተክል ምርታማነት ላይ ተጽእኖ እያሳደረ ነው። ይሁን እንጂ በምርምር ማእከሉ ሌሎች አማራጮች እየተፈለጉ ነው።

በአየር ንብረት ለውጥ ምክንያት የእንሰት ተክልን ፍቆ ለምግብነት ለማዋል እስከ ስምንት ዓመት እየቆየ መሆኑን ገልጸው፤ የምርምር ማእከሉ በሽታውን ከመቆጣጠር ባሻገር ምርታማነትን መጨመርና በፍጥነት የሚደርሱ እንሰቶችን የመለየት ሥራ እየሰራ መሆኑን ገልጸዋል።

እንደ አቶ ቤተል ማብራሪያ፣ ለቆጮ፣ ለህሚቾ፣ ለቡላ የሚሆኑ 135 የእንሰት ተክሎችን ከአርሶ አደሮች ተለይተዋል። የተለዩ ዝርያዎችን ጠብቆ ማቆየትና ወደፊት ቴክኖሎጂን በመጠቀም የማባዛት ሥራ ይሠራል። በተለይ ለመድሃኒትነት የሚውሉ የእንሰት ተክሎች ተፈላጊ በመሆናቸው እንዳይጠፉ ጠብቆ የማቆየት ሥራ እየተሠራ እንደሚገኝ ገልጸዋል፡፡

# የኢትዮጵያውያን መገለጫ የሆነው ሩጫ ለሰላም ግንባታ መጠቀም ይገባል

## - ሀገር አቀፍ የሰላም ሩጫ በመጪው ሰኔ 23 ይካሄዳል

**ልጅዓለም ፍቅሬ**

አዲስ አበባ፡- የኢትዮጵያውያን መገለጫ የሆነው ሩጫ ለሰላም ግንባታና ለሀገራዊ መግባባት መጠቀም ያስፈልጋል ሲሉ የሰላም ሚኒስትር ዴኤታ ኬይረዲን ተዘራ (ዶ/ር) ገለጹ፡፡ የአምስት ሺህ ሜትር ሀገር አቀፍ የሰላም ሩጫ በመላው ሀገሪቱ ሰኔ 23 ቀን 2016 ዓ.ም እንደሚካሄድ የሰላም ሚኒስቴር አስታውቋል፡፡

“ሰላም ለሁሉም ሁሉም ለሰላም” በሚል መሪ ሃሳብ በቀጣይ ሚካሄደው ሀገር አቀፍ የሰላም ሩጫ በሰላም ለማጠናቀቅ ከሁሉም ክልሎችና ከሁለቱ ከተማ አስተዳደር ሰላምና ጸጥታ ቢሮዎች ጋር ትናንት ውይይት ተደርጓል፡፡

የሰላም ሚኒስትር ዴኤታ ኬይረዲን ተዘራ (ዶ/ር) በወቅቱ እንደገለጹት፤ የኢትዮጵያውያን መገለጫ የሆነው ሩጫ ለሰላም ግንባታ መጠቀም ያስፈልጋል፡፡

ስፖርት ከየትኛውም እንቅስቃሴ በላይ የዴሞክራሲ ባህል፣ የእውነተኛ ትግል፣ የመከባበርና የመፈቃቀር ማሳያ መድረክ ነው ያሉት ዶክተር ኬይረዲን፤ ተወዳዳሪና ተፎካካሪ አካላት አሸናፊ ለመሆን ተወዳድረው ለአሸናፊው እውቅና ከሰጡ በኋላ በመካከላቸው ያለው ልዩነት አጥበው መግባባት የሚችሉበትና እውነተኛ የዴሞክራሲ ሥርዓት የሚገነባበት ዘርፍ ነው ብለዋል፡፡

የሰላም ሚኒስቴር የዜጎችን ሰላም ለማስጠበቅና በሀገራዊ ጥቅም ላይ የውይይት ባህል እንዲዳብር እንዲሁም ቀጣናዊ ሰላምና መረጋጋት እንዲሰፍን ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር እየሠራ መሆኑን ኬይረዲን ዶ/ር ተናግረዋል፡፡

ኬይረዲን ዶ/ር ፤ ሩጫ ለኢትዮጵያውያን መገለጫ በመሆኑ ይህንንም እሴት ለሰላም ግንባታ መጠቀም እንደሚያስፈልግ አመልክተው፤ የአካል ብቃት እንቅስቃሴ የጋራ መግባባትን በመፍጠር ሰላምን ከማስፈን አኳያ አንድ እርምጃ ማራመድ የሚችል መሆኑን አስረድተዋል፡፡

እንደ ኬይረዲን ዶ/ር ገለጻ፣ የሕዝቦች ለሕዝቦች ቅርርብና ሀገራዊ መግባባት ለመፍጠር ስፖርት ቁልፍ መሣሪያ ነው፡፡ ታላቁ የሰላም ሩጫ ከስፖርታዊ ፋይዳው ጎን ለጎን የሀገርን ሁለንተናዊ ሰላምና መረጋጋት ለማረጋገጥ ከፍተኛ ሚና አለው፡፡

የሰላም ሩጫው የተፈለገውን ውጤት እንዲያስገኝ ሁሉም ባለድርሻ አካላት በተለይ የሰላምና ጸጥታ ቢሮዎች ተገቢውን ትኩረት በመስጠት የድርሻቸውን እንዲወጡ ጥሪ አድርገዋል፡፡

በውድድሩ ከአንደኛ እስከ ሶስተኛ የወጡ ተወዳዳሪዎች ከ15 ሺህ እስከ 50 ሺህ ብር የሚሸለሙ ሲሆን የሰላም ሚኒስቴር ከአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደርና ከታላቁ ሩጫ በኢትዮጵያ ጋር በጋራ በመሆን እደሚያዘጋጁት በመድረኩ ተገልጿል።

በውይይት መድረኩ የሰላም ሚኒስቴር አመራሮች፣ ከሁሉም ክልሎችና ከሁለቱ ከተማ አስተዳደሮች የተውጣጡ የሰላምና ጸጥታ ቢሮ ኃላፊዎች፤ የወጣቶችና ስፖርት ኃላፊዎች፣ የታላቁ ሩጫ በኢትዮጵያ አስተባባሪዎች እንዲሁም የኢትዮጵያ አትሌቲክስ ፌደሬሽን አመራሮች ተገኝተዋል።

# ከተሞችን ተወዳዳሪ ለማድረግ የምርምር ውጤቶችን ወደ ተግባር መቀየር ይጠይቃል

**አማን ረሺድ**



አዲስ አበባ፡- ከተሞችን ተወዳዳሪና ብቁ ለማድረግ የምርምር ውጤቶችን ወደ ተግባር መቀየር እንደሚያስፈልግ የአዲስ አበባ አመራር አካዳሚ አስታወቀ፡፡ አካዳሚው “ምርምር ለከተማ ትራንስፎርሜሽንና ዲጂታላይዜሽን” በሚል መሪ ሃሳብ 4ኛውን ሀገር አቀፍ የጥናትና ምርምር ጉባዔ በትናትናው ዕለት አካሂዷል፡፡

የአዲስ አበባ አመራር አካዳሚ ፕሬዚዳንት ጣሰው ገብሬ (ዶ/ር) በወቅቱ እንደገለጹት፤ ከተሞችን ተወዳዳሪና ብቁ ለማድረግ የምርምር ውጤቶች ሚና ከፍተኛ መሆኑን ተገንዝቦ ወደ ተግባር መቀየር ያስፈልጋል፡፡

አካዳሚው ከ42 ሺህ በላይ አመራሮችን ሥልጠና መስጠቱን ገልጸው፤ ይህም በተቋማት ውጤታማነት ላይ ትልቅ አስተዋጽኦ ማበርከቱን አመላክተዋል።

በከተማ አስተዳደር ውስጥ የሚገኙ አመራሮችና ባለሙያዎች የማስፈፀም አቅማቸውን ለመገንባት የሚረዱ የሥልጠና፣ የምርምር፣ የማማከርና የማህብረሰብ አገልግሎት ሥራ መሠራቱን ገልጸዋል፡፡

የአገልግሎት አሰጣጥ ላይ የሚስተዋሉ ችግሮችን በመፍታት የህብረተሰቡን እርካታ ለማረጋገጥ በጉባዔው የሚቀርቡ የጥናት ግኝቶችን በመመስረት የዲጂታል ትውልድ ግንባታ ላይ በትኩረት እንደሚሠራም ጠቁመዋል፡፡

ከ55 በላይ ሳይንሳዊ ምርምሮች በአካዳሚው ተሠርተዋል ያሉት ጣሰው (ዶ/ር)፤ የሚስተዋሉትን ችግሮች መቅረፍ እንዲቻል የምርምር ውጤቶች ተግባራዊነት ላይ ሁሉም ባለድርሻ አካላት ኃላፊነታቸውን ሊወጡ ይገባል ብለዋል።

የአካዳሚው የምርምር ልማት ዳይሬክተር አብነት ፋላሳ (ዶ/ር) በበኩላቸው፤ አካዳሚው በከተማ አስተዳደር ስር ለሚገኙ አመራርና ባለሙያዎችን በሥልጠና፣ በምርምርና ጥናት ላይ የተመሠረተ በርካታ ችግር ፈች ሥራዎችን ከባለድርሻ አካላት ጋር በቅንጅት እየሠራ መሆኑን ገልጸው፤ በቀጣይ ዘመናዊ ከተማን ለመገንባትና የዜጎችን ሕይወት በቴክኖሎጂ የተደገፈ ለማድረግ እንሚሠራ ጠቁመዋል፡፡

በመድረኩ ላይ ጥናት ያቀረቡት ግደይ ደስታ በበኩላቸው፤ በአዲስ አበባ ከተማ እየተተገበረ ያለው የዘመናዊ ከተማ ልማት እንቅስቃሴ ጥሩ ጅማሮ መሆኑን ጠቅሰው፤ ወደ ክልል ከተሞችም መስፋፋት ይኖርበታል ብለዋል።

የኢትዮጵያ ከተሞችን ከአፍሪካ ተወዳዳሪ ለማድረግ የቱሪዝም፣ የጤና ፣ የዲፕሎማሲ፣ የኮንፈረንስ ከተሞችን መገንባት እንደሚያስፈልግ ገልጸዋል።

የአማራ ክልል አመራር አካዳሚ ምክትል ፕሬዚዳንት ቹቹ አለባቸው (ዶ/ር) በበኩላቸው፤ አመራር አካዳሚያቸው የአዲስ አበባን ተሞክሮ ወደ ክልሉ በመውሰድ ተግባራዊ ለማድረግ እንደሚሠራ ጠቅሰው፤ በቀጣይ በክልሉ ከተሞች የተደረጉ የተለያዩ ጥናቶች ተግባራዊነታቸውን በመከታተል ውጤታማ እንዲሆኑ ለመሥራት መታቀዱን አስረድተዋል፡፡

በመድረኩም የከተማ አስተዳደሩ ከፍተኛ የሥራ ኃላፊዎችና ባለድርሻ አካላትን ጨምሮ የዘርፉ ምሁራን የተገኙ ሲሆን ከተሞች ላይ ያተኮሩ አምስት ጥናታዊ ጽሁፎች ቀርበው ዉይይት ተደርጎባቸዋል፡፡

# ርዕሰ አንቀፅ

## የትምህርት ሥርዓቱን ስብራት ለማከም!

ትምህርት ለአንድ ሀገር ሁለንተናዊ እድገት ዋነኛ አቅም ነው። ከዚህ የተነሳም ሀገራት ለትምህርት ዘርፍ ከፍተኛ ሀብት በመመደብ ዘመኑን በእውቀት የሚዋጅ ትውልድ ለመፍጠር ትኩረት ሰጥተው ይሠራሉ። እንደ ሥራቸው ስኬትም ዛሬ ላይ እንደ ሀገር ያሉበትን ከፍታ ለመቀናጀት ችለዋል ።

በዕድገት እና በሥልጣኔ አንቱ የተባሉ ሀገራት እና ሕዝቦች ፤ አሁን ለደረሱበት ደረጃ በዋንኛነት የሚጠቀሰው ለትምህርት /ለእውቀት ሽግግር የሰጡት ትኩረት ነው ። ነገዎቻቸውንም የተሻለ ለማድረግ የሚያደርጉት ሁለንተናዊ ጥረትም በትምህርት ላይ ካላቸው የጸና እምነት የሚነጭ ነው።

በእኛም ሀገር ከትምህርት ጋር በተያያዘ የነበረው አስተሳሰብ በየዘመኑ የተለያየ ገጽታ ቢኖረውም ፤ የዘመናዊ ትምህርት መስፋፋትን ተከትሎ የተፈጠረው እሳቤ ግን ፤ ለትምህርት ትልቅ ትኩረት የሰጠ ፤ ለሀገርም ሆነ ለተሻለ ማኅበረሰብ ግንባታ ትምህርት ወሳኝ አቅም እንደሆነ በተጨባጭ ያመላከተ ነው።

ለዚህም ሀገሪቱ ለዘመናዊ ትምህርት በሮቿን መክፈት ከጀመረችበት ጊዜ ጀምሮ መንግሥት እና መላው ሕዝብ የትምህርትን ሁለንተናዊ ጠቀሜታ በመገንዘብ በነበሩ አማራጮች በሙሉ የትምህርት መሠረተ ልማቶችን ለማሟላት ረጅም ርቀት ተጉዘዋል ። በየዘመኑ የነበረ ትውልድ የተሻለ ትምህርት የሚያገኝበትን ዕድል ለመፍጠር የአቅሙን ያህል ተንቀሳቅሰዋል ።

ሕዝባችን ገና ከጅምሩ ልጆቹን ማስተማሩ ለራሱም ሆኑ ለሀገሩ እንዲሁም ለመጪው ትውልድ ብሩህ ነገዎች እንደማስተማመኛ አድርጎ በመውሰድ ፤ ተቸግሮና ተንገላቶም ቢሆን ልጆቹን ለማስተማር ብዙ ዋጋ ከፍሏል። በትምህርት ወስጥ አርቆ ያየውን ተስፋ ለመጨበጥ ዛሬዎቹን መስዋዕት አድርጎ አቅርቧል ።

ይህም ሆኖ ግን ሀገራዊ የትምህርት ሥርዓቱ በየወቅቱ የነበረው የፖለቲካ ሥርዓት ጥላ ያጠላበት በመሆኑ ፤ ሀገሪቱ እና ሕዝቦቿ ለዘርፉ ለመክፈል የተገደዱትን ዋጋ ያህል ተጠቃሚ መሆን ሳይችሉ ቀርተዋል። ከዚህ ይልቅ በየዘመኑ የነበረው የትምህርት ሥርዓት በፈጠረው ግራ መጋባት ሀገሪቱ ያልተገባ ዋጋ ለመክፈል የተገደደችበት ሁኔታ ተፈጥሯል።

የትናንት ታሪካችን በተጨባጭ እንደሚያመለክተው ፤ እንደሀገር ብዙ ተስፋ የተጣለበት ትውልድ እውቀት ሊፈጥር የሚችለውን ስክነት አጥቶ ፤ የማኅበረሰቡን ማኅበራዊ እና መንፈሳዊ እሴቶችን በሚጋጭ ጥራዝ ነጠቅነት ተወስዶ ፤ ለራሱም ሆነ ለሀገሩ ያልሆነበት ታሪካዊ ክስተት ተፈጥሯል ። የዚያ ጥራዝ ነጠቅነት እርሾም ዘመን ተሻግሮ አሁን ያለውን ትውልድ ዋጋ እያስከፈለ ይገኛል።

ችግሩ/ስብራቱ ዛሬ ላይ አድጎ ብዙ ዩኒቨርሲቲዎች እና ሰፊ የተማረ ኃይል ባለበት ሁኔታ የተለየ ገጽታ ሊላበስ አልቻለም ፤ ይህም በማኅበረሰቡ ውስጥ ለትምህርት የነበረውን ከፍተኛ መነቃቃት አደብዝዞታል ፤ ለችግሩ ዘላቂ መፍትሄ ካልተገኘለት በሀገሪቱ ዛሬም ሆነ ነገዎች ላይ ይዞት ሊመጣ የሚችለው ፈተና በቀላሉ የሚሰላ አይሆንም።

ብዙ በመሥራት ራሱን እና ሀገርን መለወጥ የሚችለውን ትውልድ በቁሙ በጠባቂነት እና በጥራዝ ነጠቅነት እየጎዳ ያለው ሀገራዊ የትምህርት ሥርዓት አሁን ላይ ግልጽ በሆነ መንገድ ማስተካከያ ሊደረግለት ይገባል፤ ይህንን ማድረግ ከተሳነንና ለዚህ የሚሆን ማኅበረሰባዊ መነቃቃት ካጣን እንደ ሀገር የምናስበው ብልጽግና ከምኞት ያለፈ ሊሆን አይችልም ።

በትምህርት ሥርዓቱ ላይ የሚስተዋለውን ችግር/ስብራት ለማከም የምንችለው የምዘና ሥርዓትን በማዘመን ወይም ሥርዓተ ትምህርትን በማሻሻል ብቻ አይደለም ። ከዚህም ባለፈ በትምህርት ላይ የሚደረገውን ሪፎርም ከታች በመጀመር ፤ በማኅበረሰባችን ውስጥ ከትምህርት ጋር በተያያዘ የተፈጠረውን አሉታዊ አስተሳሰብ በአግባቡ በመግራት ጭምር ነው።

በትምህርት ሥርዓቱ ላይ የሚስተዋለው ችግር /ስብራት ለማከም ፖለቲካዊ እና ተቋማዊ ብቻ ሳይሆን ማኅበራዊ መፍትሄ የሚፈልግ ነው። በትውልድ ግንባታ ውስጥ ሰፊ አስተዋጽኦ ያላቸውን ማኅበራዊ ተቋማትን ጠንካራ ድጋፍ የሚሻ ፤ የቤተሰብንም ንቁ ተሳትፎ ፤ የትውልዱንም የእውቀት መሻት መነቃቃት የሚጠይቅ ነው!


# አዲስ ዘመን

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስፈጻሚ**
ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22
ኢሜል ፡- epa@press.et

**ዋና አዘጋጅ**
አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**
ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ
ወረዳ 06
የቤት ቁጥር 319
ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et
ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**
ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com
ስልክ - 011-126-43-41
ፋክስ - 011-811-13-15
የዝግጅት ክፍል ፋክስ - 251-011-1-56-98-62

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**
ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ
ስልክ፡- 011 126 4200
Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

**የዜና ማዕከል ዋና አዘጋጅ**
ወርቁ ማሩ
Email:- workumaru2@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- እስማኤል አረቦ
- ቦጋለ አበበ

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**
ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73
ፋክስ - 011-126-58-12
ቴሌግራም - 097- 608-47-07 - Press

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**
ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ** ፡- ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


# ነፃ ሃሳብ

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው፡፡በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም፡፡

## ስለ ሀገር - እንመካከር

**መልካምሥራ አፈወርቅ**

ምንጊዜም በግል ከወጠኑት ሃሳብ ይልቅ በጋራ የመከሩበት ጉዳይ ሚዛን ደፍቶ ይገኛል፡፡ ይህ እውነት ከግለሰቦች አልፎ ወደ ሀገርና ሕዝብ በተሻገረ ጊዜም ትርጉሙ ከበድ ያለ ነው፡፡ ‹‹አንድ ሰው አይፈርድም አንድ እንጨት አይነድም›› እንዲሉ ከግላዊነት በላይ የአብሮነት ተግባር ፍሬው ያማረ፣ ውጤቱ የሰመረ ይሆናል፡፡

አሁን ላይ ሀገራችን ኢትዮጵያ በትኩረት እየመከረች ነው። ይህ ምክሯ በሕዝቦቿ የማንነት ህልውና ላይ የተመሰረተ ጽኑ አለት ሆኖ ተገንብቷል፡፡ እንዲህ መሆኑ ‹‹እያንዳንዱ - ለእያንዳንዱ ሁሉም ለብዙኃኑ›› እንዲያገባው ሆኖ የተዋቀረ ነው፡፡ ይህ የኢትዮጵያዊነት ጥብቅ ሰንሰለት በዋዛ እንዳይላላ፣ እንዳይፈታ ሆኖ ተጋምዷል፡፡

ሀገራዊ ምክክሮች ሲካሄዱ የተለያዩ ዓላማዎችን ከግብ ለማድረስ ሲባል ነው፡፡ እነዚህ ምክክሮች ደግሞ የአጭር ጊዜ ግብን ለማሳካትና መሠረታዊ ለውጥን ለማምጣት ጭምር የሚካሄዱ ናቸው፡፡ የአጭር ጊዜ ግብን ለማሳካት የሚካሄደው ምክክር ዋንኛ ዓላማ ቀውስን ለመከላከልና በየአጋጣሚው የሚፈጠሩ ግጭቶችን ለመፍታት ነው፡፡ ይህ የምክክር አይነት በተወሰነ ጥረት፣በአጭር ጊዜና በጥቂት ኃይሎች ብቻ ችግሮችን ለመፍታት የሚካሄድ ነው፡፡

ይህ አይነቱ ሂደት ጥቂት ተልዕኮችን ብቻ በመያዝ አነስተኛ በሚባል ቆይታ የአጭር ጊዜ ሂደት ይኖረዋል። በምክክሩ የሚሳተፉ አካላትም ውስን ቁጥር ያላቸው በመሆኑ ምክክሩን ለማቅለል የሚያግዙ ናቸው። እንዲህ አይነቱ የምክክር ይዘት ሰፊ መሰረት ያለው እንዲሆን አይጠበቅም። በርካታ የአካታችነት ቅርንጫፎች እንዲኖረውም አያስገድድም፡፡

መሠረታዊ ለውጥን ለማምጣት የሚደረገው ሀገራዊ ምክክር ግን በባህሪው ረዘም ያለ ጊዜ የሚወሰድ እንደመሆኑ በርካታ የህብረተሰብ ክፍሎች እንዲሳተፉበት የሚጋብዝ ነው፡፡ በዚህ ሂደትም የተለያዩ አመለካከቶች እንደሚንጸባረቁ ይጠበቃል፡፡ ምክክሩ በአንድ ሀገር በግልጽ በሚስተዋሉ መሠረታዊ ልዩነቶች ላይ የሚያተኩር ሲሆን፤ በየጊዜው እነዚህን ችግሮች ለማጥበብና ለመፍታት አበክሮ ይሰራል፡፡ በዚህ የምክክር ሂደት የሕዝብና የመንግሥት ግንኙነቶችን ዳግም ለመወሰን አልያም አዲስ የሚባል ውል ለማጠናከር መሰረት ይጣላል፡፡ ልዩነቶች ባሉበት አካባቢ ከኃይል አማራጭ ይልቅ ሰላማዊ አንድነት እንዲጠናከር ይሰራል። ሀገር ወደ አዲስና ዴሞክራሲያዊ ምዕራፍ እንድትሻገር የማድረግ ኃይልም አለው፡፡

ዓለም አቀፋዊ ተሞክሮዎች እንደሚጠቁሙት፤ ሀገራዊ ምክክር ማለት አዲስና ያልተለመደ ክስተት አይደለም፡፡ መረጃዎች እንደሚነግሩን የመጀመሪያው ሀገራዊ ምክክር መነሻ እ.ኤ.አ በ1989 በምሥራቅና መካከለኛው አውሮፓ ሰፍኖ ከነበረው የኮሚኒዝም ሥርዓት መንኮታኮት ጋር ይያያዛል፡፡ ይህ አጋጣሚ በዘመኑ በየሀገራቱ የተከሰተውን ፖለቲካዊ ክፍተት ለመድፈን የሚያስችል ምክንያትን ፈጠረ። በዚህ ወቅት ፖላንድ፣ ሀንጋሪ፣ ቼኮዝሎቫኪያ፣ ምሥራቅ ጀርመንና ቡልጋሪያ በችግሮቻቸው ዙሪያ ለመምከር በክብ ጠረጴዛ ዙሪያ ተቀመጡ፡፡

ተከታዩ ምክክር የታየው በአፍሪካና አፍሪካውያን ጉዳይ ላይ ነበር፡፡ እንደ እኤአ በ1990ዎቹ ገደማ ሥልጣን በያዙ መሪዎችና በዜጎቻቸው መካከል እየተፈጠረ የመጣው ልዩነት በርካታ ፈረንሳይኛ ተናጋሪ ሀገራትን ወደምክክር ጉባኤ እንዲያመሩ አድርጓቸዋል፡፡

በተመሳሳይ በዚሁ ጊዜ በደቡብ አሜሪካ አሳታፊ አስተዳደርን ለመመስረት ሲባል መግባባት ላይ የተደረሰበት ሀገራዊ ምክክር እንደቦሊቪያና ኮሎምቢያ የመሰሉ የደቡብ አሜሪካ ሀገራት በሕገ መንግሥት ጉዳዮች ላይ ከስምምነት እንዲደርሱ ያስቻለ ነው፡፡

በቅርቡ ደግሞ በመካከለኛው ምሥራቅና ሰሜን አፍሪካ ከአረብ ሀገራት ጋር ተያይዞ የተነሳው ትኩሳት በሌሎች ሀገራት ዘንድ ለመስፋፋት ኃይሉ የተጠናከረ ነበር፡፡ ይህ ችግር ስሩን ሰዶ ከመዛመቱ በፊት በሞሮኮ፣ሊቢያ፣ቱኒዚያና ግብጽ ምክክር ሊካሄድ ግድ ብሏል፡፡ ሱዳን ሊባኖስና ዮርዳኖስ፣ የመንና ባህሬንም ሀገራዊ ምክክሮችን በማካሄድ ስኬትና ውድቀቶቻቸውን ለመለየት ችለዋል፡፡

ዛሬ ሀገራችን በጽኑ እየተፈተነችበት ላለው የሰላም እጦት ሕዝቦቿ በእኩል መክረው፣ መፍትሔ ሊሹላት ይገባል፡፡ ሰላም ከሌለ የሁሉም ዜጎች ህልም ከቶውንም እውን መሆን አይችልም፡፡ ሰርቶ ማደር ውሎ መግባት፣ አይታሰብም፡፡ ሌት ተቀን እንቅልፍ የሚነሳን የሰላማችን ስብራት በወጉ ተጠግኖ ጤናው ይረጋገጥ ዘንድ በአንድ እሳቤ የመከረ፣ በጋራ ክንድ የተጣመረ አንድነት ዕውን ሊሆን ግድ ይላል፡፡

በሀገራችን የሚካሄደው ምክክር በኅብረተሰቡ፣ በመንግሥትና ሕዝብ መካከል ያለውን ግንኙነት ጤናማ በማድረግ ለዘመናት በችግር ሲጓዝ የቆየውን ውስጣዊ ቀውስ በውይይትና በሰላም ለመፍታት የሚያስችል ነው። በዚህ ሂደት የፖለቲካ ባህል ዳብሮ ምቹ የዴሞክራሲዊ ሥርዓት እንዲገነባ ፣ ወቅታዊ ችግሮች ለዘለቄታው ተፈተው አስተማማኝ ሰላም እንዲሰፍን ያላሰለሰ ጥረት ይደረጋል፡፡

በኢትዮጵያ መካሄድ የጀመረው ሀገራዊ ምክክር ሕዝብና ትውልድ ወደተሻለ ምዕራፍ እንዲሻገሩ የማድረግ ኃይል አለው፡፡ ሀገራዊ ምክክሩ በተለያዩ የኅብረተሰብ ክፍሎች መሀል የሃሳብ ልዩነቶች ሲፈጠሩና ከጦርነትና ግጭቶች ማግስት የፖለቲካ ክፍተት ሲያጋጥም ሰላምና መግባባት እንዲፈጠር አልሞ የሚሠራ ነው፡፡

በአንድ ሀገር ብሔራዊ ምክክር ሲኖር በማህበረሱ መሀል የሚከሰቱ ከባድ ያለመግባባት ችግሮችን በሰላማዊ መንገድ ለመፍታት ይቻላል፡፡ እንዲህ መሆኑ በመንግሥትና በሕዝብ መካከል የመተማመን ስሜት እንዲፈጠር ያግዛል፡፡ ምክክርን ባህል በማድረግና ዴሞክራሲያዊ ሥርዓትን በማጠናከር ልዩነቶችን በዘለቄታዊነት ለመፍታት ለሚደረገው ጥረትም ዓይነተኛ መፍትሔ ይሆናል፡፡

የሀገራዊ ምክክር መኖር በፖለቲካ ፣ማህበራዊና ኢኮኖሚ ያደገና የተለወጠ ሥርዓት ለመገንባት መሠረት ይጥላል፡፡ ይህ የምክክር ሂደት የራስን ችግር በራስ ለመፍታት የሚደረገውን ጥረት በተለየ ቅርበት መፍትሔ ለመስጠትም የሚያግዝ ነው፡፡

የሀገራዊው ምክክር ኮሚሽኑ የኮሚሽነር ምክር ቤቱ በሚያወጣው መመሪያ መሠረት አጀንዳዎች ተለይተው በተለያዩ አካላት ወሳኝ የሚባሉ ውይይቶች እንዲካሄዱ ያደርጋል፡፡ የኢትዮጵያ ሀገራዊ ኮሚሽን በሕግ ከተቋቋመበት ጊዜ አንስቶ በተለያዩ ፈተናዎች መሀል ተራምዷል፡፡

ኮሚሽኑ በእስከዛሬ ቆይታውም በአስር ክልሎችና በሁለት የከተማ አስተዳደሮች ከአንድ ሺ በላይ ወረዳዎች የአጀንዳ ማሰባሰብ ሂደት ነበረው፡፡ በአዲስ አበባ ከተማም በምክክር የምዕራፍ ሂደቱ የሚሳተፉ ተወካዮችን በማስመረጥ የአጀንዳ ማሰባሰብ ስራውን በትኩረት ቀጥሏል፡፡

ከግንቦት 21 ቀን ጀምሮ ለሦስት ቀናት በነበረው ምክክር የወረዳ ማህበራት፣ የኅብረተሰቡና የመንግሥት ተወካዮች፣ እንዲሁም የባለድርሻ አካላት ተሳታፊዎች ነበሩ፡፡ ሕዝቡን ወክለው አጀንዳ የሚሰጡ ወገኖችም በሚያቀርቧቸው ይዘቶች ላይ ሰፊ ምክክር እንደሚደረግ ይጠበቃል፡፡

አሁን ላይ በተጀመረው የአጀንዳ ማሰባሰብ ሂደት ማንኛውም ኢትዮጵያዊ ዜግነት ያለው ሁሉ በግልም ይሁን በጋራ አጀንዳውን ወደ ኮሚሽኑ የማምጣት መብት አለው። ምክክሩ ግልጽና ሁሉን አካታች ይሆን ዘንድም በስፋት እየተሠራበት ነው፡፡

ሀገር ካስማዋ ጸንቶ ሕዝቦቿ በኑሯቸው እንዲታመኑ ሰላም ይሉት ወሳኝ ጉዳይ ሊኖር ግድ ይላል፡፡ ልዩነቶች ተፈተው፣ ግጭትና ጦርነት ይቆም ዘንድ መካሪ፣ ዘካሪ ኃይል ያስፈልጋል፡፡ በየትኛውም ዓለም በልዩነት ፣ በሃሳብ ተነጣጥሎ መኖር አዲስ የሚባል አይደለም፡፡ ጉዳዩ በአጭሩ ካልተቋጨ ግን የዚህ መንገድ መጨረሻው ገደል እንደሚሆን መገመቱ ቀላል ነው፡፡

ልዩነቱ ሰፍቶ ግጭት የሚፈጥር ፣ጦርነት የሚያጭር በሆነ ጊዜ ችግሩ በምክክር እንዲፈታ የሚያስማማ፣ የሚያቀራርብ አካል ሊኖር ያስፈልጋል፡፡ ዛሬ ሀገራችን በመልከ ብዙ ችግሮች እየተፈተነች ነው፡፡ የፖለቲካ ልዩነት፣ የፍላጎት መለያየትን አስከትሎ ፣የመብትና የይገባኛል ጥያቄዎች ጤናማ መስመራቸውን ከሳቱ ቆይተዋል ፡፡

ነፍጥ አንግበው፣ ጫካ መሸገው፣ ከመንግሥት ጋር ፊትና ጀርባ የሆኑ ወገኖች ዛሬ ስለሀገርና ሕዝብ ሰላም ሲባል ልዩነታቸውን በመነጋገር፣ በመወያየት እንዲፈቱት ይጠበቃል፡፡ ለዚህ እውነት የብረት ድልድይ የሆነው ሀገራዊ የምክክር ኮሚሽን ከሁሉም ወገን የሚደርሰውን የአጀንዳ ጭብጥ በማሰባሰብ ወደሥራ ለመግባት ዝግጅቱን አጠናቋል፡፡

አሁን በአዲስ አበባ ከተማ የተጀመረው የአጀንዳ ግብአት በአጭር ጊዜ ተጠናቆ ወደ ቀሪ ክልሎች በመድረስ ተግባራዊ እንዲሆን የሁሉም ዜጎች ንቁ ተሳትፎ ይጠበቃል። ከሀገራዊ ምክክሩ የሚገኙ ቱርፋቶችን ለመካፈል ‹‹ሁሉም ወገን ለሁሉም›› የራሱን አሻራ ሊያኖርም ግድ ይለዋል፡፡ የዚህ እውነታ መልክ አንድም የሰላም፣ ሌላም ደግሞ የሀገር ጉዳይ ነውና ፡፡

# በክልሉ ከአምስት ሺህ 800 ቶን በላይ የሻይ ምርት ወደ ማዕከላዊ ገበያ ተልኳል

## -በቀጣዩ መኸር ወቅት የሚተከል ከአንድ ሚሊዮን በላይ የሻይ ችግኝ ተዘጋጀ

**ልጅዓለም ፍቅሬ**

አዲስ አበባ፡- በበጀት ዓመቱ ባለፉት ፲፩ ወራት ከአምስት ሺህ 800 ቶን በላይ የሻይ ቅጠል ምርት ወደ ማዕከላዊ ገበያ መላክ መቻሉን የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ሕዝቦች ክልል አስታወቀ፡፡ በቀጣዩ መኸር ወቅት በ35 ሄክታር መሬት ላይ የሚተከል ከአንድ ሚሊዮን በላይ የሻይ ችግኝ መዘጋጀቱን ተገልጿል፡፡

የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ሕዝቦች ክልል የቡና፣ ሻይና ቅመማ ቅመም ባለሥልጣን ዋና ዳይሬክተር አቶ አስራት መኩሪያ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንዳስታወቁት፤ በክልሉ በበጀት ዓመቱ ሰባት ሺህ 26 ቶን የሻይ ምርት ለመላክ ታቅዶ እስካሁን አምስት ሺህ 839 ቶን የሻይ ቅጥል ምርት ወደ ማዕከላዊ ገበያ በመላክ የእቅዱን 83 በመቶ ማሳካት ተችሏል፡፡

ለማዕከላዊ ገበያ ከቀረበው ውስጥ አንድ ሺህ 430 ወይም ከ24 በመቶ በላይ የሚሆነው ወደ ውጭ ሀገር ገበያ ኤክስፖርት የተደረገ መሆኑን አቶ አስራት ጠቁመዋል፡፡

የሻይ ምርት በክልሉ በከፋና ሸካ ዞኖች በሰፊው እየለማ ነው ያሉት አቶ አስራት፤ በአጠቃላይ ሁለት ሺህ 283 ሄክታር መሬት ላይ እየለማ ይገኛል ብለዋል፡፡

እንደ አቶ አስራት ገለጻ፤446 ሄክታር መሬት የሚሆነው በአርሶ አደሩ የለማ ነው፡፡ በዚህም ሴት አርሶ አደሮችን ጨምሮ አጠቃላይ 512 አርሶ አደሮች እየተሳተፉ ይገኛሉ፡፡

በተለይ በክልሉ ከፍተኛ ምርት የሚሰጡ አካባቢዎች ተለይተው በተገቢው መንገድ እንዲመረት ከማድረግ ጎን ለጎን በዘርፉ ያለው ኢንቨስትመንት ለማሳደግ ባለሀብቶችን የመሳብ ሥራዎች መሠራታቸውንም ነው አቶ አስራት የገለጹት፡፡

ክልሉ ከሻይ ልማት አንጻር ከፍተኛ አቅም ያለው ነው ያሉት አቶ አስራት፤ በተለይ አረንጓዴ ሻይ ለቀማ ላይ ለበርካታ ሰዎች የሥራ እድል መፍጠር መቻሉን አብራርተዋል፡፡ አቶ አስራት ፤ እስከ በጀት ዓመቱ መጨረሻ ድረስ በ35 ሄክታር መሬት ላይ የሻይ ቅጠል ልማት ለማልማት አንድ ሚሊዮን የሻይ ቅጠል ችግኝ ተዘጋጅቷል ብለዋል፡፡

የግብዓት አቅርቦትን ከማሳለጥ፣ የሰው ኃይል ከማልማት፣ ተጨማሪ አምራች ኢንዱስትሪዎችን ከመሳብ እንዲሁም በስፋት ችግኝ ጣቢያዎችን ከመክፈት ጋር ተያይዞ ተጨማሪ ሥራዎች እንደሚፈልግ ተናግረዋል፡፡

አቶ አስራት፤ በክልሉ አረንጓዴ ሻይ ቅጠል በሰፊው ተዘጋጅቶ ወደ ገበያ እየወጣ ይገኛል ያሉ ሲሆን የተዘጋጀው የሻይ ችግኝ በአርሶ አደሩ ለማልማት እቅድ ተይዟል፡፡

ከአየር ንብረት ለውጥ ጋር በተያያዘ የተወሰነ ለውጥ ቢኖርም እስካሁን ያለው በምርትና በአመራረት ሂደት ላይ ችግር አለማሳደሩን ገልጸው፤ በተለይ የዝናብ ስርጭቱ ተከታታይነት ስላለው ምርታማነትን እንዲጨምር እንዳደረገው አስረድተዋል፡፡

# ችግር ፈች የፈጠራ ሥራዎችን በመደገፍ ዓለም አቀፍ ተወዳዳሪነትን ማሳደግ ያስፈልጋል

**ታደሠ ብናልፈው**

ሆሳዕና፡- ችግር ፈች የሆኑ የፈጠራና የምርምር ሥራዎችን በማሳደግና በመደገፍ የኢኮኖሚያዊ ተወዳዳሪነትን ማሳደግ ያስፈልጋል ሲሉ የማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል ምክትል ርዕሰ መስተዳድር አቶ አንተነህ ፍቃዱ ተናገሩ።

በማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል የመጀመሪያው የሳይንስና የፈጠራ ሥራዎች ዐውደ ርዕይና ውድድር “ማዕከላዊ ኢትዮጵያን የሳይንስ፣ የኢኖቬሽንና የቴክኖሎጂ ማዕከል እናድረግ” በሚል መሪ ቃል ሲካሄድ የቆየው ከትናንት በስቲያ ተጠናቋል።



**አቶ አንተነህ ፍቃዱ**

የማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል ምክትል መስተዳድር አቶ አንተነህ ፍቃዱ በዐውደ ርዕዩ ማጠቃለያ ላይ እንደተናገሩት፤ በፈጠራና በምርምር የተገነባ ኢኮኖሚ ዘላቂ ልማትን ለማስመዝገብና ተወዳዳሪ ለመሆን ያስችላል። ችግር ፈች የሆኑ የፈጠራና የምርምር ሥራዎችን በማሳደግና በመደገፍ የኢኮኖሚያዊ ተወዳዳሪነትን ማሳደግ ያስፈልጋል፡፡

የፈጠራና የምርምር ሥራ ዘላቂ ልማትና ኢኮኖሚያዊ እድገትን በማስመዝገብ ብልፅግናን እውን ለማድረግ ትልቅ አቅም አለው ብለዋል።

የፈጠራ ሥራ የሀገርን ኢኮኖሚ በማሳደግ በሁሉም ዘርፍ ተፅኖን ለመፍጠር ያስችላል ያሉት ምክትል ርዕሰ መስተዳድሩ፤ በፈጠራና በምርምር ብልፅግናን እውን ለማድረግ እየተሠራ ነው ሲሉ ገልጸዋል።

የሀገርን እድገት ዘላቂ በማድረግ ምርትና ምርታማነትን ለማሳደግ የፈጠራ ሥራ አስፈላጊ መሆኑን አመልክተው፤ ምርትና ምርታማነት ለማሳደግ የፈጠራ ሥራዎች ላይ በትኩረት መሥራት ተገቢ ነው ሲሉ ተናግረዋል።

ተለዋዋጭ በሆነ ዓለም ላይ ዘላቂ ልማትና ኢኮኖሚያዊ እድገት እንዲኖር የፈጠራና የምርምር ሥራ አስፈላጊ ነው ያሉት አቶ አንተነህ፤ በክልሉ እየተሠሩ ያሉ የፈጠራ ሥራዎች ዘላቂ ልማትን ለማስመዝገብ የሚያስችሉ ናቸው ሲሉ ገልጸዋል።

የሀገርን ኢኮኖሚ ለማሳደግ፣ የምርት ጥራትን ለማረጋገጥና ምርትና ምርታማነትን ለመጨመር ሳይንሳዊ ፈጠራና ቴክኖሎጂ አስፈላጊ ነውም ሲሉ አብራርተዋል።

የፈጠራ ሥራ ፣ ለዜጎች የስራ እድል ለመፍጠር፣ በዓለም ገበያ ተወዳዳሪ ለመሆን፣ አይበገሬ ኢኮኖሚያዊ አቅም ለመፍጠር፣ የኑሮ ደረጃን ለማሻሻልና መሰል ጥቅሞችን ለማግኘት ያግዛል ሲሉ ተናግረዋል።

ጥራት ያለው ትምህርት ለዜጎች መስጠት፣ ግብዓት ማሟላት፣ኢንተርፕራይዞች ላይ ኢንቨስት ማድረግ በአጠቃላይ የፈጠራ ምህዳሩን ምቹ ማድረግ ለፈጠራ ሥራዎች በሚፈለጉት ልክ እንዲያድጉ ያደርጋል ብለዋል።

አዳዲስ ሃቦችን በማመንጨትና ወደ ተግባር በማውረድ የሚሰሩ የፈጠራ ሥራዎች የማህበረሰብን ችግርን የሚፈቱ ናቸው ያሉት ምክትል ርዕሰ መስተዳድሩ፤ ለፈጠራ ሥራ ትኩረት መስጠት ያስፈልጋል ሲሉ ገልጸዋል።

የቴክኖጂ ምርቶችን በቀላል ዋጋ ለማህበረሰቡ ተደራሽ ለማድረግ በሀገር ውስጥ በፈጠራ ሥራ መተካት ተገቢ ነው፤ በክልሉ እየተሠሩ ያሉ ፈጠራዎችን ለማህበረሰቡ በቀላል ዋጋ ተደራሽ ለማድረግ እየተሠራ እንደሚገኝም ተናግረዋል።

በኢኮኖሚው እድገት ላይ የሚገጥሙ ተግዳሮቶችን ተሻግሮ ዘላቂ ልማትን ለማሳደግና ዘላቂ ለማደረግ የፈጠራ ሥራ አስፈላጊ ነው ብለዋል።

ሀገሪቱ ብዙ ሀብትና የፈጠራ ባለቤቶች ያላት ናት ያሉት አቶ አንተነህ፤ ያላትን የተፈጥሮ ሀብትና የፈጠራ ባለቤቶችን በመጠቀም ዘላቂ ልማት ለማስመዝገብ መሥራት ያስፈልጋል ሲሉ ጠቁመዋል።

# የአክሱም አውሮፕላን...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

እንደቆየ አውስተዋል፡፡

የኢትዮጵያ አየር መንገድ የአውሮፕላን ማረፊያው ታህሳስ ወር 2016 ዓ.ም የጀመረው የጥገና ሥራ በፍጥነት ተጠግኖ ወደ ሥራ እንዲገባ ባደረገው ጥረት በተያዘለት ጊዜ ሥራው ተጠናቆ ሰኔ 02 ቀን 2016 ዓ.ም መደበኛ አገልግሎቱ ይጀምራል ሲሉ ገልፀዋል፡፡

የከተማ ነዋሪ ለሰላም እና ለአብሮነት ያለው እሴት ከፍተኛ መሆኑን በመግለፅ፤በኤርፖርቱ ሥራ መጀመር ብዙ እንግዶች ሊመጡ ስለሚችሉ ነዋሪው እንደ ከዚህ ቀደሙ የከተማዋ ሰላም እና ፀጥታ በማስከበር እና እንግዶቹ ተቀብሎ ማስተናገድ እንደሚኖርበት ተናግረዋል፡፡

አክሱም ከተማ ባሏት ቅርሶች እና ታላላቅ ታሪኮች የዓለም ከተማ ናት ያሉት ከንቲባው፤ በሆቴል ፣ ቱሪዝም እና አገልግሎት ዘርፎች የሚደረጉ ኢንቨስትመንቶች ተጠናክረው እንዲቀጥሉ በትኩረት ይሠራል ብለዋል፡፡

የኤርፖርቱ እንደገና ሥራ መጀመር ተዳክሞ የቆየው የኢኮኖሚ ፍሰት እንደሚያነቃቃው በመጥቀስ፤ በውጭ ሀገር ለረጅም ጊዜ ከቤተሰብ ጋር ያልተገናኘው የትግራይ ዲያስፖራ እና የከተማዋ ጎብኚዎች የተፈጠረው ዕድል በመጠቀም የሀገራቸውን ቅርስ እንዲጎበኙ እና የኢንቨስትመንት ሥራዎች ላይም እንዲሳተፍ ጥሪ አቅርበዋል፡፡

# በሜዲካል ኮሌጁ...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

ለውጡ በጊዜ ሂደት ውስጥ የሚገኝ በመሆኑ ታካሚዎች ረዘም ላለ ጊዜ ህክምናቸውን እንደሚከታተሉ ገልጸዋል፡፡

በሆስፒታሉ የሚሰጠው አገልግሎት ውጤታማ ነው በማለት የገለጹት ዶ/ሩ፣ ታካሚዎች በተሻለ ፍጥነት ለውጥ ለውጥ ማምጣት እንዲችሉ የቤተሰብ ክትትል ወሳኝ መሆኑን አንስተዋል፡፡

እንደ ዶ/ር አካሉ ማብራሪያ፣ ህክምናው በባለሙያ እርዳታ ብቻ የሚሰጥ ሳይሆን የቤተሰብንም ተሳትፎ የሚፈልግ በመሆኑ በተቻለ መጠን ቤተሰብ ላይ ግንዛቤ የመፍጠር ሥራዎች ይሠራሉ፡፡

ከቤተሰብ አካባቢ ታካሚውን በመርዳት በኩል ክፍተቶች መኖራቸውን የጠቆሙት ዶ/ር አካሉ፤ ከቤተሰብ ጥሩ እገዛ የሚያገኙ ህጻናትም ሆኑ አዋቂዎች ታካሚዎች እገዛ ከማይደረግላቸው ይልቅ ፈጣን ለውጥ እንደሚያመጡም አስታውቀዋል፡፡

የሥነ ልሳን ከሚገጥማቸው ህጻናት መካከል አብዛኛውን ቁጥር የሚይዙት ብዙ ጊዜያቸውን ከስልክና ቴሌቪዥን ጋር ሲያሳልፉ የነበሩ ህጻናት መሆናቸውንም ዶ/ር አካሉ አንስተዋል፡፡

አፉቸውን መፍታት ባለባቸው ጊዜ መፍታት ያልቻሉ እድሜያቸው ከ3 ዓመትና ከዚያ በላይ የሆኑ ህጻናት ህክምናውን መውሰድ ይችላሉ ያሉት ዶ/ሩ፤ ከአደጋና ከተለያዩ በሽታዎች ሳቢያ የመናገር ችግር የገጠማቸው በማንኛውም የእድሜ ክልል ውስጥ የሚገኙ ሰዎችም ህክምናውን መውሰድ እንደሚችሉም ጠቁመዋል፡፡

ህክምናው ተጨባጭ ለውጥ ማምጣት የሚያስችል መሆኑንም እንዲሁ ጨምረው ተናግረዋል፡፡

እርሳቸው እንዳሉት፣ ከህክምናው ጋር ተያይዞ የባለሙያ እና የህክምና መሳሪያ እጥረት ቢኖርም ከተለያዩ ድርጅቶች በተገኙ ድጋፎችን በመታገዝ ህክምናውን ለመስጠት ጥረት እየተደረገ ይገኛል፡፡

ይህ ህክምና መስጠት ያልተጀመረባቸው የአፍሪካ ሀገራት መኖራቸውንም አንስተው፣ እጥረቶች ቢኖሩም ህክምናው በሀገር ውስጥ መሰጠት መቻሉ መልካም ነገር ነው ብለዋል፡፡

ከሌሎች ያደጉ ሀገራት አንጻር ሲታይ ግን በባለሙያ፣ በህክምና አሰጣጥና ከመሳሪያ አቅም ጋር ተያይዞ ብዙ የሚቀረን መሆናችንን አመላክተዋል፡፡

# ኪነ-ጥበብን በመጠቀም በልኩ ያልታወቀውን...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

ኪነ-ጥበብ አርቃ የማየትና የመጠየቅ አቅም አላት፤ ይህን አቅም ወደተግባር በማዋል የኢትዮጵያን ባህልና ታሪክ ማስተዋወቅ እንዲሁም ትስስሩን ማጠናከር ይገባል ብለዋል።

ኢትዮጵያ ቅዱስ ያሬድን የመሰለ የመፍጠር አቅም ያለው ታላቅ የኪነ-ጥበብ ሰው አፍርታለች ያሉት ጠቅላይ ሚኒስትሩ፤ ጠቢቡንና ሥራዎቹን ግን ምን ያክል በልኩ አውቀን አስተዋውቀነዋል የሚል ጥያቄ ይነሳል ሲሉ ተናግረዋል።

ታሪካችንን፣ ባህላችንንና አጠቃላይ እሴቶቻችንን ለማስተዋወቅ ደግሞ ኪነ-ጥበብ ዋነኛ መሣሪያ በመሆኗ ልንጠቀምባት ይገባል ሲሉ መልዕክት አስተላልፈዋል።

ኢትዮጵያም ሰፊ ታሪክና ቱባ ባህል ያላት ሀገር እንደመሆኗ ኪነ-ጥበቡን በመጠቀም ትውልዱ ስለሀገሩ እንዲያውቅ የውጭውም ዓለም ስለኢትዮጵያ እንዲገነዘብ ለማድረግ በትኩረት መሥራት እንደሚገባ አሳስበዋል።

ኪነ-ጥበቡን ስናስብ ያለፈ ታሪክና ሥራዎችንም መዘንጋት አይገባም ያሉት ጠቅላይ ሚኒስትሩ፤ በአንድ ዓይኑ ወደኋላ የሚያይ ሀገር ጥበበኛ ነው ምክንያቱም የኋላውንም የሚያይ የፊቱንም ያልዘነጋ ነው ሲሉ አስረድተዋል። በታሪክ ቅብብሎሽ ሂደት የተገነባ ትስስር ይበልጥ ውጤታማ እንደሚሆን ጠቁመዋል።

በማዕከሉ እንድንገኝ ያደረገን ምክንያትም የሙዚቃ ትምህርት ቤቱ ቅዱስ ያሬድንና ዕውቁን የጥበብ ሰው ፕሮፌሰር አሸናፊ ከበደን ስለሚያስታውሰን፤ በቀጣይ ደግሞ የማዕከሉ ኃላፊ የሆነውን የሙዚቃ ሰው ግርማ ይፍራሸዋን የያዘና የተሳሰረ ታሪክ ያለው መሆኑ ነው ብለዋል።

ይህን አይነት የትውልድ ቅብብሎሽ በማጠናከር በኪነ-ጥበቡ ለሀገር የሚተርፍ ውጤታማ ሥራ ማከናወን ተገቢ ነው ሲሉ ተናግረዋል።

የሙዚቃዊ ጥበባት ማዕከሉ በስማቸው የተሰየመላቸው ፕሮፌሰር አሸናፊ ከበደ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የያሬድ የሙዚቃ ትምህርት ቤት መስራችና የመጀመሪያው ዳይሬክተር በመሆን አገልግለዋል።

“የኢትዮጵያ የሙዚቃ አቀናባሪ” ስያሜን ያተረፉት ፕሮፌሰር አሸናፊ ከበደ “ባለ ዋሽንቱ እረኛ” ወይም “The Shepered Fluitist” በተሰኘው ክላሲካል ሙዚቃቸው በስፋት ይታወቃሉ።

ፕሮፌሰሩ ለሕትመት ያበቁትን “Roots of Black Music” መጽሐፍ፤ በርካታ ጥናታዊ ፅሁፎችና የተለያዩ የጥበብ ሥራዎችንም አበርክተዋል።

በመድረኩ የትምህርት ሚኒስትርና የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ቻንስለር ፕሮፌሰር ብርሃኑ ነጋን ጨምሮ ሚኒስትሮች፤ የተለያዩ ሀገራት አምባሳደሮች፤ የአፍሪካ ህብረት ተወካዮችና ጥሪ የተደረገላቸው እንግዶች ተገኝተዋል።

የማዕከሉ ኃላፊ ግርማ ይፍራሸዋና የትምህርት ቤቱ ኦርኬስትራ ለታዳሚዎች የተለያዩ ጥበባዊ ሥራዎችን አቅርበዋል።

ፖለቲካ እና ልዩ ልዩ

# ነፃ ሃሳብ



በቁምላቸው አበበ ይማም (ሞሼ ዳያን)
fenote1971@gmail.com

ቁምላቸው አበበ በአማራ ባህል፣ ቱሪዝምና ማስታወቂያ ቢሮ፤ በኢትዮጵያ ዜና አገልግሎት፤ በደቡብ መገናኛ ብዙኀን፤ በጋዜጠኝነትና በታሪክ ባለሙያነት ያገለገሉ ሲሆን፤ የደቡብ ኤፍ ኤምን ከባልደረቦቻቸው ጋር በመሆንም አቋቁመዋል። በፌዴራል ውሃ ስራዎች ኮንስትራክሽን ድርጅትና በአለ በጅምላ በኮሙዩኒኬሽን ዳይሬክተርነት አገልግለዋል። ከአአዩ በቋንቋና ታሪክ የመጀመሪያ ዲግሪያቸውን የሰሩ ሲሆን፤ በዚሁ ዩኒቨርሲቲ በጋዜጠኝነትና ኮሙዩኒኬሽን ሁለተኛ ዲግሪያቸውን በማጠናቀቅ ላይ እያሉ ባጋጠማቸው ድንገተኛ ህመም ተስተጓጉሏል። ጥልቅ ሀሳብ ያዘሉ ወቅታዊ ጉዳዮች ላይ የሚያተኩሩ ፁሑፎችን በማህበራዊ ሚዲያና በተለያዩ ጋዜጦች በማውጣት ይታወቃሉ።

## ወርቃማ ሕግ ገሸሽ አድርገን የየራሳችንን ወርቅ ቅብ አብለጭላጭ ሕግ ያወጣን መስሏል

ኢትዮጵያውያን ከ99 በመቶ በላይ አማኞች ናቸው የሚል የጨረታ /Clichy / እውነት አለ። የክርስትና ፣ የእስልምና ፣ የይሁዲ ወይም የሌላ ዕምነት ተከታዮች ናቸው። ጥያቄው እኔን ጨምሮ ይሄን እምነታቸውን በተግባር ይኖሩታል የሚለው ነው። አዎ ! አብዛኞዎቹ ዕምነታቸውን በህይወታቸው ገልጠው ይኖራሉ። ቁጥሩ ቀላል የማይሆን አማኒ ግን ከዕምነቱ አስተምህሮና ቀኖና በተቃራኒው መቆሙ ጻሐይ የሞቀው የአደባባይ ሀቅ ከሆነ ውሎ አድሯል።

ቁጥራችን ቀላል ያልሆነ ይሄን እምነታችንን በህይወታችን ስለማንኖረውና ስለማንገልጠው ዛሬም ሆነ ትናንት ሀገራችን ፈተና ላይ ወድቃለች። ልዩነት፣ ጥላቻና መጠራጠር መልካሙን ተቆጣጥሮታል። ሀገራችንና ሕዝባችን እረፍት አጥተዋል ። ሃይማኖታችንና ዕምነታችን ወደ ሰውነት ተራ መመለስ ተስኗቸዋል። ከራሳችንም ከአምላኩም ተጣልተናል። በዓላትን በነቂስ ወጥተን አክብረን ወደየቤታችን ስንመለስ ልዩነታችንን ፣ ጥላቻችንን፣ መጠራጠራችንና አጠቃላይ ፖለቲካችን የቱ ጋ ነበር ያቆምነው ብለን እንደ እሪያ ወደ ጥፋታችን እንመለሳለን ። የጥላቻንና የልዩነትን ፍላጻ ወደ ሚያንበለብሉት ማህበራዊና መደበኛ ሚዲያዎች ጎራ እንቀላቀላለን። ውጊያውን እንመራለን።

ከገባንበት ሁለንተናዊ ቀውስ ለማገገምም ሆነ በሀገራችን ዘላቂ ሰላምና አንድነት ለማረጋገጥ የጣልናቸውንና የረሳናቸውን ዕምነቶች ፣ ሃይማኖቶች ባህላዊ ወረቶች እንዲያንሰራሩና መልሰው እንዲያቆጠቅጡ ሌት ተቀን መስራት ይጠበቅብናል። ጎን ለጎን መንግሥት ልዩነትንና ጥላቻን የሚጎነቁሉ አስተሳሰቦችን ከስር ከስር የማስወገድ ኃላፊነት አለበት። ይህን ማድረግ ካልቻልን ከገባንበት ፈተና መውጣት አይቻልም። ከፈተናዎቻችን አንዱ የግብይት ሥርዓታችን ነውና እሱን በአለፍ ገደም አይተን ወደ ዛሬው መሰናዘሪያችን ወደ ወርቃማው ሕግ እናልፋለን።

በሀገራችን የግብይት ሥርዓት ላይ የምናየው ስስት፣በአንድ ጆምበር የመከበር አባዜ፣ኪሎ መቀሸብ፣በምግብ ሸቀጦች ላይ ባእድ ነገር መጨመር፣ አመሳስሎ ማምረት፣የመጠቀሚያ ጊዜያ ቸው ያለፈባቸውን ምርቶች ለገበያ ማቅረብና ሌሎች ፈተናዎች አማኝ ከሆነች ሀገር ለዛውም የሦስቱ አብርሃማዊ ዕምነቶች ማለትም የክርስትና፣የእስልምና እና የይሁዲ ዕምነቶች ቀደምት ተቀባይ ከሆነች ሀገር የሞራል ስሪት ጋር የሚጋጭ ነው።

የግብይት ሥርዓቱን አነሳን እንጂ ነገረ ስራችን ሁሉ አማኝ ያለበት ሀገር ላይ መሆኑ ግራ ያጋባል። ምን ነካን ያስብላል። በጥቂት አስርት አመታት ውስጥ አንተ ትብስ አንቺ ትብሽ መባባል፣መተሳሰብ፣መተዛዘን እንዴት እንዲህ ሊዳከም ቻለ፤ፈሪአ ፈጣሪ የነበር ሕዝብ ዛሬ ምናገኘውና ተጨካከነ ብሎ መጠየቅ የአባት ነው። እየሆነ ያለው ግን ከዚህ በተቃራኒው ነው። የሚጠይቅም የሚመልስም ብርቅ ሆኗል። ከዛ ይልቅ መላመድን መርጠናል። ባላየ ባልሰማ ማለፈን በጀ ብለናል።

"አንተ ላይ እንዲሆን የማትፈልገውን ነገር በሌላው ላይ አታድርግ።" የሚለውን ወርቃማ ሕግ ገሸሽ አድርገን የየራሳችንን ወርቅ ቅብ አብለጭላጭ ሕግ ያወጣን መስሏል። መጭበርበር፣ማጭበርበር፣ መወሻሸት፣መከዳዳት፣ማታለል፣መታለል፣ወዘተረፈ የዕለት ተዕለት ምሳችን የሆነ ይመስላል።አለማዊ ሕጉም አስርቱ ትዕዛዛትም ሆነ ስነ ምግባርና እሴት አባ ከና ሚላቸው እየጠፉ ነው።

እውነት ለመናገር ከዚህ የውድቀት ቁልቁለት የሚገታንና ወደ ቀደም ከፍታችን የሚመልሰን አለማዊና መንፈሳዊ ተቋም አለ ወይ ብሎ መጠየቅ በራሱ ያባባል።ያስጨንቃል። መልሱ ምንም ይሁን የዜግነት ድርሻን መወጣት ሌላው ቢቀር ከህሊና ሙግትና ክስ ያድናል።ፖሊስ አቁመን፣ዳኛ ሰይመን፣የሃይማኖት አባት ሰምተን ሰው መሆን ካቃተን እስኪ ወርቃማውን ሕግ እንሞክረው።

ላንተ ቢደረግልህ ምትወደውን ለሌሎችም አድርግ፤ባንተ ላይ እንዲደረግ የማትፈልገውን በሰው ላይ አታድርግ። ብዙ አይነት ሕጎች አሉ። ይህኛው ሕግ ግን ወርቃማ በሚል የተቀመጠው ለአብዛኞቹ አለማዊም ሆነ መንፈሳዊ ሕጎች መሰረት በመሆኑ ነው።ወርቃማው ሕግ ውስጣችን ሰርፆ የመግባት አቅም አለው። እንደሌሎች ሕጎች ሕግ አስከባሪ ፈርተን የምንተገብረው አይደለም።

ወርቃማው ሕግ ከሰዎች ጋር ያለንን ግንኙነት ወደ መልካምነት ይቀይራል። ሰዎችን የሚጎዳ ነገር የማናደርገው በውል ስለታሰርን ወይም ወንጀል ስለሆነ አይደለም እኛ ላይ ቢደረግ ስለማንወድ ነው። ይህ ሕግ ማህበረሰቡንም ወደ ተሻለ ደረጃ የሚያሸጋግር ነው። ኢፍትሐዊነትን እና የሌሎችን በደልና ቅሬታም ይቀንሳል።ይህን ወርቃማ ሕግ ለማወቅ ሕግ ት/ቤት መግባት ወይም የሕግ መጽሐፍትን መመርመር አያስፈልግም።

ልብ ብለን ካስተዋልነው በእያንዳንዳችን ልብ ውስጥ ተከትቧል። አጭር እና ግልፅ ነው።"ላንተ ቢደረግልህ የምትወደውን ለሌሎችም አድርግ !!"ይህን ታላቅ ሕግ አውቀህ በትክክል ከተገበርከው በቃ! ሀሪ ጌንስለር የጻፈውን አጣቅሼ የወርቃማውን ሕግ ጥቂት ወርቃማ ነጥቦች ላንሳልህ ይለናል ኪዳኔ መካሻ። እንዲህ ሆነ ፤አንድ ዝንጀሮ እና አሳ ከወንዝ አጠገብ ይኖሩ ነበር። ዝንጀሮው ወርቃማውን ሕግ ስለሚያከብር ሁሌም ለሱ እንዲደረግለት የሚፈልገውን ለሌሎችም ያደርግ ነበር።

አንዳንዴ ግን ሕጉን የሚተገብረው በቅጡ ሳያስተውል በየዋህነት ነበር። አንድ ቀን ኃይለኛ ጎርፍ መጣና እየባሰ ሲሄድ ዝንጀሮው ተንጠላጥሎ ከወንዙ አቅራቢያ ያለው ዛፍ ላይ ወጣ። ቁልቁል ሲመለከትም የጎርፉ ውሃ ትንሿን ወንዝ ስለሞላት አሳውን ሲያንገላታው ተመለከተ። ዝንጀሮው 'እኔ ውሃው እንዳይደርስብኝ መሸሸ ፈልጌ ዛፍ ላይ ወጥቻለሁ አይደል?ለአሳውስ? እኔ እንዲደረግልኝ የምፈልገውን ለሱም ማድረግ አለብኝ' ብሎ አሰበና ከዛፉ ላይ ወርዶ ከወንዙ ውስጥ አሳውን አውጥቶ የዛፉ ቅርንጫፍ ላይ አስቀመጠው።እንዳሰበው ሳይሆን ቀረና ወዲያውኑ አሳው ሞተ።

ይህ የአፍሪካውያን ብሒል ወርቃማውን ሕግ በአግባቡ መረዳትና እኛ የምንፈልገውን ነገር ለሌሎች ስናደርግ በሌሎች እና በኛ መሀል ያለውን ልዩነት መረዳት እንዳለብን ይጠቁማል። ከየዋሁ ዝንጀሮ አይነት ስህተት ለመጠበቅ "እኔ ሌላው ሰው በሚገኝበት ሁኔታ ላይ ብሆን ይህ የማደርገው ነገር እንዲደረግብኝ ፍቃደኛ ነኝን?" ብለን መጠየቅ አለብን።

አንድ አደገኛ ወንጀለኛ ነበር። ለብዙ ጊዜ ሀገሩን ሲያምስ ኖሮ አንድ ቀን ተያዘና ታሰረ ክስም ቀረበበት። ክሱ የቀረበበት ፍርድ ቤት ግድግዳ ላይ "ለሌሎች አንተ እንዲሆንልህ የምትወደውን አድርግላቸው።" የሚል ጥቅስ ተለጥፏል። ይህን የተመለከተው ወንጀለኛ፤"ክቡር ዳኛ እርሶ በኔ ቦታ ቢሆኑ ወደ እስር ቤት መግባት አይፈልጉምና በወርቃማው ሕግ መሰረት እርሶ ላይ እንዲሆን የማይፈልጉትን እኔ ላይ ፈርደው ወህኒ ሊከቱኝ አይገባምና በነፃ ይልቀቁኝ" ሲል አመለከተ።

ዳኛው "ወርቃማውን ሕግ በትክክል ስላልተረዳከው ነው ተከሳሽ። በታላቁ ሕግ መሰረት አንተን በእስር መቅጣት እችላለሁ። ምክንያቱም እኔም እንዳንተ አደገኛ ወንጀለኛ ብሆን አሁኑኑ ወደ እስር ቤት ለመላክ ፍቃደኛ ነኝ።" ብለው ቀና አሉና "እንዲህ አይነት ወንጀል ከሰራሁ አደራ እንዳትለቁኝ ወደ ወህኒ ወርውሩኝ።" በማለት ለችሎቱ ታዳሚ አሳሰቡ።ወንጀለኛውንም ተገቢውን የእስር ቅጣት ፈረዱበት።

ወንጀለኛው ወርቃማውን ሕግ አለሳልሶ በመተርጎም በፍፁም ከሌሎች ፍላጎት ጋር የሚቃረን ነገር አታድርግ በማለት ነው ከቅጣት ለማምለጥ የሞከረው።ሆኖም ብዙ ጊዜ ሌሎች የማይፈልጉትን ነገር ማድረግ ያስፈልገናል። እሳት ውስጥ እጁን የሚከት ሕፃንን መከልከል አለብን፣ያለ ሸያጭ ደረሰኝ የሚሸጥልንን ነጋዴ እምቢ ማለት አለብን፣ ሙሰኞችን ማጋለጥ፣ ወንጀለኞችን ለሕግ ማቅረብ አለብን። ይሄን የምናደርገው እኛም በእንዲህ አይነት ሁኔታ ውስጥ ብንገኝ እኛ ሌላው ላይ ያደረግነው ያ ሰው የማይፈልገው ነገር እንዲደረግብን ፍቃደኛ እንሆናለን።

ወርቃማው ሕግ ሌሎችን የሚጎዳ ተግባር የሚፈፅሙ ሰዎች የማይፈልጉትን ነገር እንድናደርግ ስለሚፈቅድልን ነው። ሕጎች የወጡት የሰዎችን ባህሪ ለመቆጣጠር ነው። በእርስ በርስ ግንኙነታችን ውስጥ በሚከሰት የፍላጎትና የጥቅም ግጭት እራሳችንን ወይም ሌላውን ለመጥቀም ሌሎችን እንዳንጎዳ ነው ዋነኛ አላማቸው ። ሕጎችን አውቆ የራስን መብት ማስከበር ግዴታንም መወጣት በሕግ ተጠያቂ ከመሆን ያድናል።

ከየትኛውም ሕግ በላይ በማንኛውም የሕይወታችን እንቅስቃሴ ልንጠቀምበት የሚገባን አስፈላጊውና ታላቁ ሕግ ግን ይህ ወርቃማው ሕግ ነው።ለማንኛውም የሕጎች ሁሉ ምንጭ የሆነውን ታላቁን ሕግ እናከብረው። ምንም ነገር ከማድረጋችንም በፊት "የማደርገው ነገር እኔ ላይ ቢደረግ እወዳለሁ?"የሚለውን ይህን የወርቃማውን ሕግ ወርቃማ ጥያቄ እራሳችንን መጠየቁን አንዘንጋ!! እስኪ እውነታውን ከመጽሐፍ ቅዱስ አንጻር ደግሞ በወፍ በረር እንቃኘው።

"ወርቃማው ሕግ" የሚለው አገላለጽ መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ አይገኝም። ብዙ ሰዎች ይህን አገላለጽ የሚጠቀሙት ኢየሱስ ያስተማረውን አንድ የሥነ ምግባር ደንብ ለማመልከት ነው። ኢየሱስ ታዋቂ በሆነው የተራራ ስብከቱ ላይ የሚከተለውን የሥነ ምግባር ደንብ ሰጥቶ ነበር። "ሰዎች እንዲያደርጉላችሁ የምትፈልጉትን ነገር ሁሉ እናንተም አድርጉላቸው። **"ማቴዎስ 7:12፤ ሉቃስ 6:31፤ ።**

ወርቃማው ሕግ፣ ሌሎች እንዲይዙን በምንፈልግበት መንገድ እነሱን እንድንይዝ ያበረታታናል። ለምሳሌ አብዛኞቻችን ሌሎች ሰዎች አክብሮት፣ ደግነትና ፍቅር ሲያሳዩን ደስ ይለናል። በመሆኑም እኛም ለሌሎች "እንዲሁ" ልናደርግላቸው ይገባል። ወርቃማው ሕግ ከሁሉም የሕይወታችን ዘርፎች ጋር በተያያዘ ይሠራል። ለምሳሌ ትዳራችንን ያጠናክርልናል። **ኤፌሶን 5:28, 33** ወላጆች ልጆቻቸውን ጥሩ አድርገው እንዲያሳድጉ ይረዳቸዋል። **ኤፌሶን 6:4፤** በጓደኛሞች፣ በጎረቤታሞች እና በሥራ ባልደረቦች መካከል ጥሩ ግንኙነት እንዲኖር ያደርጋል። **ምሳሌ 3:27, 28፤ ቆላስይስ 3:13፤**

ወርቃማው ሕግ በተለምዶ ብሉይ ኪዳን በሚባለው የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ውስጥ የሚገኘውን አብዛኛውን ሃሳብ ጠቅልሎ የያዘ ነው። ኢየሱስ ስለ ወርቃማው ሕግ ሲናገር "ሕጉም (የመጀመሪያዎቹ አምስት የመጽሐፍ ቅዱስ መጻሕፍት) ሆነ የነቢያት ቃል (የትንቢት መጻሕፍት) የሚሉት ይህንኑ ነው" ብሏል። **(ማቴዎስ 7:12)** በሌላ አባባል ወርቃማው ሕግ በብሉይ ኪዳን መጻሕፍት ውስጥ በዋነኝነት የተገለጸውን መሠረታዊ ሃሳብ ጠቅለል አድርጎ ይዟል፤ ይህ ሃሳብ 'ባልንጀራህን እንደራስህ ውደድ' የሚለው ነው። **ሮም 13:8-10፤**ወርቃማው ሕግ፣ ሰጥቶ የመቀበል ጉዳይ ነው? አይደለም። ወርቃማው ሕግ ትኩረት የሚያደርገው በመስጠት ላይ ነው።

ኢየሱስ ወርቃማውን ሕግ ባስተማረበት ወቅት እየተናገረ የነበረው በጥቅሉ ሰዎችን እንዴት መያዝ እንዳለብን ብቻ አይደለም፤ ከዚህም ባለፈ ጠላቶቻችንን እንኳ እንዴት ልንይዝ እንደሚገባ እየገለጸ ነበር። **(ሉቃስ 6:27-31, 35)** ከዚህ አንጻር ወርቃማው ሕግ ለሁሉም ሰው መልካም እንድናደርግ የሚያበረታታ ነው።

**ወርቃማውን ሕግ ተግባራዊ ማድረግ የምትችሉት እንዴት ነው?**

**1.አስተዋይ ሁኑ።** ለሌሎች ሰዎች ትኩረት ስጡ። ለምሳሌ፣ አንድ ሰው ከባድ ሸክም እንደያዘ ስትመለከቱ፣ ጎረቤታችሁ ታምሞ ሆስፒታል እንደገባ ስትሰሙ ወይም የሥራ ባልደረባችሁ እንደከፋው ስታስተውሉ ይሆናል። 'ለሌሎች ሰዎች ፍላጎት ትኩረት የምትሰጡ' ከሆነ ሌሎችን የሚጠቅም ነገር መናገር ወይም ማድረግ የምትችሉበት አጋጣሚ ማግኘታችሁ አይቀርም። **ፊልጵስዩስ 2:4፤**

**2.የሌሳውን ስሜት ስመጋራት ጥረት አድርጉ።** ራሳችሁን በሌሎች ቦታ ለማስቀመጥ ሞክሩ። እናንተ በዚያ ሁኔታ ውስጥ ብትሆኑ ኖሮ ምን ይሰማችሁ ነበር? **(ሮም 12:15)** የሌሎችን ስሜት ለመረዳት ጥረት ስታደርጉ እነሱን ለመርዳት መነሳሳታችሁ አይቀርም።

**3. እንደ ሁኔታው ማስተካከያ አድርጉ።** እያንዳንዱ ሰው የተለያየ እንደሆነ አትርሱ። ሌሎች እንዲደረግላቸው የሚፈልጉት ነገር እናንተ እንዲደረግላችሁ ከምትፈልጉት የተለየ ሊሆን ይችላል። በመሆኑም ልታደርጉላቸው የምትችሏቸው የተለያዩ ነገሮች ቢኖሩም ይበልጥ የሚያስፈልጋቸውን ነገር መርጣችሁ አድርጉላቸው። ፣ **ቆሮንቶስ 10:24፤**

**ሻሎም ! አሜን።**

ማህበራዊ

# የሕይወት ገጽታ

## «ስደትን በግብርና መግታት ይቻላል»

**ስምስም መንግሥቱ**

**- አርሶ አደር ወንድሙ ደስታ**

ላቤ በአንገቴና በጀርባዬ ይወርዳል ሳይሆን፤ ይንቆረቆራል ነው ሊባል የሚችለው፡፡ ምንም እንኳን አካባቢው በደን የተከበበና አረንጓዴ ቢሆንም ነፋሻማ የአየር ፀባይ የለውም፤ ይልቁንም በወበቅ ላብበላብ የሚያደርግ የአየርፀባይ ነው ያለው፡፡ ፀሐይም ሆኖ፤ ዝናብም ዘንቦ የአካባቢው ሙቀቱ ተመሳሳይ ነው፡፡ አካባቢውን አረንጓዴው በረሃ ብሎ መጥራት ሳይቀል አይቀርም ፡፡

በአብዛኞቹ የኢትዮጵያ ክፍሎች አረንጓዴ ነገር ማየት በሚናፍቅበ፤ ገበሬዎች ለከብቶቻቸው የሳር ግጦሽ አጥተው መኖ በሚቸገሩበትና ውሃ ለማጠጣት ሩቅ መንገድ ለመሄድ በሚገደዱበት፣ ሰዎችም በዛፍ ጥላ ስር ለመጠለል አካባቢ ሲመርጡ በሚስተዋልበት በዚህ በግንቦት ወር በደቡብ ምእራብ ኢትዮጵያ ሕዝቦች ክልል ግን ከእግረኛ እና ከመኪና መንገድ በስተቀር አፈር አይታይም፡፡

ለከብቶች የሚሆነው የሳር ግጦሽ ስፍራ ሳሩን በእግር ለመርገጥ ያሳሳል፡፡ የአካባቢው የመኖሪያ መንደሮች አጥር በአረንጓዴ ተክል የተከበበ ነው። ከመኖሪያና ከእርሻ ማሣ ውጪ የሚገኘውም ቦታ ቢሆን ደን የለበሰ ነው፡፡ በዚህ ወቅት የእርሻ ማሳውም በበቆሎ ተሸፍኗል፡፡ ቡና አብቃይ አካባቢ በመሆኑም የቡና ተክሉና ለቡና ጥላ የተተከሉት እንደ ዋንዛ፣ ግራር፣ ያሉ ሀገር በቀል ዛፎች፣ የቅመማ ቅመም ልማቱ ሌላው የአካባቢው መስህቦች ናቸው፡፡ የአካባቢውን አረንጓዴነትና ለምነት በቃላት ከምገልጽላችሁ፤ ዓይኔም አይቶ ካደነቀው በላይ ነው፡፡

ተፈጥሮ ለዚህ አካባቢ አድልታለች፡፡ ከአመት አመት አረንጓዴ፣ የዝናብ እጥረት የማያውቀው አካባቢ ነው፡፡ የአካባቢው አረንጓዴነትና የአየር ፀባዩ ከጋምቤላ ክልል ጋር ተቀራራቢ ሆኖ ነው ያገኘሁት፡፡ ጋምቤላ ክልል አረንጓዴው በረሃ የሚል ስያሜ ወጥቶለታል፡፡ አጎራባች በመሆናቸው ይሆን ተመሳሳይ መልክአምድር እንዲጋሩ ያደረጋቸው? ምንም እንኳን ተቀራራቢ የአየር ፀባይ ቢኖራቸውም የጋምቤላ ክልል የአየር ሙቀት መጠን ከፍ እንደሚልና አንዳንድ ሙቀቱ ከአቅማቸው በላይ የሚሆንባቸው የክልሉ ነዋሪዎችም ነፋሻ አየር ፍለጋ በደቡብ ምእራብ ኢትዮጵያ ሕዝቦች ክልል ቆይታ እንደሚያደርጉ ነው የሰማሁት፡፡

ሁሌምእርጥብሳርየማይለያቸውእንስሳትውሃ ይጠማቸዋል ተብሎ አይታሰብም፡፡ የሚግጡት ሣር ከውሃ ጋር የተቀላቀለ ነው፡፡ ገበሬውም ቢሆን መሬቱን አርሶ ለሰብል ልማት ዝግጁ ለማድረግ ብዙ ጉልበቱን አያደክምም፡፡ እንዲህ ባለው የተፈጥሮ ፀጋ በታደለ አካባቢ የሚኖር ማህበረሰብ በእንስሳት፣ በሰብል፣ በአትክልትና ፍራፍሬ፣ በቡና ልማት ከሌሎች የሀገሪቱ አካባቢዎች የተሻለ እንደሚሆን ይታሰባል፡፡ ምርታማ በሆነ አካባቢ የሚኖር ደግሞ በኢኮኖሚ ያደገ፣ ከራሱ አልፎ ለሀገር የሚበቃ ቱሩፋት የሚያስገኝ እንደሚሆን ይጠበቃል፡፡

አካባቢውን እየቃኘሁ፤ በተፈጥሮ እየተደመምኩ፤ በአእምሮዬ የተለያዩ ሃሳቦች ተመላለሱ፡፡ እንዲህ በተፈጥሮ ፀጋ ውስጥ የሚኖር ገበሬ በሀብቱ ተጠቅሞ እራሱንም ሀገሩንም በኢኮኖሚ ለማሳደግ ምን ያህል እየተጋ ይሆን? የሚል ሃሳብ ነበር ወደ አእምሮዬ የመጣው፡፡ የሳር ቤት የነበረው ገበሬ የቆርቆሮ ክዳን ያለው ቤት ገንብቶ መኖሪያውን መቀየሩን እንደ አንድ ለውጥ ልናነሳ እንችል ይሆናል፡፡ ምናልባትም ልጆቹን ማስተማሩ ሌላው ለውጥ ነው፡፡ ግን ለውጦቹ መሠረታዊ የሚባሉ ናቸው ወይ? ሲባል አሁንም ጥያቄ ማስነሳቱ አይቀርም፡፡ ገበሬው ከእለት ፍጆታ ውጪ የሚያወጣው ምርት እያመረተ አለመሆኑን አኗኗሩ



ማሳያ ነው፡፡ ክረምት ከበጋ ማምረት የሚለው የሥራ ባህል አልተቀየረም፡፡ ወቅቱን የጠበቀና በሚፈለገው ልክ የግብአት አቅርቦት አለመኖር፣ የመንገድና ሌሎች መሠረተ ልማቶች አለመሟላታቸው የገበያ ትስስር አለመፈጠሩ ሌላው ገበሬው የሚያነሳቸው ተግዳሮቶች ናቸው፡፡ ይህን ችግር ለመቅረፍና አርሶ አደሩ ክረምትን ጠብቆ ከማምረት እንዲላቀቅ፣ በውስን ሰብል ልማት ላይ ብቻ እንዳያተኩር ተጨማሪ ምርቶችንም እንዲያመርት ጅምር ሥራዎች ቢኖሩም አሁንም ችግሮቹን ለመሻገር ብዙ ሥራ ይጠይቃል፡፡ የአመለካከት ለውጥ ላይም መሥራት ይጠበቃል፡፡ በተፈጥሮ ፀጋ የታደልን ሆነን ሳለን ዘመናዊ አርሶ አደር አለመፍጠራችን ቁጭት ያሳድራል፡፡

አሁንም ገበሬው ከቀደመው የአስተራረስ ዘዴው አልተላቀቀም ዛሬም ድረስ የእሱን ድካም ሊቀንስ የሚችል ነገር አልተፈጠረም። ማልዶ ከተኛበት ተነስቶ ሲሰራ ነው የሚውለው፡፡ በዓል፣ ሰርግ፣ ሽምግልና ከሌለበት ፀአዳ ልብስ ለብሶ አይታይም፡፡ የእጁንም አፈር አይታጠብም፡፡ እርሻ ባይኖርበት የጓሮ አትክልቱን ይኮተኩታል፡፡ ከብቶቹን ያሰማራል፡፡ ለአጭር መንገድ የታክሲ ሰልፍ የለመደ የከተማ ሰው የገጠሩ ማህበረሰብ በየቀኑ በእግሩ የሚሄዳዘውን ኪሎ ሜትር ቢያውቀው በጣም አስገራሚ ነው፡፡ የገጠሩ ማህበረሰብ ሥራው ሁሉ በእንቅስቃሴ የተሞላ ነው፡፡

የገጠሩን ማህበረሰብ አኗኗር እንዲህ በሃሳቤ እያወጣሁና እያወረድኩ፤ ቁጭትም እያደረብኝ፤ አንድ ሰፊ የሣር ግጦሽ ባለው መስክ ላይ ከብቶቻቸውን አሰማርተው በርቀት ላይ ሆነው የሚጠብቁ ሰው አየሁ፡፡ ጠጋ ብዬ ሰላምታ ሰጠኋቸው፡፡ እርሳቸውም ደንገጥ ብለው በአክብሮት ለሰላምታዬ ምላሽ ሰጡኝ፡፡ ፈገግታቸውና አቀባበላቸው ልብ ይሞላል፡፡ በስም እንድንተዋወቅም ጠየኳቸው ወንድሙ ደስታ ብለው ተዋወቁኝ፡፡ የሚኖሩበት አካባቢም በደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ሕዝቦች ክልል ጊምቦ ወረዳ ሀማኒ ቀበሌ እንደሚባል ነገሩኝ፡፡

አቶ ወንድሙ ለመግባባት ቀለል ያሉና ጨዋታ የሚያውቁ ሰው ሆነው ነው ያገኘኋቸው፡፡ አቶ ወንዱሙ የትውልድ ዘመናቸውን በትክክል አያውቁትም፡፡ 60 አመት እንደሚሆናቸው ነው የገመቱት፡፡ ቀጠን ማለታቸው ይሁን፣ በቁመትም አጠር ብለው መታየታቸው የ60 አመት የእድሜ ባለፀጋ አይመስሉም፡፡ ቀልጠፍ ያሉ ናቸው፡፡ በልጅነታቸው የትምህርት እድል አግኝተው ቢማሩም ከአራተኛ ክፍል በላይ መግፋት ግን አልቻሉም፡፡ በወቅቱ የትምህርትን ጥቅም ተገንዝቦ በትምህርታቸው እንዲገፉ የሚያበረታታቸው ሰው በማጣታቸው ከአራተኛ ክፍል በላይ መዝለቅ ሳይችሉ መቅረታቸውን ይናገራሉ፡፡ በልጅነት ጊዜያቸው ከትምህርታቸው ይልቅ ከብት በመጠበቅና (በእረኝነት) ኋላም እድሜያቸው እየጎረመሰ ሲመጣ ወላጆቻቸውን የግብርና ስራ ሲያግዟቸው እንደነበር ነው ያጫወቱኝ። እርሳቸውም የቤተሰባቸውን ሥራ ተከትለው ነው ዛሬም ድረስ ግብርናውን መተዳደሪያቸው ያደረጉት።

አቶ ወንድሙ ለአጭር ጊዜም ቢሆን በውትድርና ሙያ ውስጥ እንደነበሩም አጫውተውኛል፡፡ ኢትዮጵያ በወታደራዊ የደርግ ሥርዓት አገዛዝ ውስጥ በነበረችበት ወቅት ከመንግሥት የእናት ሀገር ጥሪ ቀርቦላቸው ግዳጃቸውን ለመወጣት ወደ ሰሜን ኢትዮጵያ ዘምተዋል፡፡ በወቅቱ ጥሪውን መቀበል ግዴታ ስለነበር ሁሉም ከየአካባቢው የሰው ኃይል ይልካል፡፡ እርሳቸውም የዚህ አጋጣሚ ተካፋይ በመሆን አሰብ ላይ ዘምተዋል። እሳቸው ከዘመቱ አንድ አመት ተኩል በኋላ ግን የደርግ መንግሥት ተሸንፎ ኢህአዴግ ሀገሪቱን ሲቆጣጠርና የቀድሞ ሰራዊት ሲበተን እርሳቸውም ወደአካባቢያቸው ተመለሱ፡፡

“...ለአጭር ጊዜም ቢሆን የጦርነትን አስከፊነት አይቻለሁ፡፡ የሰው ህይወት የሚቀጥፍ የሀገር ሀብትን የሚጎዳና ወደኋላም የሚያስቀር መሆኑን ተገንዝቤያለሁ” ይላሉ፡፡

ጦርነቱ ከተጠናቀቀ በኋላም ሠራዊቱ ላይ የደረሰውን ጉዳትና በየአካባቢው የነበረው ማህበረሰብ ለስደት ሲዳረግ የነበረውን አስከፊ ሁኔታ አስታውሰዋለሁ የሚሉት አቶ ወንድሙ፤ በጉዞ ላይ ብዙዎች በረሀብና በውሃ ጥም ተንገላትተዋል፡፡ ጥቂት የማይባሉ ዜጎችም ሞተዋል፡፡ እርሳቸውም ወደ ጅቡቲ ተሰደው ከብዙ ውጣ ውረድ በኋላ ተንገላተው ወደ ቀያቸው መመለሳቸውንም አይረሱትም ፡፡

አሁን ላይ ኢትዮጵያን ስለገጠማት የእርስ በእርስ ጦርነት ሁኔታ እንደተናገሩት፤ ጦርነት ያደረሰው ጉዳትና አስከፊነት ካለፈው ትምህርት መውሰድ ይገባል፡፡ ኢትዮጵያ ሰፊ መሬት ፣ የሚሰራ የሰው ኃይል ያላት በሀብት ላይ የምትገኝ ሀገር ናት፡፡ ዜጎች ተስማምተው በጋራ ሆነው ለሀገራቸው እድገት ሊተጉ እንጂ ለውድቀት መነሳት የለባቸውም ይላሉ፡፡ የውጭ ጠላት ሲመጣ በጋራ መክቶ ለመመለስ መነሳት እንጂ ለእርስ በእርስ ጦርነት ጦር መዞ መነሳት አይገባም። ካሉ በኋላ አሁን ላይ በሀገራዊ ምክክር አለመግባባቶችን ለመፍታት በመንግሥት በኩል የተጀመረውን ጥረትም ይደግፋሉ፡፡ አለመግባባቶች በውይይትና በመነጋገር መፈታት አለበት ይላሉ፡፡ መንግሥት ሰላም እንዲሰፍን የጀመረውን በምክክር የመፍታት ጥረት እንዲቀጥል የሁሉም ያላሰለሰ ጥረት ያስፈልጋል ብለዋል፡፡

### ስለአካባቢያቸው

ስለ አርሶአደሩ የለውጥ ሁኔታ የተሰማኝን ስሜት ስለ አካባቢያቸው፣ ስለሥራቸው፣ ስለቤተሰባቸው፣ አንስተንም ተጨዋወትን። እርሳቸው እንዳሉት፤ የአካባቢው መሬት ጤፍ፣ ጥራጥሬ፣ ቡና፣ እንሰት፣ የተለያዩ ፍራፍሬዎችና አትክልት፣ ሁሉንም የሰብል አይነቶች ያመርታል። የአካባቢው የአየር ፀባይ ለሰብል ልማት የተመቸ ነው፡፡ ዝናብ የማይዘንብባቸው ጊዜያቶች ጥቂት ወቅቶች ብቻ ናቸው፡፡ በተጨማሪም በአካባቢያቸው ሸካ የሚባል ወንዝ በመኖሩ በመስኖ ማልማት ይቻላል፡፡ በተለይም በመስኖ እንደ ድንች፣ ጥቅል ጎመን፣ ቀይስር፣ ካሮት፣ ሽንኩርት፣ የመሳሰሉ አትክልቶች፣ ፍራፍሬም ማልማት ይቻላል፡፡ ይሁን እንጂ በአካባቢው ላይ የመስኖ ልማት ባለመታወቁ ወንዙ ለመስኖ ጥቅም መዋል የጀመረው ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ነው፡፡ አሁን ላይ ገበሬው ጥቅሙን እየተገነዘበ በመምጣቱ የተለያዩ አትክልትና ፍራፍሬዎችን እያለማበት ይገኛል፡፡

ስለሥራቸው ደግሞ እንዲህ አጫውተውኛል። የሚተዳደሩት በግብርና ሥራ ነው፡፡ እርሳቸው እንዳሉት መሬታቸው ሰፊ አይደለም፡፡ አንድ ሄክታር መሬት ነው ያላቸው፡፡ አንድ ጥማድ በሚሆነው መሬት ላይ የቡና ተክል ያለማሉ፡፡ በቀሪው ላይ ደግሞ በቆሎ፣ ሙዝ፣ ጎን ለጎን ደግሞ እንሰት በተጨማሪ ያለማሉ፡፡ በአንድ ጥማድ መሬት ላይ ከሚያለሙት ቡና በአመት አምስት ኩንታል ያገኛሉ፡፡ በቆሎም በአመት እስከ ስድስት ኩንታል የሚሆን ምርት ይሰበስባሉ፡፡ ከሙዝ ምርት ደግሞ ለገበያ አቅርበው ወደ ስድስት ሺ ብር ገቢ ያገኛሉ፡፡ የእንሰት ምርቱ ደግሞ ለቤት ቀለብ ይውላል፡፡

**ወደ ገጽ 7 ዞሯል**

ማህበራዊ

# የሕይወት ገጽታ

## ስደትን በግብርና...

ከገጽ 6 የዞረ

ስለአርሶአደሩ የለውጥ ሁኔታ የተሰማኝን ስሜት በተመለከተም አቶ ወንድሙ፤ በእርሳቸው በኩል ከፍተኛ የሆነ ለውጥ ላለማምጣታቸው ምክንያት ነው ብለው የነገሩኝ፤ በቂ የሆነ የእርሻ መሬት አለመኖር ነው፡፡ እንደ አጠቃላይ ግን ከተለመደው የግብርና አሰራር ውስጥ አለመውጣት ያመጣው ችግር እንደሆነ ያምናሉ፡፡


አካባቢው ለም ቢሆንና መሬትም ቢኖር አጠቃቀሙን ማወቅ ካልተቻለ ተጠቃሚ መሆን አይቻልም የሚሉት አቶ ወንድሙ፤ «በግሌ የምለው አጠቃቀሙን አላወቅንበትም፡፡ ሰው ለም መሬት በመያዝ ለችግር እጋለጣለሁ ብሎ አላሰበም፡፡ ግን ካላለሙ ለችግር መጋለጥ ይኖራል» ሲሉ ይገልጻሉ። እርሳቸው እንዳሉት ከወንዝ ጠልፎ በመስኖ መጠቀም፣ ኩታገጠም የአስተራረስ ዘዴ መጠቀም በአካባቢው የተለመደ የግብርና ሥራ አይደለም፡፡ ምርታማ ለመሆን ዘመኑ የሚጠይቀውን የግብርና ሥራ መከተል እንደሚያስፈልግ ግንዛቤ የተገኘው ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ነው፡፡

የመስኖ ልማቱ ሥራ የተጀመረውም ሆነ ጥቅሙ የታወቀው ከአራትና አምስት አመታት ወዲህ ነው፡፡ ግብርናውን ለማዘመንም በትምህርት አለመታገዝም ሌላው ክፍተት ነው፡፡ የትምህርቱን አስፈላጊነትም ሲያስረዱ፤ በእውቀት ላይ የተመሰረተ የግብርና ሥራ ቢሰራ ለአካባቢው የአየር ፀባይና የመሬት ሁኔታ ተስማሚ የሆነ ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ ያላቸው ሰብልና ሌሎችንም ለይቶ በማምረት ተጠቃሚ መሆን የሚቻልበት ዕድል ይፈጠር ነበር።

ይህ ባለመሆኑ ግብርናው ከኋላቀር የአስተራረስ ዘዴ ሳይላቀቅ ዘመን መሻገሩን ይገልጻሉ፡፡ ገበሬው ተጨማሪ የገቢ ማስገኛ ሥራዎችን ባለመሥራቱ ከእጅ ወደ አፍ የሆነ ኑሮ ላይ እድሜውን እንዲያሳልፍ መገደዱን ያስረዳሉ፡፡ እርሳቸው በዚህ ሁኔታ ውስጥ ቢያልፉም ለተተኪው ትውልድ ግን ተስፋ ሰጪ የሆነ ነገር መኖሩን መታዘባቸውንና እያዩ እንደሆነም ይናገራሉ፡፡ በእርሳቸው እድሜ ያላዩት ከቅርብ ጊዜ ወዲህ የተጀመረው ወንዝ ጠልፎ በመስኖ ማልማት፣ በግብርና ባለሙያዎች የተለያየ እገዛ ማድረግ መጀመሩ፣ ግብርናውን ለማሳደግ የሚያስችሉ የተለያዩ ሥልጠናዎች እየተሰጡ መሆናቸውን ለአብነት አንስተዋል፡፡ ወደፊት የመሬት አጠቃቀም ላይ ያለው የእውቀት ማነስም በትምህርት እየዳበረ ሲሄድ በአነስተኛ መሬት የተለያዩ ምርቶችን በማምረት ምርታማነትን ማሳደግ የሚቻልበት ዘዴ ሊኖር እንደሚችልም ያላቸውን ተስፋ ነው የተናገሩት፡፡ የግብርናው ሥራ ዘምኖ ምርታማነት ቢያድግ የገጠሩ ማህበረሰብ ከከተማ ኑሮ ባልተናነሰ ሊኖር ይችላል ይላሉ፡፡ ዛሬ ከተማ ፍለጋ ገጠሩን ለቀው የሚሄዱ ሁሉ በአካባቢያቸው ላይ የተሻለ ኑሮ መኖር ከቻሉ አካባቢያቸውን ለቀው ለመሄድ እንደማይነሳሱ ነው ያስረዱት፡፡

ስለአካባቢያቸውም እንደተናገሩት፤ አካባቢው በተፈጥሮ ፀጋ የታደለ መሆኑ ለሰው ልጅ ጤና ተስማሚ ነው፡፡ በግላቸው አካባቢያቸው የመንፈስ እርካታ ይሰጣቸዋል፡፡ በንጹህ አየር ላይ ሆነው ነው የግብርና ሥራቸውን የሚያከናውኑት። ለከብቶቻቸውም መኖ አይቸገሩም፡፡ ሰው ባለው መደሰት አለበት የሚል እምነት አላቸው፡ ፡ የሚያስፈልገው የሥራ ተነሳሽነት ብቻ ነው ይላሉ። መሬቱም የሚሰራ እጅ እየጠበቀ እንደሆነ ነው የገለጹት፡፡ ሁሉንም አይነት ምርት ማምረት ከተቻለ ውጤታማ መሆን እንደሚቻል፣ ምርት ካለ ደግሞ ሸጦና ለውጦ የከተማው ማህበረሰብ እንደሚኖረው አይነት ኖሮ መኖር እንደሚቻል ያስረዳሉ፡፡

በአካባቢያቸው የመብራት አገልግሎት



የሚቀረው ቢሆንም አንዳንዶች አካባቢዎች ላይ አገልግሎቱ በመኖሩ ወደፊት ይሟላል የሚል ተስፋ አላቸው። በተለይም የከተማ ኑሮ ፍለጋ አካባቢያቸውን ለቀው ወደተለያዩ የሀገሪቱ ክፍሎች የሚሄዱ ወጣቶች በአካባቢያቸው ላይ ሰርተው ለመለወጥ ጥረት ቢያደርጉ ከከተማ ለማግኘት የሚፈልጉትን ነገር ሁሉ ወደአካባቢያቸው ማምጣት እንደሚችሉ አቶ ወንድሙ ምክራቸውን ለግሰዋል፡፡

ለውጥ በሰው ልጅ እጅ ላይ እንደሆነም ይናገራሉ፡፡ ወጣቱ ትውልድ ወደኋላ የቀረውን የግብርና ሥራ በማሻሻልና በማዘመን ምርታማነትን ማሳደግ መቻል አለበት የሚል እምነት አላቸው፡፡ ግብርናውን ለማዘመን እርሳቸው ካሳለፉት የግብርና ሥራ የተለያዩ እድሎች መኖራቸውንና ወጣቱ ይሄንን እድል ተጠቅሞ እራሱንና ሀገሩን ማሳደግ እንዳለበትም መልእክታቸውን አስተላልፈዋል፡፡ ከተማም ቢሆን በቀላሉ የሚኖርበት፣ የኑሮ ውጣ ውረድ የሌለበት እንዳልሆነ ወጣቱ ሊገነዘብ ይገባል ብለዋል፡፡

### ስለገበሬው ሁኔታ

ገበሬው የአመት ጉርሱና ልብሱ የግብርናው ሥራ ላይ የተመሰረተ በመሆኑ ገንዘብ የለውም የሚለው ተደጋግሞ ይነሳል፡፡ እውነት ገበሬው ገንዘብ የለውም? አቶ ወንድሙ፤ ገበሬው ደሀ አይደለም ይላሉ፡፡ ተቀጥረውም ይሁን በተለያየ መንገድ ገንዘብ ያላቸው ሰዎች አሉ ፡፡ ገበሬው ደግሞ ሀብቱ ያለው ጎተራ ውስጥ ነው፡፡ ከጎተራው አውጥቶ ወደብር ይለውጣል፡፡ በእርሳቸው እምነት በግብርና የሥራ ወቅት ወገቡን ጠበቅ አድርጎ ያልሰራ ሰው ብቻ ነው ብር የሚያጣው፡፡ በተለይ ገበሬ ጠንክሮ ከሰራ መንግሥትም የሚያስፈልጉትን የግብርና ግብአቶች በወቅቱ ካቀረበ፣ የተለያዩ የሰብል በሽታዎች ሲያጋጥሙም ፈጥኖ መከላከል ከተቻለና ምርታማነት ካደገ እንደገበሬ ሀብታም የለም ነው የምለው ሲሉም አንስተዋል፡፡

### ስለትዳራቸው

አቶ ወንድሙ ስለባለቤታቸውና የትዳራቸው ሁኔታ እንደነገሩኝ፤ ባለቤታቸው ወይዘሮ አዛለች ማሞ ይባላሉ፡፡ በትዳር ከ30 አመት በላይ አብረው ኖረዋል።

"... አምስት ልጆች የወለደችልኝ ባለቤቴ ናት፡፡ እወዳታለሁ፡፡ አከብራታለሁ፡፡ እርስዋም እንደኔው እንደሆነች ነው የሚሰማኝ፡፡ ኑሮአችንም እንደአቅማችን እንደቤታችን ነው፡፡ በመካከላችን መጥፎ ነገር ተፈጥሮ ከቤት ወጥታ የሄደችበት ጊዜ የለም፡፡ እርስዋ የቤቱን ሥራ እኔ ደግሞ የግብርናውን ስራ እየተወጣን በፍቅር አብረን እየኖርን ነው፡፡ እንደውም ልጆቼ ትዳራቸው እንደ እኔና ባለቤቴ እንዲሆንላቸው ነው የምመኘው" ፡፡

መቼም እንኳን ሰውና ሰው እግርና እግርም ይጋጫል ይባላል፡፡ ግጭት መኖሩ አይቀርም፡፡ አምሽቶና ጎንጨት ብሎ ቤት መግባት የአባወራ ወግ ተደርጎም ስለሚወሰድ እዚህ ላይም አቶ ወንድሙ፤ ብዙ ጊዜ በመካከላቸው ግጭት የሚነሳው ከልጆች ጥፋት ጋር በተያያዘ እንደሆነና ግጭቱም ለኑሮ መሆኑን ነው የነገሩኝ፡፡ ባለቤታቸው ከቤት ሥራ በተጨማሪ በግብርና ሥራ አረም በማረም፣ በመጎልጎል እንደሚያግዟቸው፣ በጋራ እንደሚሰሩና ለፀብ ጊዜ እንደሌላቸው ነው ያጫወቱኝ፡፡

በገጠር ሴቶች የሥራ ጫና እንዳለባቸው፣ ወንዱ ደግሞ መጠጥ ጎንጨት ብሎ የሚገባ ሽምግልና እውላለሁ እያለ የተለያዩ ምክንያቶችን በመስጠት ሥራ እንደማያግዝ ስለሚነገረውም አቶ ወንድሙ የሚባለው ነገር እርሳቸውን እንደማይገልጽ ነው የነገሩኝ፡፡ በጋራ ሆነው በኑሮአቸው ለውጥ ለማምጣት እንጂ ባለቤታቸው ብቻ እንዲወጡ የሚያሳድሩት ጫና አለመኖሩን ነው ያስረዱት። በመጠጥ በኩል ያላቸውንም ልምድ ሲናገሩ፤ ሰክረው ቤተሰባቸውን ለሚያውኩ አንዳንዶች ያዝናሉ፡፡ ሁሉ ነገር ልክ አለው ብለው ያምናሉ። በመሆኑም በመጠኑ አካባቢ ላይ የሚገኙ የባህል መጠጦችን አልፎ አልፎ ይጠቀማሉ፡፡ በባህሪያቸው አለኝ ብለው ማባከን፣ ተቸግረውም መታየት አይፈልጉም፡፡ ሁሉን ነገር በልክ የሚለውን ነው የሚመርጡት፡፡

### ስለልጆቻቸው የአስተዳደግ ሁኔታ

አቶ ወንድሙ፤ አምስት ልጆች አሏቸው፡፡ ልጆቻቸውንም ያስተምራሉ፡፡ 12ኛ፣ 10ኛ፣ 9ኛ፣ 6ኛ ክፍል የደረሱ ናቸው፡፡ 10ኛ እና 12ኛ ክፍል የደረሱት ጥሩ ውጤት ባለማምጣታቸው ካሉበት ክፍል በላይ መግፋት አልቻሉም፡፡ ልጆቻቸው በትምህርታቸው ውጤታማ ላለመሆናቸው ልጆቹ ብቻ ሊወቀሱ አይገባም ይላሉ፡፡ በትምህርታቸው እንዲጠነክሩ ስለትምህርታቸው ክትትል በማድረግም ሆነ የሚያስፈልጋቸውን ነገር እንዳላሟሉላቸውና የእርሳቸውም ድጋፍ እንዳነሳቸው ይገልጻሉ፡፡ የአቅም ማነስ ክፍተት እንደሆነም ይገነዘባሉ፡፡

በግብርና ሥራ የልጆች እገዛ እንዴት እንደሆነም ጠይቄያቸው፤ «ልጆችን እንዳሳደግሻቸው ነው፡፡ ሥራ እያሳየሽና እየመራሻቸው ከሆነ ይከተሉሻል። እኔም በትምህርታቸው ውጤታማ እንዲሆኑ ተገቢውን ድጋፍ ባላደርግላቸውም በግብርናው ላይ ችሎታ እንዲኖራቸው፣ ቤተሰብንም ማገዝ እንዳለባቸው የምችለውን ሁሉ አድርጌያለሁ። በሥራ ያግዙኛል» በማለት ምላሽ ሰጥተውኛል። ሁሉት ልጆቻቸውን ኩለው በመዳር ለጎጆ አብቅተዋል፡፡ የልጅ ልጆችም ለማየት በቅተዋል። ልጆች እራሳቸውን እንዲችሉ ወላጅ ይጨነቃል የሚሉት አቶ ወንድሙ፤ ለራሱና ለሀገር የሚጠቅም ዜጋ ማፍራት የወላጅ ድርሻ ከፍተኛ እንደሆነም ያምናሉ፡፡

### ስለኑሮአቸው ሁኔታ

የገጠሩ ማህበረሰብ የኤሌክትሪክ ኃይል አገልግሎት፣ የመንገድና ሌሎች የመሠረተ ልማት እጥረቶች እንዳሉበት ያስታውሳሉ፡፡ እርሳቸው እንዳሉት ላምባ፣ ኩራዝ ነበር ለቤታቸው መብራት የሚጠቀሙት፡፡ ዛሬ በየቤቱ የኤሌክትሪክ ኃይል እንዲዳረስ በመንግሥት በኩል ጥረት ተደርጎ አንዳንድ አካባቢዎች ተጠቃሚ መሆን ቢጀምሩም የሚቀሩ አካባቢዎች እንዳሉ ያስታውሳሉ። በተለይም የገጠሩን ማህበረሰብ በጣም ተጠቃሚ እያደረገ ያለው በፀሐይ ኃይል የሚሰራው የመብራት አገልግሎት የብዙዎችን የኃይል አቅርቦት ችግር እየፈታ እንደሆነና እርሳቸውም አንዱ ተጠቃሚ መሆናቸውን ይገልጻሉ፡፡ ጥቅሙና አስፈላጊነቱ እያደገ መምጣቱንም ተናግረዋል። በዚህ አጋጣሚም መንግሥት ተደራሽነቱ ላይ አጠንክሮ እንዲሰራ ጠይቀዋል፡፡

ከዚህ አንጻርም የቀድሞ ኑሮቸውን አሁን ላይ ከሚኖሩት ጋር በማነጻጸር ልዩነት እንዳለው ይናገራሉ፡፡ እርሳቸው ግብርና በጀመሩበት ዘመን የግብርና ሥራቸው በእውቀት ታግዞ ቢሆን በኑሮቸው ለውጥ ያመጡ እንደነበር፣ ያም ሆኖ ግን ከቀድሞ የተሻለ የኑሮ ደረጃ ላይ እንደሚገኙ ነው የገለጹት፡፡ «እድሜዬ በገፋ ጊዜ የመጣው ለውጥ ጥሩ እድል ነው ብዬ ነው የማስበው» ሲሉም ተናግረዋል፡፡ እርሳቸው እንዳሉት አካባቢያቸው ላይ በቆርቆሮ የተሰራ ቤት አልነበረም፡፡ የግብርና ሥራውም ቢሆን አልተስፋፋም፡፡ ዛሬ ልማቱ ተስፋፍቷል፡፡ እኔ የቀደመውንም የአሁኑንም ልዩነቱን ስለማውቅ የተሻለው የትኛው እንደሆነ ለመናገር እችላለሁ፡፡ የአሁኑ ትውልድ ግን ያለፈውን ስለማያውቅ ችግሩ ላይገባው ይችላል። ከእኛ ግን በታሪክ መማር ስለሚችል አሁንም ለተሻለ ነገር መነሳት አለበት ብዬ ነው የማምነው በማለት ያስረዳሉ፡፡

በግላቸው ለልጆቻቸውም ለአካባቢያቸው ልጆች ያሳለፉትን ጊዜ ያጫውቷቸዋል፡፡ በቀን ሥራ በሰአት በአንድ ብርና ባነሰ ዋጋ እየተከፈላቸው ኑሮን ለማሸነፍ ያደርጉት የነበረውን ጥረት ሁሉ እንደሚነግሯቸውና እነርሱ ግን ከእርሳቸው በተሻለ ኑሮ እንዲኖሩ በተሰማሩበት የሥራ መስክ ጠንክረው እንዲሰሩ፣ በትምህርታቸውም ውጤታማ እንዲሆኑ፣ የወጣትነት ጊዜያቸውን በከንቱ እንዳ ያሳልፉ ምክራቸውን እንደሚለግሷቸው ነው የገለጹት፡፡

ኢኮኖሚ

# ባህልና ቱሪዝም

## ጥናትና ምርምር - ለዘላቂ ቱሪዝም ልማት

**ሰሚራ በርሀ**

ኢትዮጵያ ለቱሪዝም ሥራ ሊውሉ የሚችሉ የአያሌ ቅርሶች፣ ድንቅ የተፈጥሮ ሀብቶች፣ ባህሎች፣ ፓርኮች፣ የዱር እንስሳትና የመሳሰሉት ሀብቶች ባለጸጋ ናት። ከእነዚህ የቱሪዝም ሀብቶች መካከልም ከ16 የማያንሱት በዓለም ቅርስነት በዩኒስኮ ተመዝግበዋል።

እነዚህን የቱሪዝም ሀብቶች ለመጎብኘትም በርካታ የውጭ ቱሪስቶች ወደ ሀገሪቱ ይመጣሉ። ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ደግሞ የሀገር ውስጥ ቱሪስቶችም እነዚህን የቱሪስት መዳረሻዎች በስፋት መጎብኘት ጀምረዋል።

ሀገሪቱ በቱሪዝም ዘርፍ ያላትን ይህን እምቅ አቅም ከግምት ውስጥ በማስገባት መንግሥት ዘርፉን በቀጣይ የሀገር ምጣኔ ሀብት ምሰሶ አድርጎ ከያዛቸው አምስት ግዙፍ ዘርፎች መካከል እንዲካተት አርጎታል። መንግሥት ይህን በማድረግ ብቻም አላቆመም። ሀገሪቱ በውጭም በሀገር ውስጥ ጎብኚዎች ሊጎበኙ የሚችሉ በርካታ የቱሪስት መዳረሻዎች ቢኖሩም፣ ቱሪስቶችን ይስባሉ፤ ቆይታቸውን ያረዝማሉ ያላቸውን በርካታ አዳዲስ የቱሪስት መደረሻዎችን በአዲስ አበባና በተለያዩ ክልሎች አልምቶ ወደ ሥራ አስገብቷል፤ እያለማም ይገኛል።

የቱሪስት መዳረሻ ልማቶቹ የሚያስፈልጋቸውን የሠለጠነ የሰው ሃይል ለማሟላት በቱሪዝም ማሠልጠኛ ኢንስቲትዩት ከሚሰጡ ሥልጠናዎች በተጨማሪ በዩኒቨርሲቲዎች፣ በቴክኒክና ሙያ ሥልጠና ተቋማትም በሰው ሃይል ልማቱ ላይ በትኩረት እየተሠራ ነው።

የኢትዮጵያ ቱሪዝም ማሠልጠኛ ኢንስቲትዩት በመንግሥት ከተሰጡት ተልእኮዎች መካከል ትምህርትና ሥልጠና ዋናውና አንዱ ነው። ሌላው የጥናትና እና ምርምር፣ የማማከር ሥራ እና የማህበረሰብ አቀፍ አገልግሎት ነው። በትምህርትና ሥልጠና ሥራው ተማሪዎችን በመደበኛነት እየተቀበለ የሚያስተምር ሲሆን፣ በዘርፉ ሥልጠናዎችን ይሰጣል፤ ምርምርና ጥናቶችን እያካሄደ በመንግሥት የተሰጡትን ተልኮዎች እየፈጸመ ይገኛል።

ኢንስቲትዩቱ በየአመቱ የጥናት እና ምርምር ጉባኤ ያካሂዳል። ዘንድሮም በቅርቡ ለ13ተኛ ጊዜ ይሄው ጉባዔ ተካሂዷል። ጉባዔው በተለያዩ ምሁራን ጥናት እና ዝግጅት የተደረገባቸው አራት የምርምር ውጤቶች ቀርበውበታል።

በጉባዔው ላይ እንደተጠቆመው፤ ጥናትና ምርምር ውጤቶች ለእንድ ሀገርና ማህበረሰብ ችግሮች ሁነኛ መፍትሄ ለመስጠት ያስችላሉ፤ የትምህርትና ሥልጠና ሥርዓትን ለማሻሻልም ጉልህ ሚና አላቸው።

‹‹ቀጣይነት ያለው ቱሪዝም እና ሆስፒታሊቲን መገንባት›› በሚል መሪ ቃል የተካሄደው ይህ ጉባዔም የዘላቂ ቱሪዝም ልማት ግንባታ ጉዳይ ሲታሰብ በዘርፉ የሚደረጉ ምርምሮች ሚና የጎላ መሆኑ ተጠቁሞበታል።

በጉባዔው ላይ የተገኙት የሥራ እና ክህሎት ሚኒስትር ዴኤታ ዶክተር ተሻለ በሬቻ እንደገለጹት፤ የምርምር ሥራን ባህል ማድረግ ቴክኖሎጂንና የሥራ እድልን ለመፍጠር ያግዛል። የምርምር ሥራ ለአንድ ሰሞን ተደርጎ የሚተው ሳይሆን፣ ተልዕኮን በላቀ ደረጃ ለማከናወን የሚረዳ መሆን ይኖርበታል።

የቱሪዝም ማሠልጠኛ ኢንስቲትዩት ምክትል ዋና ዳይሬክተር አቶ ይታሰብ ስዩም እንዳሉት፤ ኢንስቲትዩቱ በቱሪዝም ዘርፍ በዋናነት ሥልጠናዎች ፣ የጥናትና ምርምርና እንዲሁም የቴክኖሎጂ ሽግግር ሥራዎች ይሠራሉ። የጥናትና ምርምር ተቋሙ በየአመቱ በሚያዘጋጀው መድረክ ጥናቶች የሚቀርቡ ሲሆን፣ ዘንድሮም በዚህ መድረክ ላይ አራት ትናቶች ተመርጠው ቀርበዋል።

ኢንስቲትዩቱ በቱሪዝም ዘርፉ የሚያስፈልገውን የሰው ሃይል እያሠለጠነ ወደ ዘርፉ እንደሚያሠማራ ጠቅሰው፣ በአሁኑ ሰዓትም በኢንስቲትዩቱ እየተሠራ ያለና በመጠናቀቅ ላይ የሚገኝ ጥናት መኖሩን ምክትል ዳይሬክተሩ አስታውቀዋል። ይህ ጥናት ዘርፉ ምን ያህል የሰው ሃይል ይፈልጋል? ከማሠልጠኛ ተቋማት ምን ይጠበቃል? በሚል ያለውን ክፍተት ለመሙላት የሚያስችል በመላው ሀገሪቱ የተደረገ ጥናት ነው ብለዋል።

በጥናት እና ምርምር ጉባኤዔው የቅርስ ጥበቃ እና አስተዳደር ፣ ቅርሶች በሚገኙባቸው አካባቢዎች ላይ የሚገኙ የማህበረሰብ ክፍሎች ያላቸው ተጠቃሚነት ፣ ለቅርሶች በሚደረግ ጥበቃ የማህበረሰብ ተሳትፎ አስፈላጊነት ፣ ዘመኑ የሚጠይቀውን የቱሪዝም ዘርፉን የሠለጠነ የሰው ሃይል ማቅረብ ፣ የቱሪዝም ሀብትን በሚገባ ማስተዋወቅ እንዲሁም ሀገር በቀል እውቀቶችን በሥልጠና ሥርዓት ውስጥ ማካተት የሚሉ ጉዳዮች በጉባዔው ላይ ጥናታቸውን ያቀረቡ ምሁራን በዋናነት ያነሷቸው ሃሳቦች ናቸው ። ዘላቂነት ያለው ቱሪዝምን እንዴት መገንባት ይቻላል ፣ የባለድርሻ አካላት ሚና ምን መምሰል አለበት በሚል የተዘጋጁ ጥናቶች በቀረቡበት በዚህ መድረክ ላይ ፣ በኢንስቲትዩቱ የተጋበዙ እንግዶች እና የዘርፉ ባለሙያዎች ተገኝተዋል።

> **እየተጠናቀቀ ባለው 2016 በጀት ዓመት ኢንስቲትዩቱ የስምንት ክልሎችን ባህላዊ ምግቦች ለማጥናት አቅዶ ባለፉት ዘጠኝ ወራት የአምስቱን ክልሎች አጥንቷል፡፡ ጥናት የተደረገባቸው ምግቦችም የስልጤ ፣ ሀዲያ ፣ ወላይታና ኮንሶ ባህላዊ ምግቦች ናቸው**

ኢትዮጵያ በተባበሩት መንግሥታት የትምህርት ፣ የሳይንስ እና የባህል ድርጅት /ዩኔስኮ/ የማይዳሰሱ እና የሚዳሰሱ ቅርሶች በሚል 11 የሚሆኑ ቅርሶችን አስመዝግባለች። የእነዚህ ቅርሶች መመዝገብ በዓለም አቀፍ ደረጃ የሚገኙ ጎብኚዎችን ከእስከ አሁኑም በላቀ መልኩ ወደ ሀገሪቱ እንዲመጡ ምቹ ሁኔታን ይፈጥራል። ከቅርሶች ጋር ተያይዞ የተካሄደው ጥናትና ምርምር ያለው ፋይዳም ከፍተኛ ነው።

በሀገራችን የቱሪዝም ኢንዱስትሪ ውስጥ ለሀገር ውስጥም ሆነ የሌላ ሀገር ጎብኚዎች ምርጫቸው የሚያደርጓቸው በዓመት ቀላል የማይባል የጎብኚ ቁጥርን የሚያስተናግዱ የቱሪስት መዳረሻ የሆኑ ቅርሶች እንዳሉ የተጠቀሰ ሲሆን፣ ረጅም ዓመት ያስቆጠረ ቅርስ ባለበት ሁኔታ ጠብቆ ማቆየት እና ማስተዳደር እንደሚገባ ተመልክቷል።

ቅርስን ጠብቆ በማቆየት እና ማስተዳደር በኩል ሃላፊነቱ ቅርስን እንዲያስተዳድር ሃላፊነት የተሰጠው አካል መሆን እንደሌለበት የተገለጸ ሲሆን፣ ቅርሱ የሚገኝበት አካባቢ ማህበረሰብ ጨምሮ የአካባቢው አስተዳደር ሃላፊነት እንዳለባቸው በመድረኩ በቀረበው ጥናትም ታይቷል። በአፍሪካም ሆነ በሀገራችን ቅርሶችን የማስተዳደር እና ጠብቆ የማቆየት ክፍተት በተቋማት ላይ እንደሚታይ የተገለጸ ሲሆን፣ በዚህም ምክንያት ቅርሶች በአንድም በሌላም መንገድ ጉዳት እየደረሰባቸው መሆኑ ተጠቁሟል።

ቅርሶች በምን ምክንያት ሊጎዱ ይችላሉ በሚል ጥያቄዎች ተያይዘው ተነስተዋል። ለእዚህ ከተሰጡ ምላሾች መካከልም የሕዝብ ቁጥር መጨመርን ተከትሎ በህብረተሰቡ ዘንድ እየጨመረ የመጣው የመሠረተ ልማት ፍላጎት፣ በከተማ ግንባታ ወቅት የሚያስፈልጉ አገልግሎቶች መጨመር የሚሉት ይጠቀሳሉ። እነዚህን አገልግሎቶች የቱሪስት መዳረሻ ናቸው በሚባሉ ሥፍራዎች ውስጥ ማሟላት አጠያያቂ እንዳልሆነም ተጠቁሞ፣ ሥራዎቹ በቅርሶች ላይ ጉዳት በማያስከትል መልኩ መከናወን እንዳለባቸውም ተመልክቷል።

ሌላኛው ቅርሱን ለመጠበቅእና ለማቆየት የሚደረጉ ጥንቃቄዎችና የሚካሄዱ ጥገናዎች የአካባቢው ማህበረሰብ ያለውን ሀገር በቀል እውቀት መጠቀምን ታሳቢ ያደረገ እንዲሆን የማድረግ አስፈላጊነትም ተጠቁሟል፤ ይህ እንዲሆን የሚመለከተው አካል ፈቃድ አስፈላጊ ነው የሚል ሃሳብ ተነስቷል።

በመድረኩ እንደተጠቆመው፤ ህብረተሰቡ በእቅራቢያው የሚገኘውን ቅርስ ፣ ከባቢያዊ ሁኔታ ለመረዳት የሚያስችል እና በራሱ ቅርሱን የሚጠብቅበት ዘመናትን የተሻገረ እውቀት አለው። ይህን አቅም በሚገባ ለመጠቀም ባለድርሻው አካል ቅርሱን ለመጠበቅ በሚያደርገው እንቅስቃሴ ውስጥ የህብረተሰቡን የባለቤትነት ስሜት በመረዳት ለማህበረሰብ ተሳትፎ ዋጋ መስጠት ይገባዋል።

ህብረተሰብ ተኮር የቱሪዝም ልማት ሌላው በመድረኩ የተነሳ ርእሰ ጉዳይ ነው። ይህ አይነቱ የቱሪዝም ልማት በተለይ ቅርስ ያለበት አካባቢ የሚኖር ህብረተሰብ ቅርሱን እየጠበቀ እና እየተንከባከበ ከቅርሱ ማግኘት የሚገባውን ጥቅም እንዲያገኝ ማድረግ የሚያስችል አሠራር ነው። የቱሪዝም ልማት የአካባቢውን ማህበረሰብ ከቱሪዝም ተጠቃሚ የሚያደርግ እንጂ አሉታዊ ተጽዕኖ የሚያሳድር መሆን የለበትም።

ሌላው በመድረኩ የቀረበው ጥናት በሀገር በቀል እውቀቶች ላይ ያተኮረው ነው። ኢትዮጵያ በተለያዩ ጉዳዮች ላይ ሀገር በቀል ሀብት በብዛት ያላት ሀገር እንደመሆኗ በቱሪዝሙም ዘርፍም እንዲሁ የሀገር በቀል አውቀቶች ባለጸጋ ናት። ይህን ሀብት በመጠቀም በኩል ግን ብዙም አልተሠራም።

በሀገር በቀል እውቀቶች ላይ የተካሄደው ጥናትም የሀገር በቀል እውቀቶችን ፋይዳ በቴክኒክና ሙያ ትምህርት ዘርፍ ማካተትን ታሳቢ ያደረገ ነው። ሀገር በቀል እውቀቶች ላይ ጥናት ማድረግ አስፈላጊ የሆነበትን ምክንያት የጥናቱ አቅራቢ ሲያብራሩ እንዳሉት፤ በቱሪዝም ዘርፉ ለሀገር በቀል እውቀቶች እየተሰጠ ያለው ትኩረት አናሳ ነው ። እንደ ቱሪዝም ማሰልጠኛ ኢንስቲትዩት ያሉ ተቋማትና ሌሎች ለቱሪዝም ኢንዱስትሪው የሠለጠነ የሰው ሃይልን የሚያቀርቡ ማሠልጠኛ ተቋማት በሚሰጧቸው የሥልጠና መስኮች ላይ የሀገር በቀል እውቀት /የሀገር ውስጥ ምግብ አዘገጃጀትና የመሳሰሉት/ አለማካተታቸው እንደ ማሳያ ተነስቷል።

ሀገር በቀል እውቀቶችን በማሠልጠኛ ተቋማት ውስጥ እንዲካተቱ ለማድረግ ብዙ ጥረት ማድረግን ይጠይቃል ያሉት አቅራቢው፣ መተግበር ግን እንደሚቻል ነው ያስታወቁት። እነዚህ ሀገር በቀል እውቀቶች በተለያዩ የሀገሪቱ ክፍሎች የሚገኙ መሆናቸውንም በመጥቀስ፣ በእነዚህ ላይ ጥልቅ ጥናት ማድረግ እንደሚያስፈልግም ጠቁመዋል።

በሀገሪቱ የተለያዩ አካባቢዎች በሚገኙ ባህላዊ ምግቦች እና መጠጦች ላይ ጥናት በማድረግና በእዚህ ሀገር በቀል እውቀት ላይ የራሱ የትምህርት ፍኖተ ካርታ እንዲዘጋጅለት በማድረግ፣ እውቀቱን በማሠልጠኛ ተቋማት ሥልጠና ሥራ ላይ በማካተት ቢሠራ በዓለም የንግድ ውድድር ላይ በሚገባ ተጠቃሚ እንደሚያደርግም ተጠቁሟል። በሀገር በቀል እውቀት ላይ የተጠናከሩ ጥናቶችን በማድረግ በገበያው ላይ ጠንካራ አቅርቦትና የገበያ ትስስር በመፍጠር ተጠቃሚ መሆን ይቻላል ተብሏል።

ሀገር በቀል እውቀቶችን መመዝገብ ፣ የሥራ እድል መፍጠር የሥልጠና ሰነድ ማዘጋጀት ፣ እና ሠልጣኞች ከሀገር በቀል እውቀቶች ጋር እንዲተዋወቁ ማድረግ ይገባል የሚል ምክረ ሃሳብም ተሰጥቷል።

ማሠልጠኛ ኢንስቲትዩቱ እነዚህን ሀገር በቀል እውቀቶች በሚገባ በማስጠናት ወደ ዘርፉ እንዲገቡ ለማድረግ በተለያዩ የባህል ምግቦች ላይ ሳይንሳዊ በሆነ መንገድ ጥናት በማካሄድ ላይ እንደሚገኝ የተገለጸ ሲሆን፣ ይህንንም የሥራ እድል መፍጠሪያ ለማድረግ በሥልጠና በማካተት ለመስጠት እንዲያስችል ለማድረግ እየሠራ ይገኛል ተብሏል።

በመድረኩ ላይ እንደተጠቆመው፤ እየተጠናቀቀ ባለው 2016 በጀት ዓመት ኢንስቲትዩቱ የስምንት ክልሎችን ባህላዊ ምግቦች ለማጥናት አቅዶ ባለፉት ዘጠኝ ወራት የአምስቱን ክልሎች አጥንቷል። ጥናት የተደረገባቸው ምግቦችም የስልጤ ፣ ሀዲያ ፣ ወላይታና ኮንሶ ባህላዊ ምግቦች ናቸው። እነዚህ ጥናት የተደረገባቸውን ባህላዊ ምግቦች የጥናት ሰነድ ወደ ሥልጠና በማካተት ምግቦቹ ደረጃቸውን በጠበቁ ሆቴሎች የሚዘጋጁበትን ሁኔታ ለመፍጠር ታቅዶ እየተሠራ ነው።

በመድረኩ ላይም ሀገር በቀል እውቀቶችን በመተመለከተ ከባህላዊ ምግቦች ባሻገር በባህላችን ውስጥ ያሉ የእንግዳ አቀባበል ፣ አለባበስ ፣ ባህል እና ሙዚቃ ማሰብ ከታዳሚያን የተነሱ ሃሳቦች ናቸው ።

የቱሪዝም ዘርፉን ይበልጥ ለማሳደግ እና ሀገር የሚገባትን ጥቅም እንድታገኝ በዘርፉ የተሠማሩ አገልግሎት ሰጪ ተቋማት አገልግሎት አሰጣጣቸውን ደረጃውን የጠበቀ ማድረግ ፣ እንደ ሀገር ያሉትን ሀብቶች በሚገባው ልክ ለመጠቀም የሚያስችሉ ሀብቶችን ማስተዋወቅ እና ገቢ እንዲያመጡ ማድረግ እንደሚገባ ተጠቅሷል ።

ሀገሪቱ ከቱሪዝም ሀብት የሚገባትን ጥቅም እንድታገኝ ለማድረግ በሚሰሩ ሥራዎች የዘርፉ ባለድርሻ አካላት ከሀገር ውጪ የሚመጡ ጎብኚዎችን ለመሳብ ከሚያደርጉት ጥረት ጎን ለጎን የሀገር ውስጥ ጎብኚዎችን የበለጠ ለመሳብ መሥራት እንደሚገባም ተመላክቷል።

በመድረኩ ላይ በቱሪዝም ዘርፍ ውስጥ እንደ ክፍተት ተደርገው የተነሱት በተለያዩ አካባቢዎች የሚታዩት የጸጥታ ችግሮች ፣ ጎብኚዎች ሊሄዱባቸው በሚችሉ እና የቱሪዝም ሀብት በሚገኝባቸው ቦታዎች የመሠረተ ልማት አለመሟላት ፣ ረጅም ዓመት ላስቆጠሩ ቅርሶች የሚደረገው ጥበቃ ጉድለት እንደ ችግር ተጠቅሰዋል።

# ሳምንቱን በታሪክ

## የታሪክ ነጋሪው ታሪክ

**ዋለልኝ አየለ**

አዲስ ዘመን ጋዜጣ የዘመን መስታወት ነው፡፡ የዘመን መስታወት ነው ማለት በየዘመኑ የነበሩ ሁነቶችን ያሳየናል ማለት ነው፡፡ በዚህ «ሳምንቱ በታሪክ» በተሰኘው ዓምድ እንኳን ብዙ ታሪኮችን አይተንበታል፡፡

ዛሬ ደግሞ የራሱን ታሪክ ልናይ ነው፡፡ የዘመን መስታወት የሆነው አዲስ ዘመን ጋዜጣ መታተም የጀመረው ከ83 ዓመታት በፊት በዚህ ሳምንት ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ነው። የጋዜጣው 83ኛ ዓመት ባለፈው አርብ ግንቦት 30 ቀን 2016 ዓ.ም ነበር፡፡ ይህ የዜናም የታሪክም ነጋሪ የሆነ ጋዜጣ እስኪ ዛሬ የራሱን ታሪክ እናስታውስለት፡፡

ከዚያ በፊት ግን እንደተለመደው ሌሎች የዚህ ሳምንት የታሪክ ክስተቶችን በጥቂቱ እናስታውስ፡፡

ከ24 ዓመታት በፊት በዚህ ሳምንት ግንቦት 26 ቀን 1992 ዓ.ም «የፊደል ገበታ አባት» በመባል የሚታወቁት ቀኝ አዝማች ተስፋ ገብረሥላሴ (ዘብሔረ ቡልጋ) ተወለዱ፡፡

ከ251 ዓመታት በፊት በዚህ ሳምንት ግንቦት 27 ቀን 1765 ዓ.ም፤ ቁንጅናቸው፣ በባልትና ሙያቸው፣ በፖለቲካ ብቃታቸው ተደናቂና ተፅዕኖ ፈጣሪ የነበሩት፣ በኢትዮጵያ ታሪክ ስማቸው ጎላ ብሎ ከሚጠቀሱ እንስቶች መካከል አንዷ የሆኑት እና የአጼ በካፋ ባለቤት የነበሩት እቴጌ ምንትዋብ አረፉ፡፡

ከ33 ዓመታት በፊት በዚህ ሳምንት ግንቦት 27 ቀን 1983 ዓ.ም ኢህአዴግ አዲስ አበባን በተቆጣጠረ ልክ በሳምንቱ አዲስ አበባ ውስጥ ከፍተኛ ፍንዳታ ተከሰተ፡፡ ፍንዳታው የተከሰተው ጎተራ በሚገኘው የጦር መሳሪያ ማከማቻ ግምጃ ቤት ሲሆን፤ መላው አዲስ አበባን ያናወጠ፣ ከ100 በላይ የሚሆኑ ሰዎችን ሕይወት የቀጠፈ እና በርካቶችን ያቆሰለ ክስተት ነበር፡፡ በዚሁ ፍንዳታ ከኢትዮጵያ ጋር ልዩ ቁርኝት የነበረው ታዋቂው ኬንያዊ የፎቶ ጋዜጠኛ መሐመድ አሚን በፍንዳታው አንድ እጁን አጥቷል፡፡ ጆን ማታይ የተባለው ባልደረባው ደግሞ ለሕልፈት ተዳርጓል፡፡ የወቅቱ ጊዜያዊ አስተዳደር (ኢህአዴግ) ድርጊቱን የፈፀሙት «የደርግ ርዝራዦች ናቸው» ሲል «ኢህአዴግ ራሱ ነው» የሚሉ ወገኖችም ነበሩ፡፡ ያም ሆነ ይህ ከደርግና ከኢህአዴግ የግንቦት ወር ክስተቶች አንዱ ሆኖ በታሪክ ይታወሳል፡፡

ከ24 ዓመታት በፊት በዚህ ሳምንት ግንቦት 27 ቀን 1992 ዓ.ም በኢትዮጵያ የኤፍ ኤም ሬዲዮ ታሪክ የመጀመሪያ የሆነው፣ በ24 ሰዓት ሥርጭት የመጀመሪያ የሆነው ኤፍ ኤም አዲስ 97.1 ሥርጭቱን ጀመረ፡፡ በዚህ ዓመት 24ኛ ዓመቱን ሲያከብር «ለተሻለ ነገ እናንብብ» በሚል መሪ ሃሳብ የ100 ቀን ልዩ የንባብ ዘመቻ አካሂዷል፡፡ በዚህም 99 ምሁራን፣ ፖለቲከኞች፣ ደራሲዎችና ሌሎች ታዋቂ ሰዎች መጻሕፍትን ሲጠቁሙ ቆይተው በመጨረሻም በ100ኛው ቀን በውይይት፣ በመጽሐፍ ዓውደ ርዕይና ሽያጭ ተጠናቋል፡፡

ከ80 ዓመታት በፊት በዚህ ሳምንት ግንቦት 28 ቀን 1936 ዓ.ም ፍቅር እስከ መቃብር መጽሐፍን በመተረክ የሚታወቀው ተዋናይ ወጋየሁ ንጋቱ ተወለደ፡፡ የፍቅር እስከ መቃብር ደራሲ ሀዲስ አለማየሁ ስለወጋየሁ ንጋቱ ተጠይቀው «ፍቅር እስከ መቃብርን እኔ ጻፍኩት፤ ወጋየሁ ነፍስ ዘራበት» ማለታቸው ይታወሳል፡፡

ከ32 ዓመታት በፊት በዚህ ሳምንት ግንቦት 29 ቀን 1984 ዓ.ም የጋዜጠኛ፣ ደራሲና የታሪክ ተመራማሪ ጳውሎስ ኞኞ ሕይወት አለፈ፡፡ ጳውሎስ ኞኞ እና አዲስ ዘመን ጋዜጣ ጥብቅ ቁርኝት ስላላቸው ከአዲስ ዘመን ጋዜጣ ጋር አያይዘን እናነሳዋለን፡፡ በዚሁ ወደ ታሪክ ነጋሪው አዲስ ዘመን ጋዜጣ ታሪክ እንለፍ፡፡

ከታሪክ መጻሕፍት ጀርባ ማጣቀሻ ሆኖ እናገኘዋለን። የታላላቅ ሰዎች ግለ ታሪክ ሲጻፍ ምንጭ ሆኖ ይገኛል፡፡ የታላላቅ ደራሲዎችና ፖለቲከኞች ሥራዎች ይገኙበታል፡፡ ወደ አንድ ምዕተ ዓመት የተጠጉ ሁነቶች ተሰንደው ይገኙበታል። ከ80 ዓመታት በፊት የነበሩ የኢትዮጵያ ፖለቲካዊ፣ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ጥበባዊ ሁኔታዎች ይገኙበታል፡፡ አዲስ ዘመን ጋዜጣ!

በዚህ «ሳምንቱ በታሪክ» በሚለው ዓምድ ሥር ከብዙ ዓመታት በፊት በሳምንት ውስጥ የተከሰቱ ክስተቶችን የምናስታውሰው እንደ አዲስ ዘመን ጋዜጣ ያሉ አንጋፋ ታሪክ ሰናጆች ባስቀመጡት ሰነድ ነው፡፡ የሌሎችን ክስተቶች ታሪክ ሲናገር የኖረው አዲስ ዘመን ጋዜጣ የራሱ ታሪክ በጣም ሰፊ ይሆናል ማለት ነው፡፡

አዲስ ዘመን ጋዜጣ በዕለተ ቅዳሜ ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተመሰረተ፡፡ እነሆ ለ83 ዓመታት የሀገሪቱ ብቸኛ ዕለታዊ ጋዜጣ በመሆን የአራት ሥርዓተ መንግሥታትን (የአሁኑን ጨምሮ) ምንነት ሰንዶ አስቀምጧል፤ እያስቀመጠ ነው። የእነዚህ መንግሥታት ባህሪም የሚታወቀው በዚሁ ጋዜጣ ነው፡፡

አሁን ላይ ያለ ወጣት ንጉሣዊ ሥርዓቱ ምን አይነት እንደነበር አያውቅም፡፡ ቤተ መጻሕፍት በመግባት ግን ከአዲስ ዘመን ጋዜጣ ማግኘት ይችላል፡፡ የጋዜጣ ሰነድነት ከመጻሕፍትና ከሌሎች ሰነዶች ይለያል፡፡ ምክንያቱም ዜናዎች አሉበት፡፡ ዜና በወቅቱ ዜና ይሁን እንጂ ከዘመናት በኋላ ግን ታሪክ ይሆናል፡፡ ምክንያቱም የመንግሥታት ዕለታዊ ክንውኖች ስለሚጻፉበት ማለት ነው፡፡



የአዲስ ዘመን ጋዜጣ መጀመሪያው ዕትም (ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም)

**የአዲስ ዘመን ጋዜጣ የመጀመሪያ ዕትም ፤**

አዲስ ዘመን ጋዜጣ ስሙ ከታላላቅ ደራሲዎች ጋር ይነሳል፡፡ የእነዚህ ደራሲዎች ስም ሲነሳ አዲስ ዘመን፣የአዲስ ዘመን ስም ሲነሳ የእነዚህ ደራሲዎች ስም ተያይዞ ይጠራል። በተለይ የበዓሉ ግርማ እና የጳውሎስ ኞኞ ግን ይደጋገማል። ምክንያቱም እነዚህ ደራሲዎች በታሪክ እና በፖለቲካ ውስጥ ከፍተኛ ተፅዕኖ ስለፈጠሩ ነው፡፡ ደራሲና ጋዜጠኛ ብርሃኑ ዘሪሁን እና ደራሲ ስብሃት ገብረእግዚአብሔር አዲስ ዘመን ጋዜጣ ላይ የሰሩ ታላላቅ ደራሲዎች ናቸው፡፡ ብርሃኑ ዘሪሁን የጋዜጣው ዋና አዘጋጅ ነበር፡፡ ሌሎች አንጋፋና ወጣት ደራሲዎችም በአዲስ ዘመን ጋዜጣ በቋሚ ተቀጣሪነትም በፍሪላንሰርነትም፣ በውጭ ፀሐፊነትም የሰሩ ብዙ ናቸው። እነ ማዕረጉ በዛብህ፣ ደራሲ ዘነበ ወላ፣ አንተነህ ይግዛው.... ይጠቀሳሉ፡፡ እስኪ ከአዲስ ዘመን ጋዜጣ ታሪክ ጋር ስማቸው የሚነሳውን ታላላቅ ደራሲዎች እና የአዲስ ዘመን ጋዜጣን የታሪክ፣ የጋዜጠኝነትና ስነ ጽሑፍ ትዝታዎች እናስታውስ፡፡

በዓሉ ግርማ

በዓሉ ግርማ የአዲስ ዘመን ጋዜጣ ዋና አዘጋጅ የነበረ እና የስነ ጽሑፍ አርበኛ ነው፡፡ በዓሉ ግርማ በተለይም «ኦሮማይ» በተሰኘው መጽሐፉ ጋዜጠኝነትንም ስነ ጽሑፍንም አሳይቷል።

መጽሐፉ ጋዜጠኝነትንና ስነ ጽሑፍን የያዘ ነው፡፡ እንደ ጋዜጠኛ ያየውንና የሰማውን ጽፏል፡፡ የጋዜጠኛን ድፍረት አሳይቷል፡፡ ጋዜጠኛ አድርባይ፣ ወላዋይና ፈሪ መሆን እንደሌለበት አሳይቷል፡፡ የጋዜጠኝነት ሙያ ህይወትን እስከማጣት መስዋዕትነት የሚከፈልበት መሆኑን በተግባር አሳይቷል፡፡

እንደ ስነ ጽሑፍ ካየነውም፤ እነሆ መማሪያ እስከመሆን ደርሷል፡፡ ለብዙ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የጥናትና ምርምር ምንጭ ሆኗል፡፡ በጋዜጠኝነት ትምህርት ቤትም በስነ ጽሑፍ ትምህርት ቤትም ማነፃፀሪያ ተደርጓል፡፡ የስነ ጽሑፍ አላባውያን ለሚባሉት መሰረት ሆኗል፡፡ በየስነ ጽሑፍ ውይይቱ የበዓሉ መጽሐፎች ስም ይነሳል፡፡ አገላለጾቹ ስነ ጽሑፋዊ ውበት ያላቸው ናቸው፡፡ ረቂቅ አገላለጽ ይጠቀማል። ተምሳሌታዊ ትርጓሜን አሳይቷል፡፡ ፍቅርን አሳይቷል፡፡

ለህይወቱ መጥፋት ምክንያት ስለሆነ እና ፖለቲካዊ ይዘት ስለሆነ «ኦሮማይ» ተደጋገመ እንጂ ሌሎች መጽሐፎችም አሉት፡፡ የቀይ ኮከብ ጥሪ የሚለው መጽሐፉም እንዲሁ ፖለቲካና ስነ ጽሑፍን የያዘ ነው፡፡ ከአድማስ ባሻገር በብዛት የሚደጋገመው በስነ ጽሑፍ ሰዎች ዘንድ ነው፡፡ ሀዲስ፣ ደራሲው እና የህሊና ደወል የሚሉትም ቢሆን ተደጋግመው የተነበቡ ናቸው፡፡ በአጠቃላይ በዓሉ ግርማ ለስነ ጽሑፍና ለጋዜጠኝነት ሙያ መስዋዕት የሆነ ሰው ነው፡፡ እንደ ታሪክ ደግሞ በወቅቱ የነበረውን ክስተት አሳይቷል፡፡ ስለዚህ የበዓሉ ግርማ እና የአዲስ ዘመን ጋዜጣ ታሪክ የጋዜጠኝነትም ታሪክ ነው፡፡

### ጳውሎስ ኞኞ

ጋዜጠኛ የሆኑም ያልሆኑም ሰዎች ስለ ጳውሎስ ኞኞ እና አዲስ ዘመን ጋዜጣ አንድ ነገር ያውቃሉ፡፡ ይሄውም «አንድ ጥያቄ አለኝ» የሚለው የጳውሎስ ኞኞ ጽሑፍ ነው። የትም ቦታ የጳውሎስ ኞኞ ስም ከተነሳ አዲስ ዘመን ጋዜጣ ላይ የነበረው ይሄ ዓምዱ ይጠቀሳል፡፡ ጳውሎስን ለማስታወስ ሲባልም የሬዲዮ ፕሮግራም እና የህትመት ዓምዶችም ወጣ ገባ እያሉ ተሰይመዋል፡፡ በኩረጃ ሳይሆን እሱን ለማስታወስ መሆኑን እየጠቀሱ ማለት ነው፡፡

ስለጳውሎስ ኞኞ የጋዜጠኝነት ፍቅር አንድ ጓደኛው የነበረ ሰው በሬዲዮ ሲናገር የሰማሁትን ገጠመኝ ላካፍላችሁ፡፡

ጳውሎስ ታሞ ተኝቶ ነው፡፡ ጓደኞቹ ሊጠይቁት ከቤቱ ይሄዳሉ፡፡ ሲሄዱ በፀና ታሞ ተኝቷል፡፡ ብዙም አያናግራቸውም፤ በህመም ላይ አናጨናንቀውም ብለው ዝም ብለዋል፡፡ በቤቱ ውስጥ የተከፈተው ሬዲዮ እያወራ ነው፡፡ ጋዜጠኛው አንድ ስህተት ይሳሳታል፡፡ ይህኔ ጳውሎስ «አይ! አዳምጡትማ ይሄን ጋዜጠኛ...» ብሎ የጋዜጠኛውን ስህተት አስተካክሎ ነገራቸው፡፡ በህመም ላይ ያለ ሰው፤ እንኳን ስህተትን ነቅሶ ማውጣት ስለምን እየተወራ እንደሆነ ራሱ ልብ አይልም ነበር፡፡ ጳውሎስ ኞኞ ግን በህመም ውስጥ ሆኖ እንኳን መረጃን እያጣራ ይሰማ ነበር ማለት ነው፡፡

ስለ ጳውሎስ ኞኞ የሚነገር ሌላ አንድ አስቂኝ ገጠመኝ ደግሞ አለ፡፡ ለስታዲየም መስሪያ ተብሎ መዋጮ እየተዋጣ ነው፡፡ የኳስ ነገር ያልጣመው ጳውሎስ «ኧረ ይሄ ነገር ይቅር» ይላል፡፡ በጣም ወሳኝ ጉዳይ እንደሆነ ሲነግሩት «አሥራ አንድ ጅሎች አንድ ቅሪላ ሲከታተሉ ለማየት አላዋጣም» ብሎ የተሰበሰበው ብር ለሆስፒታል ግንባታ መዋል እንዳለበት ተናግሯል፡፡

ጳውሎስ ኞኞን የሚያውቀው ሁሉ አንድ የሚያውቀው ታሪኩ ደግሞ በመደበኛው ትምህርት ከ4ኛ ክፍል በላይ ያልተማረ ምሁር መሆኑ ነው፡፡ የታሪክ ተመራማሪ ነው። በኢ-መደበኛ ትምህርት እና በጥልቅ ንባብ ምሁር መሆን እንደሚቻል ያሳየ ሰው ነው፡፡ «የሴቶች አምባ፣ አጤ ምኒልክ፣ አጤ ቴዎድሮስ ፣ አስደናቂ ታሪኮች ፣ የኢትዮጵያና የጣሊያን ጦርነት ፣ አራዳው ታደሰ ፣ የኔዎቹ ገረዶች ፣ የጌታቸው ሚስቶች ፣ ምስቅልቅል፣ እንቆቅልሽ ፣ አጤ ምኒልክ ከውጭ ሀገራት የተጻጻፏቸው ደብዳቤዎች፣ አጤ ምኒልክ በሀገር ውስጥ የተጻጻፏቸው ደብዳቤዎች» የጳውሎስ ኞኞ መጽሐፎች ናቸው፡፡ ይሄ ሰው ጋዜጠኛ፣ ደራሲ፣ የታሪክ ተመራማሪ ብቻ አልነበረም፡፡ በእርሻ ሚኒስቴር (ለዚያውም ገና በ17 ዓመቱ) የእንስሳት ሐኪም ሆኖም ሰርቷል፡፡

ጳውሎስ በጋዜጠኝነት ዘርፍ በአዲስ ዘመን ጋዜጣ ፣ በኢትዮጵያ ድምፅ ጋዜጣ፣ በኢትዮጵያ ዜና አገልግሎት፣ በኢትዮጵያ ቴሌቪዥን እንዲሁም በኢትዮጵያ ራዲዮ ለአመታት መረጃ በመስጠት፣ በማስተማርና በማዝናናት ህዝብን በማንቃት በጋዜጠኝነት ሙያው አንቱታን አትርፏል።

ጳውሎስ ኞኞን ዛሬ የምናስታውሰው ከአዲስ ዘመን ጋዜጣ ጋር ባለው ታሪክ ብቻ አይደለም፡፡ የራሱ የሕይወት ታሪክም በዚህ ሳምንት ስለሚታወስ ነው፡፡ ጳውሎስ ኞኞ ህይወቱ ያለፈው ከ31 ዓመታት በፊት በዚህ ሳምንት ግንቦት 29 ቀን 1984 ዓ.ም ነው፡፡ ከአዲስ ዘመን ጋር ያላቸውን ቁርኝት የሥራ ታሪክ ብቻ ሳይሆን የሕይወት ታሪኩም አቀራርቦታል ማለት ነው፡፡ እነሆ መልካም ስም ከመቃብር በላይ ይውልና ሲወደስ ይኖራል፡፡

### ብርሃኑ ዘሪሁን

ዕውቁ የስነ ጽሑፍና የታሪክ ሰው ብርሃኑ ዘሪሁን የአዲስ ዘመን ጋዜጣ ዋና አዘጋጅ ነበር፡፡ የጋዜጣው ዋና አዘጋጅ እያለ ከመንግሥት ጋር ይጋፈጥ እንደነበርም ይነገራል፡፡

ብርሃኑ ዘሪሁን በኢትዮጵያ ስነ ጽሑፍ ውስጥ ትልቅ አሻራ አስቀምጧል፡፡ ለታሪካዊ ልቦለድ አጻጻፍ ፈር ቀዳጅ ሆኗል፡፡ የተውኔት ሥራዎችን እና የታሪክ ምርምሮችን ሰርቷል፡፡

«የቴዎድሮስ እንባ፣ የታንጉት ምስጢር፣ ማዕበል የአብዮት ዋዜማ፣ ማዕበል የአብዮት መባቻ፣ ማዕበል የአብዮት ማግስት፣ ጨረቃ ስትወጣ»፣ አማኑኤል ደርሶ መልስ፣ የእንባ ደብዳቤዎች፣ የበደል ፍፃሜ» የሚሉት መጻሕፍት ሲሆኑ፤ ‹ባልቻ አባነፍሶ፣ «ጣጠኛው ተዋናይ፣ የለውጥ አርበኞች፣ ሞረሽ...» የተሰኙ ተውኔቶችን ጽፏል፡፡

የአዲስ ዘመን ጋዜጣ ታሪክ ሲነሳ የእነዚህ ሁሉ ሰዎች ታሪክ ነው የሚነሳው፡፡ ለዚያውም ትልልቅ ፖለቲካዊ ጉዳዮች ሳይዳሰሱ ማለት ነው፡፡ በግለሰብ ደረጃ እንኳን የአዲስ ዘመን ጋዜጣን ስም የሚያስጠሩ ብዙ ታላላቅ ሰዎች አሉ፡፡

በፖለቲካው ዘርፍ ደግሞ ንጉሣዊ ሥርዓቱ ምን እንደነበር፣ በወቅቱ ምን አይነት ዜናዎች ይሰሩ እንደነበር፣ ምን አይነት ፖለቲካዊ እንቅስቃሴዎች ይደረጉ እንደነበር ይነግረናል፡፡ በወታደራዊው የደርግ መንግሥትም ሆነ በአብዮታዊው ኢህአዴግ ዘመን የነበሩ ሁነቶችን ሁሉ ከዚሁ ጋዜጣ ላይ ማግኘት ይቻላል፡፡ እነሆ በአሁኑ የብልጽግና አስተዳደርም አዲስ ዘመን ጋዜጣ ዕለታዊ ሁነቶችን እየዘገበ ዛሬን ለነገ እያስቀመጠ ነው፡፡

ጋዜጣው «አዲስ ዘመን» የሚለውን ስያሜ እንዴት አገኘ? የሚለውን እና የመጀመሪያው ዕትም ላይ የወጡ ጽሑፎችን እናስታውሳችሁ፡፡

ቀዳማዊ አፄ ኃይለሥላሴ ሚያዝያ 27 ቀን 1933 ዓ.ም ከስደት ከቆዩበት እንግሊዝ ተመልሰው አዲስ አበባ ሲገቡ ለሕዝቡ ባደረጉት ንግግር «... ከማናቸውም አስቀድሞ ለሁላችሁም ልነግራችሁና ልትረዱት የምፈልገው ይህ ቀን ለአዲሲቱ ኢትዮጵያ የአዲስ ዘመን መክፈቻ መሆኑን ነው። በዚህም በአዲስ ዘመን ሁላችን መፈፀም ያለብን አዲስ ስራ ይጀመራል ...» ብለው ስለነበር ጋዜጣውም «አዲስ ዘመን» ተብሎ ተሰየመ፡፡

በጋዜጣው የመጀመሪያ ዕትም የመጀመሪያ ገጽ ላይ ንጉሰ ነገሥቱ በፋሺስት ኢጣሊያ ወረራ ምክንያት ከአምስት ዓመታት የስደት ቆይታ በኋላ አዲስ አበባ ሲገቡ የሚያሳየውን ፎቶግራፍ እና ስለጋዜጣው ዓላማ የሚገልፅ ጽሑፍ ወጥቶ ነበር፡፡

« ... ይህ አዲስ ዘመን ተብሎ የተሰየመው ጋዜጣ ከዛሬ ጀምሮ ወደፊት ለመላው ለኢትዮጵያ ሕዝብ የረዳትነቱን ስራ ይሰራ ዘንድ ተመሰረተ፡፡ ግርማዊ ቀዳማዊ አፄ ኃይለሥላሴ ለኢትዮጵያ አዲስ በሆነው ዘመን ለሀገርና ለሕዝብ ጥቅም የሚያስፈልገውን ስራ ሁሉ እያመለከተ፤ ይልቁንም ሕዝብ ለሀገሩ ለመሪውና ለንጉሰ ነገሥቱና ለንጉሰ ነገሥቱም መንግሥት ማድረግ የሚገባውን እየገለፀ የበጎን ስራ መንገድ የሚመራ እንዲሆን ይህ ጋዜጣ በግርማዊ ንጉሰ ነገሥት ተመሰረተ፡፡

ስራውም በሦስት ቃሎች ይጠቀለላል፡፡ እውነት፣ ረዳትነትና አገልግሎት፡፡ እውነት ስንል በዚህ ጋዜጣ የሚነገረው ነገር ሁሉ መሰረቱ በፍጹም እውነትን እየተከተለ ለአንድ ጥቅም ብቻ ያልሆነና ለመላው ጥቅም የሚሰራ እንዲሆን ነው። አገልግሎት ስንል የኢትዮጵያን ነፃነት ለመመለስ ራሳቸውን መስዋዕት አድርገው የራሳቸውን ጥቅም ሁሉ አስወግደው ለሕዝባቸውና ለሀገራቸው ሲሉ የሰው አቅም ሊሸከመው የማይቻለውን ድካም ተቀብለው ማንኛውም ሰው ሊያደርገው ያልተቻለውን በኢትዮጵያ ሕይወት ውስጥ እስከዛሬ ድረስ ያልታየውን ስራ ከፍፃሜ ላደረሱ ለተወደዱ ንጉሰ ነገሥታችንና ላቆሙት መንግሥት የሚያገለግል እንዲሆን ነው...» የሚል ነበር፡፡

አዲስ ዘመን ጋዜጣ ዕለታዊ ሁነቶችን እየዘገበ እነሆ 83 ዓመታት ተጓዘ፡፡

# የዝነኞች ገጽ

## ወርቃማው ነበልባል

**ሙሉጌታ ብርሃኑ**



እሳት የወለደው ወርቃማው የእሳት ነበልባል አረንጓዴ ቢጫ ቀይ አርማዊ ቀስተደመና ሠርቶ ከሰማያዊው የሙዚቃ ሰማይ ላይ ሲወርድ የተመለከተው ማነው...ውሃ የወለደው እሳት መብረቅ ይሆናል፡፡ የመብረቁ ነበልባልም በረዶውን ከዝናብ ጋር ቀላቅሎ ድምጹን እያስገመገመ እንደሚመጣው ሁሉ ግጥሙን ከዜማው ጋር ቀላቅለው ኳ! እያሉ ወርደው ሁለት ሳሉ አንድ ሆነዋል፡፡ በመሀል ከተማ ላይ የጎሞራ ባህር ሠርተዋል፡፡ እሳትም ውሃም የጥበብ ማዕበል የሙዚቃ መርበብት ናቸው፡፡

ከ1960ዎቹ ተነስተው በ70 እና 80ዎቹ ሙዚቃዎች ውስጥ ሲንበለበሉ ቆይተው ይሄው ዛሬም ድረስ አሉ። ውቅያኖሱ የሙዚቃ ግጥም ደራሲ ይልማ ገብረአብ እና ዋኖሱ የዜማ ደራሲ አበበ መለሰ የሙዚቃ መርከብ ያረፈባቸው ጠሊቃን ናቸው፡፡ ያለ ግጥም ያለ ዜማ ያለ ሁለቱ ሙዚቃ አይቆምም፡፡ ጣምራዎቹም አንዱ ከአንዱ የማይነጣጠሉ ዘውድና ጎፈር ናቸው፡፡ ለዛሬው ግን ግድ ብሎን አንዱን ብቻ ነጥለን ልንተርከው ነው፡፡ ስለ አንደኛው ሲወራ የምንሰማው ግን ስለ ሌላኛው ነው፡፡

ነበልባሉ የእሳት ጎሞራን ይመስላል፡፡ ከጎሞራው በፊት ከብልጭታው ልንጀምር ስንል ለመጀመሪያ ጊዜ ፈንጥቆ ወደታየበት መነሻው ይወስደናል፡፡ በአራት ኪሎ በሰባ ደረጃ ቆመው አሻግረው ፒያሳን የተመለከቱ እንደሆነ በዓይን ጥቅሻ ወደዚያው ያመለክተናል፡፡ በዶሮ ማነቂያ ግንባር ቁልቁል እየተምዘገዘገን ወርደን በሠራተኛ ሰፈር ወገብ ላይ አረፍ ስንል ደግሞ ያንን ነበልባል ከብልጭታው ጋር እንመለከታለን፡፡ ያ የምንመለከተው የእሳት ብልጭታም ትንሹ ይልማ ገብረአብ ነው፡፡

በዚያ ሠራተኛ ሰፈር ውስጥ በወርሀ ነሀሴ 1953ዓ.ም ከእናቱ ማህጸን ብልጭ ብሎ ለጎመራው ጥበብ በቃ፡፡ ልጅነቱን ከጥበብ ጋር ሲሯሯጥ ነበልባሉ ቀድሞ አበሰለው፡፡ የባላባቱ የቀኝ አዝማች ገብረአብ ልጅ ነውና ለመቦረቂያው እርስቱም አይጠበውም፡፡ አርሾን ቀጥሎ ከነበረው የመኖሪያ ግቢያቸው ውስጥ ከተሠራው የቄስ ትምህርት ቤት ጀመረ፡፡ ዳዊቱንም ደገመ፡፡ አስኳላን ፍለጋ ወደ ብርሃን ትምህርት ቤት ሄዶ የአንደኛ ደረጃ ትምህርቱን በማጠናቀቅ ለሁለተኛው መሰናዶ ዳግማዊ ምኒልክ ትምህርት ቤት አመራ፡፡ ገና ብዙም ሳይርቅ ወላጅ አባቱን በሞት አጥቶ ነበርና ቀጣዩ እጣፈንታው ከእናቱና ከእንጀራ አባቱ ጋር ሆነ፡፡ ቢሆንም ግን ጥሩ እንጀራ አገኘበት እንጂ መጥፎ አልነበረም፡፡ በሙዚቃ ህይወቱም የበኩር ምስጋናውን የሚያቀርበውም ለእኚሁ የእንጀራ አባቱ ነው፡፡

በ1966ዓ.ም በዋዜማው ዕለት የተከፈተው የባህል ምሽት ቤት ባለውለታው ነው፡፡ አባቱን (የእንጀራ አባቱን) ተከትሎም ወደዚያው ይሄድ ነበር፡፡ ምናልባትም ሙዚቃን በአካል የተመለከተውና የተዋወቀው ከዚህ ሳይሆን አይቀርም፡፡ የዚህን ጊዜም ገና ልጅ ነው፡፡ የሙዚቃ መሳሪያ ባገኝ ቁጥር አርፎ መቀመጥን አያውቅም፡፡ ጊታሩንም ክራሩንም ብቻ ያገኘውን የሙዚቃ መሳሪያ ሁሉ መነካካቱ የልጅነት ነብሲያውን ታጠግበዋለች፡፡ አባቱም ቢሆኑ ተው! እያሉ አያስቆሙትም፡፡

የነገውን ይልማን ተመልክተው ሙዚቀኛ ይሆናል ባይሉም፤ ግን ደግሞ እራሱን ለልጅነት ደስታው ትተውለታል፡፡ የ11ና 12 ዓመት ልጅ ሆኖ ሙዚቀኝነት ይነሸጠዋል፡፡ ከቤት ክራሩን እያነሳ ከቤተሰቡ ፊት ቆሞ የተሾመ ደምሴ "አዳራሹ ቤቴ"ን ይጫወት ነበር፡፡ ከቤቱ ውስጥ ነጻነትና ጆሮ አልተነፈገውም፡፡ ከዚያን የትንሽነቱ ወራት ጀምሮ ከቀበሌው የኪነት ደጃፍ አይጠፋም ነበር፡፡ ሥራ ሰጥተውም ቤተኛ አደረጉት፡፡ የቀበሌው ሊቀመንበር በየስብሰባው የሚያቀረቡትንም ጽሁፍ ማዘጋጀቱን ተያያዘው፡፡ እንግዲህ እያጠፋም እያለማም ብቻ ግን እዚያ አካባቢ ያሉ ሹመኞችም ቢሆኑ ከልጅነቱ ጋር የሚንቦራጨቀውን ሙዚቃ ሊሰሙለት ይወዱ ነበር፡፡

ከቀበሌው ጋር ያለው ቁርኝት አድጎና ችሎታውም ዳብሮ ሲመለከቱ ወደ ኪነት ቡድኑ እንዲቀላቀል አደረጉት። በአንድ ወቅት የቀበሌውን ጊታር አውጥተው ሰጡት፡፡ እርሱ እንደሆን ሲፈጥረውም ቸር አድርጎ ነውና የሰጡትን ጊታር መልሶ ለሌላ ሰው አዋሰው። ከዕለታት በአንዱ ቀን ታዲያ ያዋሰው ወዳጁ ጊታሩን ተሸክሞ በቀበሌው ደጅ ሲንጎማለል ያልፋል፡፡ በቀበሌው ሰዎች ዓይን ውስጥም ገባ፡፡ ሌሊት ወደ ሰባት ሰዓት ገደማ የይልማ በር ተንኳኳ፡፡ ከገባበት የእንቅልፍ ዓለም ተመልሶ ዓይኑን እያሸሸ በሩን ከፈተ፡፡ ከውጭ የደርግ ወታደሮች ቆመዋል፡፡

ሊቀመንበሩ ሊያናግሩት እንደሚፈልጉ ሲነግሩት አዲስ ሥራ ቢመጣ ነው ብሎ በማሰብ ተከትሏቸው ሄደ። ድግሱ ግን ሌላ ነበር፡፡ የጊታሩ ጉዳይ ያልጠበቀውን መዘዝ ይዞለት መጣ፡፡ ደግነቱ እዳን አስከትሎ ዘብጥያ አወረደው፡፡ ለ6 ወራት ያህልም በእስር እንዲቀጣ ሆነ፡፡

ይልማ ከቤቱ ውስጥ ከጣራው በታች አልጋው ላይ ሆኖ ድንገት ቀጭ ቋ! መሳይ የግጥም ኮቴ "ይረገም!... ይረገም!" ሲል ከምናቡ ላይ አቃጨለበት፡፡ የሀሳቡንም በር ወለል አድርጎ ገባ፡፡ ይሄኔ ብዕሩን ለመጀመሪያው ታሪክ አንስቶ በብጣሽ ወረቀት ላይ አሳረፉት፡፡ ግጥሟ ሙዚቃ ለመሆን ትችላለች ብሎ አሰበ፡፡ እና ማንስ አሳምሮ በድምጹ ያስረቅርቃት? ግጥሟን ይዞ ሙሉቀን መለሰን ፍለጋ ወጣ፡፡

ገጽ ለገጽ ፊቱ ቆሞ እርሱን ለመመልከት በመቻሉ ይልማ ለደስታው ወደር አነበረውም፡፡ ሙሉቀን መለሰም ከፊቱ የቆመውን ታዳጊ አየት አድርጎ ወረቀቱን ተቀብሎ ግጥሙን ተመለከተው፡፡ የወደደው ቢመስልም ይሁን ብሎ ሊያልፈው ግን አልፈለገም፡፡ በደንብ እንዲያበስላት መልሶ ሰጠው፡፡ ተቀብሎም ዳግም በሌላኛው ቀን ተመለሰ፡፡ አሁንም ትንሽ መብሰል ይቀረዋል ሲል እንደገና ሦስተኛ ቀጠሮ ሰጥቶ ሸኘው፡፡ ልቡ ቆማ የጉጉት ክንፍ ልታበቅል ብትደርስም ይልማ አስተያየቱን በክብር ተቀብሎ ከመሄድ ውጪ አንዳችም ቅር አላለውም ነበር፡፡

ለዚህ አስተማሪነቱም ሙሉቀንን ያመሰግነዋል፡፡ ሦስተኛውን ቀጠሮ ሲጠባበቅ ግን ሌላ አጋጣሚ ተፈጠረ። በጭንቅላቱ የዘረው የግጥም ዛር ሲያንከላውስ ወስዶ ከኤፍሬም ታምሩ ደጅ ላይ ጣለው፡፡ የበኩር ብስራቱ ይሆናል ያለውን ሙሉቀን መለሰን ቀድሞ ኤፍሬም ታምሩ ተገኘ፡፡ "ሸግዬ" የሚለውን ግጥሙን ሰጠው፡፡ ኤፍሬም ይህን ሥራ ጨምሮ አልበሙን ባወጣ በሁለተኛው ሳምንት ሙሉቀንም "ይረገም"ን አክሎ መጣ፡፡ ይሄኔ ነው ደስታ! ይሄኔ ነው ተድላ! ይልማ ድል በድል ሆኖ ደስታና ልጅነቱ እንደ ፈንዲሻ ፈካ፡፡ የዓይኔ ነገርማ...

ከዚሁ በኋላ ይልማን ማንስ ያቁመው፤ በተራራማው የሙዚቃ አናት ላይ ወጥቶ እንደ ጎበዝ የጦር ጄነራል ወደፊት እየገፋ አጧጧፈው፡፡ እንዲህም ይቻላል እንዴ እስኪባል ድረስ አንድ ሺህ 2 መቶ ሃምሳ የሙዚቃ ምርኮ ተቆጣጠረ፡፡ ሙሉቀን መለሰ፣ ኤፍሬም ታምሩ፣ አስቴር አወቀ፣ ብዙነሽ በቀለ፣ ማህሙድ አህመድ፣አረጋኸኝ ወራሽ ቴውድሮስ ታደሰ፣ ኩኩ ሰብስቤ፣ ቴዲ አፍሮ... የይልማን የግጥም መረቅ በሰፊው ከጠጡት መሀከል በጥቂቱ እኚህ አንጋፋ ጃግሬዎች ይገኙበታል፡፡

እንደ አርጋኖን ከደመናው በላይ በውብ ፍቅር በውብ የብርሃን ግላጭ እየቀዘፈ፤ ሌላ ጊዜም እንደ መብረቅ እያስገመገመ በግጥሞቹ ነበልባል ታላላቆቹንም ታላቅ ወላፈን አድርጎ ሠርቷል፡፡

«**ሰለወይ ሰለወይ፤**
**ውብ እንዳንቺ፤**
**ጸባዩ ሰናይ፤**"

ቴዲ አፍሮ አዚሞ ተዛዚሞበታል፡፡ ይልማ እኮ ግጥምን ከመድረስ አልፎ ቅኔ ማልበስም ተክኖበታል። እንዴት ያለ ግጥም አዋቂ ነው ለማለትም አስቀድሞ የማወቅ ብቃትን የሚጠይቅ ነው፡፡ ምክንያቱም ከእርሱ ሙዚቃዎች ሙዳይ ውስጥ ያለውን ወርቅ ለመረዳት መስማት ብቻውን በቂ አይደለም፡፡ ከላይ የሚነግረን ፍቅር ሰም እንጂ ወርቁ አይደለም፡፡ የዚህን ጎበዝ ግጥሞች መርምረው ወርቁን የሚያገኙት ጥቂቶች ብቻ ናቸው፡፡

ከበስተጀርባው ታሪክ፣ ሰው፣ ሚስጥር...አንዳች ነገር አይጠፋም፡፡ ተመስጦው ምናቡን ብቻም ሳይሆን ነብሱንም ትሰውረዋለች፡፡ በመብረቅ የታጀበ የሙዚቃ ጎሞራ ከውስጡ ይፈነዳል፡፡

አብዛኛዎቹ ሥራዎቹ አንዳችም ባልጠበቅነው መንገድ ለአንዱ የተጻፉ ስውር መልዕክቶችን እናገኝባቸዋለን፡፡ በ1970 በቀይ ሽብሩ ሰሞን ይልማ አንድ የሙዚቃ ግጥም ጻፈ፡፡ ዜማውንም አበበ መለሰ ሰፍሮ አስቀመጠው። ስምንት ያህል ዓመታትን ቆይቶ 1979ዓ.ም ኤፍሬም ታምሩ ተጫወተው፡፡

«**የናፍቆት ጥፋቱ የበደሉ በደል፤**
**ሲመሽ ነብስ ይዘራል ስፍራ ሲደለደል፤**
**...**
**ለመፈራረጃው ሰፌ ቤት ሳለሽ፤**
**ምነው ባደባባይ ትቀጪኛለሽ፤**»

ስንሰማው ለከዳተኛዋ ፍቅሩ የሚያንጎራጉር ይመስለን ይሆናል፤ የዜማ ደብዳቤው ግን ለደርግ መንግሥት የተሰናዳ መልዕክት ነበር፡፡ የቀይ ሽብር አፈሳ ፊሽካው የሚነፋው ቀን ሳይሆን ማታ ተደላድለው ከተኙ በኋላ ከየበሩ እየተንኳኳና ከጦፈ እንቅልፍ መሀል ከህልም እየነጠሉ ነበርና ሲመሽ ነብስ ይዘራል ማለቱ ለዚህ ነው፡፡ ጠዋት ማልደው ሀገር ሰላም ብለው ሲነሱ አደባባዩ ሁሉ በሬሳ ተሞልቶ በደም ተጨማልቆ ይታያል። ለቅጣቱ የሚሆን ስፍራ ሳይጠፉ ምነው በአደባባዩ መገደላችን ለማለት ቅኔው በሰም ተለብጦ ቀርቧል፡፡ እንዲህ ዓይነቶቹን ለመዘርዘር እንጀምር ይሆናል እንጂ አንጨርሳቸውምና አንዲቷን ብቻ እናክላት፡፡

«**ይረገም ይህ ልቤ አልፎ የሄደበት፤**
**ይረገም ይህ ልቤ ሌላ ያሰበበት፤**
**...**
**የዓይኔ ነገርማ ገና ብዙ አለበት፤**»

ሙሉቀን መለሰ ይህን ዜማ ሲያንጎራጉር "የዓይኔ ነገርማ..." ይልማ ለሙሉቀን የሰጠው የራሱን ታሪክ ነበር፡፡ ከእንግልት መልስ ከአልጋው ላይ ጋደም ብሎ የጻፋት "ይረገም" መነሻው ይሄ ነበር፡፡ "የዓይኔ ነገርማ ገና ብዙ አለበት" ሲል ስለሚመለከትበት ዓይኑ እንጂ ስለሚያፈቅራት ጸባየ ሰናይዋ፤ ስለ አይናለም መሆኑን እንዴትስ ልናውቅ እንችልና...በጣም የሚወዳት ፍቅሩ ነበረች፡፡ ያኔ ወህኒ ሲወርድ የአይንዬ ወንድም በስፍራው ነበር፡፡

በአይንዬ ጦስ ወደፊት ገና ብዙ ነገር እንደሚጠብቀው ለማሰብ አላረፈደም፡፡ ምን ሲል እንዳሰበው የዚህን ወታደር እህት በፍቅር መመኘቱ፡፡ የዚያን ምሽት ከፖሊስ መኪና ውስጥ ሆኖ ወንድሟ መኖሩን ተመለከተ። አይንዬ ደግሞ ከበሩ ላይ ቆማ ታለቅሳለች፡፡ እነዚህን ሁለት ነገሮች ሲመለከት የተያዘው በአይንዬ ጉዳይ መሰለው። ወንድሟም የእጁን ሊሰጠው እንደሆነ አመነ። ምን ሲያቀብጠኝ ይሆን እህቱን ማፍቀሬ ሲልም አሰበ፡፡ በቀበሌው ውስጥ እንግልቱ በዛበት፡፡ ይህን የተመለከቱት የከፍተኛ ኪነትም ከዚያ አስወጥተው ወደራሳቸው ወሰዱት፡፡

በሥራ አብሯቸው ወደ ክፍለ ሀገሮች መንቀሳቀስም ጀመረ፡፡ በአንደኛው ቀን ወደ አሥመራ ለሚደረገው ጉዞ ሲሰናዳ አይኔ ለመጨረሻ ጊዜ የዚያኔ ተመለከታት። ያሳየችው ፊት ዳግም እንደማይገናኙ የሚናገር ነበር። በውስጣቸው ፍም እሳት የሆነ ፍቅር ቢቀጣጠልም ተቀያይመው ተኮራርፈዋል፡፡ ሁለቱም በልባቸው ከያዙት ፍቅር ሌላ አይንዬ በሆዷ ጽንስ ነበር፡፡ ልጅነቱ ግን ተናነቃቸውና ቃል አውጥተው ሳይተነፍሱ በዚያው ተለያዩ፡፡

«**የሀገር ቤቷ ዓይናማ አንቺ ለግላጋ፤**
**አንቺ የገጠር መለሎ የገጠር ሎጋ፤**
**ልቤን ሆዴን ሰወርሽው ሳይመሽ ሳይነጋ፤**»
(ማህሙድ አህመድ)

ከዚያ መለያየት በኋላ ግን ሌላ አዲስ የፍቅር ህይወት ጀመረ፡፡ ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ የተጣመራትን ባለቤቱንም አገኘ፡፡ በሚሠራበት ኪነት ውስጥ የነበረችና ውበቱን ያለስስት የደፋባት የደም ገንቦ አንዲት ቆንጆ ነበረች።

በልጅነቷ ላይ ቀበጥነቷ ተደማምሮ ልቡን ረታችውና ከጀላት፡፡ ልጃቸው በውበቷ ምክንያት ከዓይን ገብታ የጅብ እራት እንዳትሆን የሚሰጉት እናቷ ጸጉሯ በደረሰ ቁጥር ሁሉ በምላጭ ይሸልቱት ነበር፡፡ እርሱም ሊያገባት ቆርጦ እናቷን ተዋወቃቸው፡፡

ለእፎይታው በትዳር መጠቅለሏን ሲጠብቁት የነበረ ምኞታቸውም ነበርና በቶሎ ይሁን አሉ፡፡ የእርሱ ዘመዶች ግን ተቃወሙት፡፡ የእርሷ እናት ግን ግድ የለህም ሁለታችሁንም እኔው እድራችኋለሁ በማለት ሃሳብ እንዳይገባው ገፋፉት። ጊዜው ደርሶም ሠርጉ እንደነገ በአንደኛው ቅዳሜ ማዘጋጃ ተፈራርመው ምሽቱን ከእናቷ ቤት ሲመጡ አሳዛኙን መርዶ አረዱት፡፡ እንዴት ለወንድ አንቺ ትደግሺያለሽ በማለት ሰፈርተኛው ሁሉ ሰደበኝ፤ ስለዚህ አዝናለሁ እሷን እንጂ አንተን ለመዳር አልችልም አሉት፡፡

ይህን ጊዜ ትርምሱ ሌላ ሆነ ለነገ ሠርግ የሚደርስ ድግስ ለማዘጋጀት ሁሉም በየፊናው ተሯሯጠ፡፡ ሙሉቀን መለሰ እንጀራውን ከቤቱ አስጋግሮ አስላከ። በጠዋቱ ጄሪካን አሲዞ ጠላ ፍለጋ የወጣው ይልማ፤ ተክለሃይማኖት ሰፈር ገብቶ የማርያም ጠላ በርሜሉ ፈንድቶብን ነው እባካችሁን ተባበሩን በማለት ጠላውን በየጄሪካኑ አስሞላ። ወዛደር ሆኖ የጠላ ጄሪካኑን ተሸክሞ ሲገባ አጃቢና ሚዜው ከቤት ቁጭ ብሎ እርሱን ሲጠባበቅ ደረሰ፡፡ የኤፍሬም ታምሩ ሚስት ግን ተአምር በሚመስል መልኩ በአንድ ምሽት ሁሉንም አሰናዳችው፡፡

ይህ የሆነው በጥር ወር ላይ ነበር፡፡ ከሠርጉ 15 ቀናት ቀደም ብሎ የአልበም ሥራውን የለቀቀው ኤፍሬም ታምሩ ደግሞ በአድናቆት ሲዘመርለት የነበረበት ሰዓት ነው። የማይሆነው ሆኖ እንዳልጠበቁት ተከሰተ፡፡ የዚያን የሠርጉ እለት በሰፈሩ መቆሚያ መቀመጫ ታጣ፡፡ ከልጅ እስከ አዛውንቱ ኤፍሬምን ለማየት ሲገፋፋ የቤቱ አጥር ሳይቀር ፈረሰ፡፡ የኪነት ቡድኑ ከነ ሙዚቃ መሳሪያው ተገኝቶ አጃኢብ! የተባለለት ሠርግ ሆነ፡፡ የታሰበው መሽቶ ያልታሰበው አጋጣሚ ነጋ፡፡

በጣት ለሚቆጠሩት ግጥሞቹ ካልሆነ በስተቀር ይልማ እራሱ ዜማ አይሰራላቸውም ነበር፡፡ "እርግብ" የተሰኘውን ሙዚቃ ከሸዋ ለመስፍን አበበ ሲሰጠው ግን ከነዜማው ነበር። እርሱም በጊታሩ ጭምር በውብ ድምጹ ብሉኝ ብሉኝ እንደሚል ትርንጎ ዓይነት አድርጎ ሠራው፡፡ የተዜመላት ልጅ ከዘመናት በኋላ አባቷን ፍለጋ የመጣችው የአይንዬ ልጅ፤ እርግቤ ነበረች፡፡ "የዓይኔ ነገርማ ገና ብዙ አለበት" ሲል ታውቆት ነበር፡፡ ያኔ ሲለያት የእርሱን ልጅ በሆዷ እንደተሸከመች ታውቆት ነበር፡፡

በተለያዩ ጊዜያት ልጁን ፍለጋ ወደ እርሷ ቢሄድም አይንዬ ግን ልትሰማው አልፈቀደችም፡፡ ትንሿ እርግብ የይልማ ልጅ ስለመሆኗ ሁሉም የሚያውቀው እውነት የነበረ ቢሆንም፤ ከኔ ምንም ልጅ የለህም በማለት ከአባቷ ሸሽጋ አሳደገቻት፡፡ እርግቤ አድጋ ትልቅ ልጅ ስትሆን ግን አባቷን ስትል አፈላልጋ መጣችለት፡፡

«**እዚያ ማዶ ጋራ ያለሽው እርግብ፤**
**ምን ረሀብ አገኘሽ የሚያንገበግብ፤**»

ወርቃማው ነበልባል፤ ይልማ ገ/አብ እስከዛሬ ድረስም አንድ ሺህ 2 መቶ ሃምሳ የሙዚቃ ግጥሞችን በማበርከት እሳትና ውሃ የወለደው መብረቅ መሆኑን አስመስክሯል፡፡ ከባህሩ ቀኜ እስከ ቴዲ አፍሮ ድረስ 104 ያህል ሙዚቀኞች የእርሱን የግጥም ሥራዎች ተቋድሰዋል፡፡ በህይወት ዘመኑ የሙሉ ጊዜ ሥራውን የሰጠው ለሙዚቃው ነውና በ2011ዓ.ም የህይወት ዘመን ተሸላሚ ለመሆን በቅቷል፡፡ የወርቃማው ነበልባል እሳተ ጎሞራ ከሌላ የአልማዝ ወላፈን ጋር እንመለከተው ይሆናል፡፡

# ስፖርት





# የኮከቧ የኦሊምፒክ የወርቅ ሜዳሊያ ውጥን

**ብርሃን ፈይሳ**

የአትሌቲክሱ ዓለም ከዋክብት የውድድሮችም ድምቀት ከሆኑ የዘመኑ ድንቅ አትሌቶች መካከል አንዷ ኢትዮጵያዊቷ ጉዳፍ ጸጋይ ናት፡፡ በወጣትነት ዕድሜዋ በርካታ ስኬቶችን የተቀዳጀችው ወጣት ኮከብ አትሌት የአንጋፋዎቹን ፈር ከመከተል አልፋ ለተተኪዎች መንገድ በመክፈት ምግባረ ምስጉን ናት፡፡ እየተቀዛቀዘ ባለው የኢትዮጵያ አትሌቲክስ ስኬት ውስጥ እየበራች ተስፋነቷን ስታስመሰክርም ቆይታለች፡፡ አሁን ደግሞ ኢትዮጵያውያን በተደጋጋሚ በከበሩበት ታላቅ የውድድር መድረክ ሌላ ክብርን ለመቀዳጀት እየተጋች ትገኛለች፡፡

ከትግራይ ክልል የተገኘችው ጉዳፍ አትሌቲክስን የተቀላቀለችው ተማሪ ሳለች ነበር፡፡ እለሽኛዋና ጠንካራዋ አትሌት ሀገሯን የወከለችው ገና በልጅነቷ ሲሆን፤ እአአ በ2014 በተካሄደው የዓለም የቤት ውስጥ ቻምፒዮና በ16 ዓመቷ በ1ሺ 500 ሜትር ርቀት በመሳተፍ 9ኛ ደረጃን በመያዝ ነበር ያጠናቀቀችው፡፡ በዚያው ዓመት አሜሪካ ዩጂን ላይ በተደረገው ከ20 ዓመት በታች ቻምፒዮናም በድጋሚ ኢትዮጵያን ወክላ ከእድሜ እኩዮቿ ጋር በመፎካከር የብር ሜዳሊያ ማጥለቅ ችላለች፡፡

ከሁለት ዓመት በኋላ ዳግም በወጣቶች ቻምፒዮና ላይ ስትሳተፍም በሀገሯ ልጅ ቃልኪዳን ገዛኸኝ ተይዞ የቆየውን ፈጣን ሰዓት በ10 ሰከንዶች በማሻሻል በዚህ የእድሜ ገደብ የ1ሺ500ሜትር ርቀት የዓለም ክብረወሰን ባለቤት ለመሆን ችላለች፡፡ ይህም በድጋሚ ለዋናው ብሄራዊ ቡድን ሲያሳጫት ፓርትላንድ ላይ በቤት ውስጥ ቻምፒዮና ሶስተኛ ደረጃን ይዛ በማጠናቀቅ ለሀገሯ የነሃስ ሜዳሊያን አስገኝታለች፡፡ ተስፈኛዋ አትሌት 20 ዓመት ባይሞላትም የነበረችበት አቋም በዚያው ዓመት በተካሄደው የሪዮ ኦሊምፒክ በ800 ሜትር ርቀት ተሳታፊ እንድትሆንም አስችሏታል፡፡ ቀጣዩ የለንደን ዓለም ቻምፒዮናም አትሌቷን በድጋሚ ሀገሯን እንድትወክል ኃላፊነት ያሰጣት ቢሆንም ውጤታማ ግን አልነበረችም፡፡

ጠንካራ ስራ መታወቂያዋ የሆነው ጉዳፍ በድጋሚ ወደ አቋሟ ተመልሳ በዳይመንድ ሊግ ውጤታማነቷን በማስመስከር፤ በኳታሩ የዓለም ቻምፒዮና የኢትዮጵያ ብሔራዊ ቡድን ዝርዝር ውስጥ ልትካተት ችላለች፡፡ በቻምፒዮናው ያጠለቀችው ሜዳሊያ ደግሞ ለቶኪዮው ኦሊምፒክ እንድትመረጥ አስችሏታል፡፡ ጉዳፍ በዚህ ኦሊምፒክ ከምትታወቅበት ርቀት ውጪ በ5ሺ ሜትር የተካፈለች ሲሆን፤ በተከታታይ ዓመት ለሀገሯ ሁለት የነሐስ ሜዳሊያዎችን አስመዝግባለች፡፡ በባለቤቷ ህሉፍ ይህደጎ አሰልጣኝነት ስኬታማ ዓመትን ያሳለፈች ሲሆን፤ ሌቪን ላይ በ1ሺ 500 ሜትር የዓለምን ክብረወሰን በመጨበጥ ጭምር የአትሌቲክስ ስፖርት ፈርጥ መሆኗን አሳይታለች፡፡



**ጉዳፍ ፀጋይ በፓሪስ ኦሊምፒክ ለወርቅ ሜዳሊያ ከሚጠበቁ አትሌቶች አንዷ ናት ፤**

እአአ 2022 ደግሞ ኢትዮጵያን ወክላ በዓለም እና በቤት ውስጥ ቻምፒዮና እና 2 የወርቅ እና 1 የብር ሜዳሊያዎችን ያስመዘገበችበት ነበር፡፡ ሀገር ወዳዷ ጉዳፍ በወቅቱ ከሰሜኑ ጦርነት ጋር በተያያዘ ከቤተሰቦቿ የመራራቅ አጋጣሚ ሳትረታ ኢትዮጵያን በማስቀደም ለባንዲራ ሲታገሉ ከነበሩት መካከል አንዷ ናት፡፡ በዚህ ባህሪዋ ለበርካታ ወጣት አትሌቶች ተምሳሌት የምትሆነው ጉዳፍ ያለፈውን ዓመት በድንቅ አቋም የግል እና ዓለም አቀፍ ውድድሮች ሸፍናለች፡፡ በቡዳፔስቱ የዓለም ቻምፒዮና 10ሺ ሜትር የወርቅ ሜዳሊያ ስታጠልቅ በዳይመንድ ሊግ እና በቤት ውስጥ የቱር ውድድሮች ስኬትን ልትቀዳጅ ችላለች፡፡ ዓመቱን ያጠናቀቀችውም በዓለም ቻምፒዮና ሁለት ሜዳሊያዎችን የማጥለቅ ቁጭቷን በዩጂን ዳመንድ ሊግ በመወጣት ሲሆን፤ የ5ሺ ሜትር የዓለም ክብረወሰንን ወደ ኢትዮጵያ መልሳ የክብር ባለቤት መሆኗ የሚታወስ ነው፡፡

ያለፈውን ዓመት በአስደናቂ ብቃትና ስኬት ያጠናቀቀችው አትሌቷ በተያዘው ዓመት በአትሌቲክስ ቤተሰቡ ዘንድ በከፍተኛ ጉጉት እንድትጠበቅ አድርጓታል፡፡ የኦሊምፒክ ዓመት እንደመሆኑ በታላቁ የውድድር መድረክ የምታስመዘግበው ድል ከወዲሁ አጓጊ ነው፡፡ በእርግጥ የውድድር ዓመቱን በቤት ውስጥ ቻምፒዮና የጀመረች ሲሆን በ3 ሺ ሜትር የብር ሜዳሊያ አጥልቃለች። በዳይመንድ ሊጉ ጎን ለጎን በ10ሺ ሜትር የዓለም ክብረወሰንን ለመስበርም ሙከራ ላይ ነበረች፡፡ የዚህ ዓመት ግቧ ግን ኦሊምፒክ በመሆኑ ዛሬ ላይ 47 ቀናት ብቻ ለቀሩት የፓሪሱ ኦሊምፒክ በዝግጅት ላይ ትገኛለች፡፡

በእርግጥም በወጣቶች ቻምፒዮና፣ በቤት ውስጥ ቻምፒዮና፣ በዳይመንድ ሊግ እና የዓለም ቻምፒዮና መድረኮች ተሳትፎ ባስመዘገበቻቸው ሜዳሊያዎች ብዛት የተንቆጠቆጠው መደርደሪያዋ በኦሊምፒክ መድረክ ግን በአንድ ነሐስ ብቻ የተገደበ ሆኗል፡፡ ስለዚህም ፓሪስ ላይ አዲስ ታሪክ ለማጻፍ ወጥናለች፤ ይህንንም «ሀገሬን በዚህ መድረክ መወከል መቻሌ የሚሰጠኝ ስሜት ከፍተኛ ነው፤ ሕዝቡ ሁሌም ሜዳሊያ እንድናስመዘግብ ይጠብቃል፡፡ ቀደምት አትሌቶችም ይህንኑ ሲያደርጉ ነበር፡፡ ነገር ግን የእኔ ግብ ሜዳሊያ ብቻ ሳይሆን የወርቅ ሜዳሊያ ማጥለቅ ነው፡፡ ሀገሬን ስወክል ሁሌም ኃላፊነት እንዳለብኝ ይሰማኛል» ስትል ትገልጻለች፡፡

ከዓለም አትሌቲክስ ጋር አጭር ቆይታ የነበራት የ27 ዓመቷ አትሌት ጉዳፍ «ኦሊምፒክ ትልቅ የውድድር መድረክ በመሆኑ የምንጊዜም ህልሜ ነው፡፡ በአትሌቲክስ የማስበውን ሁሉ ማሳካት ብችልም በኦሊምፒክ ወርቅ ማግኘት ግን ይቀረኛል፤ በመሆኑም ቀጣዩ ግቤ ይህ ነው» ስትልም አጽንኦት ትሰጣለች፡፡


## የጨረታ ማስታወቂያ

1. **በድጋሚ የወጣ የተለያዩ ያገለገሉ ተሽከርካሪዎች ጨረታ የጨረታ ቁጥር 003/2023/ 24**

የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ብዛታቸው 16 (አስራ ስድስት) የተለያዩ ያገለገሉ ተሽከርካሪዎችን ባሉበት ሁኔታ በጨረታ አወዳድሮ ለመሸጥ ይፈልጋል፡፡

1. ስለ አሻሻጡ የተዘጋጀውን ዝርዝር ሁኔታ የያዘውን ሰነድ ቄራ ፊት ለፊት በሚገኘው የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ሕንፃ 2ኛ ፎቅ ቢሮ ቁጥር 211 የማይመለስ ብር 300.00 (ሦስት መቶ ብር ብቻ) በመክፈል ከሰኔ 04 ቀን 2016 ዓ.ም ጀምሮ እስከ ሰኔ 18 ቀን 2016 ዓ.ም ከጠዋቱ 2፡00 ሰዓት እስከ ቀኑ 10፡00 ሰዓት ድረስ ባሉት የስራ ቀናት መግዛት ይችላሉ፡፡
2. ተጫራቾች ያገለገሉ ተሽከርካሪዎችን ከሰኔ 04 ቀን 2016 ዓ.ም ጀምሮ እስከ ሰኔ 19 ቀን 2016 ዓ.ም ድረስ ቃሊቲ ከመንገድ ትራንስፖርት የማሽከርከር ብቃት ማረጋገጫ እና ማሰልጠኛ ተቋም አለፍ ብሎ በሚገኘው በባንኩ የተሽከርካሪ ጋራዥ የቀድሞ አማልጋ ሜትድ ግቢ ውስጥ ከጠዋቱ ከ2፡00 ሰዓት እስከ ቀኑ 6፡00 ሰዓት፤ ከሰዓት በኋላ ከቀኑ 7፡00 ሰዓት እስከ ቀኑ 10፡00 ሰዓት ድረስ በመገኘት ማየት ይችላሉ፡፡
3. የተዘጋጀው የጨረታ ሰነድ ማስገቢያ ሳጥን ሰኔ 20 ቀን 2016 ዓ.ም ከጠዋቱ 3:00 ሰዓት ታዛቢዎች በተገኙበት ይታሸጋል፡፡
4. ተጫራቾች ለተሽከርካሪው የሚሰጡትን ዋጋ ከጨረታ ሰነዱ ላይ ባለው ክፍት ቦታ በመሙላት የጨረታ ማስከበሪያ እና ሌሎችም አስፈላጊ ሠነዶችን በፖስታ በማሸግ ቄራ ፊት ለፊት በሚገኘው የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ሕንፃ 2ኛ ፎቅ በተዘጋጀው የጨረታ ሰነድ ማስገቢያ ሳጥን ውስጥ ሰኔ 20 ቀን 2016 ዓ.ም ከጠዋቱ 3:00 ሰዓት እስከ 4፡00 ሰዓት ብቻ ያስገባሉ፡፡
5. ሰኔ 20 ቀን 2016 ዓ.ም ከጠዋቱ 4፡15 ሰዓት ተጫራቾች ወይም ህጋዊ ወኪሎቻቸው እንዲሁም ታዛቢዎች በተገኙበት ቄራ ፊት ለፊት በሚገኘው የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ የሠራተኞች የመዝናኛ ክበብ አዳራሽ በግልጽ ይከፈታል፡፡

**2. በድጋሚና አዲስ የወጣ የተለያዩ ያገለገሉ ንብረቶች ጨረታ የጨረታ ቁጥር 004/2023/24**

የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ያገለገሉ የተለያዩ ፈርኒቸር፣ የቢሮ እቃዎች፣ የአልሙኒየም ፍሬምና ያገለገሉ የብረታ ብረት ንብረቶች ባሉበት ሁኔታ በጨረታ አወዳድሮ ለመሸጥ ይፈልጋል፡፡

1. ስለ አሻሻጡ የተዘጋጀውን ዝርዝር ሁኔታ የያዘውን ሰነድ ቄራ ፊት ለፊት በሚገኘው የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ሕንፃ 2ኛ ፎቅ ቢሮ ቁጥር 211 የማይመለስ ብር 300.00 (ሦስት መቶ ብር ብቻ) በመክፈል ከሰኔ 04 ቀን 2016 ዓ.ም ጀምሮ እስከ ሰኔ 11 ቀን 2016 ዓ.ም ከጠዋቱ 2፡00 ሰዓት እስከ ቀኑ 10፡00 ሰዓት ድረስ ባሉት የስራ ቀናት መግዛት ይችላሉ፡፡
2. ተጫራቾች ያገለገሉ ንብረቶችን ከሰኔ 04 ቀን 2016 ዓ.ም ጀምሮ እስከ ሰኔ 12 ቀን 2016 ዓ.ም ድረስ የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ቃሊቲ ቅርንጫፍ ትይዩ ባለው አስፓልት ወደ ውስጥ ገባ ብሎ በሚገኘው የቀድሞ ብራሌ ጥጥ መዳመጫ ግቢ እና ልደታ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ፊት ለፊት ዛጉዌ ህንፃ ግራውንድ ውስጥ ከጠዋቱ ከ2፡00 ሰዓት እስከ ቀኑ 6፡00 ሰዓት፤ ከሰዓት በኋላ ከቀኑ 7፡00 ሰዓት እስከ ቀኑ 10፡00 ሰዓት ድረስ ባሉት የስራ ቀናት በመገኘት ማየት ይቻላል።
3. የተዘጋጀው የጨረታ ሰነድ ማስገቢያ ሳጥን ሰኔ 13 ቀን 2016 ዓ.ም ከጠዋቱ 3:00 ሰዓት ላይ ታዛቢዎች በተገኙበት ይታሸጋል፡፡
4. ተጫራቾች ለንብረቱ የሚሰጠውን ዋጋ ከጨረታ ሰነዱ ላይ ባለው ክፍት ቦታ በመሙላት የጨረታ ማስከበሪያ እና ሌሎችም አስፈላጊ ሰነዶችን በፖስታ በማሸግ ቄራ ፊት ለፊት በሚገኘው የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ሕንፃ 2ኛ ፎቅ በተዘጋጀው የጨረታ ሰነድ ማስገቢያ ሳጥን ውስጥ ሰኔ 13 ቀን 2016 ዓ.ም ከጠዋቱ 3:00 ሰዓት እስከ 4፡00 ሰዓት ብቻ ያስገባል፡፡
5. ሰኔ 13 ቀን 2016 ዓ.ም ከጠዋቱ 4፡15 ሰዓት ተጫራቾች ወይም ህጋዊ ወኪሎቻቸው እንዲሁም ታዛቢዎች በተገኙበት ቄራ ፊት ለፊት በሚገኘው የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ የሠራተኞች የመዝናኛ ክበብ አዳራሽ በግልጽ ይከፈታል፡፡

ተጫራቾች ለሚጫረቱበት የንብረት ዓይነቶች የጨረታ የመነሻ ዋጋውን 25% (ሃያ አምስት በመቶ) የጨረታ ማስከበሪያ (Bid Bond) በባንክ ክፍያ ማዘዣ (CPO) ለኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ያገለገሉ ንብረቶች አስወጋጅ (Commercial Bank of Ethiopia Disposal) በሚል ማቅረብ ይኖርባቸዋል፡፡

ለጨረታ ማስከበሪያ የተያዘው ሲፒኦ አሸናፊ ለሚሆነው በሚገዛው ንብረት ክፍያ ላይ የሚታሰብ ሲሆን አሸናፊ ላልሆኑት ለጨረታ ማስከበሪያ ያስያዙት ሲፒኦ ተመላሽ ይደረግላቸዋል፡፡

ባንኩ የተሻለ አማራጭ ካገኘ ጨረታውን በከፊልም ሆነ በሙሉ የመሠረዝ መብቱ የተጠበቀ ነው፡፡

## የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ




# ስጦሩ ውጤት - ጠንክሮ ማጥናት

**እየሩስ ተስፋዬ**

ልጆችዬ እንዴት ናችሁ? ሰላም ናችሁ? ሳምንታችሁ እንዴት አለፈ? ደስ በሚል ሁኔታ እንዳሳለፋችሁ እርግጠኛ ነኝ፡፡ ልጆችዬ ትምህርት ለሁሉም ነገር መሠረት እንደሆነ ትገነዘባላችሁ ብዬ ተስፋ አደርጋለሁ፡፡ ወላጆቻችሁ እና አሳዳጊዎቻችሁም፤ ወደ ፊት ትምህርታችሁን ጨርሳችሁ ውጤታማ ዜጋ እንድትሆኑ ወደ ትምህርት ቤት የሚልኳችሁም ይህንን በማሰብ ነው፡፡ ታዲያ እናንተስ ውጤታማ እና ጎበዝ ተማሪ ለመሆን ታነባላችሁ? በርትታችሁ እና ጠንክራችሁ ታጠናላችሁ? ያልገባችሁን ለመምህራን ትጠይቃላችሁ? መልሳችሁ «እንዴ በሚገባ!» የሚል እንደሚሆን ምንም ጥርጥር የለንም፡፡



ልጆችዬ የዓመቱ መደበኛ የትምህርት መርሀ ግብር ሊጠናቀቅ ጥቂት ቀናት ብቻ ናቸው አይደል የቀሩት? የሰኔ ወር ደግሞ የዓመቱ የመጨረሻ ፈተና እና ውጤት የሚገለጽበት ነው፡፡ እናንተም ዓመቱን በሙሉ ፕሮግራም በማውጣት ስታጠኑ፣ ያልገባችሁን ስትጠይቁ፣ መምህሮቻችሁን በንቃት ስትከታተሉ እንደነበር ተስፋ አደርጋለሁ፡፡ በተለይም የዓመቱ የትምህርት አጋማሽ ላይ ያገኛችሁት ውጤት በትምህርታችሁ የበለጠ እንድትጠነክሩም ሆነ ማሻሻል ያለባችሁን ነገር እንድታሻሽሉ በሚገባ ያግዛችኋል፡፡

ልጆችዬ የትምህርት ዓመቱን በጥሩ ውጤት ለማጠናቀቅ ያላችሁ ጥቂት ቀናት ብቻ ናቸው፡፡ እናንተም በርትታችሁ በጥናት እያሳለፋችሁ እንደሆነ ተስፋ አደርጋለሁ፡፡ እናም እናንተ እንዳታጠኑ የሚያዘናጓችሁን ነገር ማድረግ የለባችሁም። ለምሳሌ ቴሌቪዥን ማየት፣ ጌም መጫወት፣በጥናት ሰዓት መጫወት እና መረበሽ በፍጹም የለባችሁም፡፡ ልጆችዬ ማወቅ ያለባችሁ ነገር ምን መሰላችሁ? አሁን መደበኛው ትምህርት ሊዘጋ ጥቂት ቀናት ብቻ ስለቀሩ ጨዋታውም ይሁን ሌሎች ነገሮችን በእረፍት ጊዜያችሁ መከወን እንደምትችሉ እና አሁን ከሁሉም ነገር ቅድሚያ መስጠት ያለባችሁ ለትምህርታችሁ ብቻ መሆኑን ነው፡፡ እናም ልጆችዬ ጥናት የሚጀመረው ፈተና ሲደርስ ብቻ አይደለም፡፡

ልጆችዬ እስቲ ገምቱ? ዓመቱ መጨረሻ ላይ ማን ጥሩ ውጤት በማምጣት የሚያጠናቅቅ ይመስላችኋል? ይህንን መገመት ይከብዳል አይደል? መገመት አይከብድም፡፡ እንደውም በጣም ቀላል ነው፡፡ «እንዴት ?» ካላችሁም፤ ሁልጊዜ የሚያጠና፣ መምህራን ሲያስተምሩ በሚገባ የሚከታተል፣ በክፍል ውስጥ የማይረብሽ፣ በክፍል ውስጥ መምህራን ሲያስተምሩ በንቃት የሚሳተፍ ጥያቄዎችን የሚመልስ፣ ያልገባውን የሚጠይቅ፣የፈተና መመሪያዎችን በሚገባ አንብቦና ተረድቶ ትክክለኛውን የሚመልስ እና ሌሎችንም ተግባራዊ የሚያደርግ ተማሪ ዓመቱ መጨረሻ ላይ ጥሩ ውጤት ለማምጣት ምንም የሚከለክለው ነገር የለም፡፡ ስለዚህም ልጆች ይህንን የሚያደርግ ተማሪ ዓመቱ መጨረሻ ላይ ጥሩ ውጤት አስመዝግቦ በትምህርት ቤቱ እና በወላጆቹ እስከመሸለም ይደርሳል፡፡

መቼም ልጆችዬ ስለ ጥናት እና ንባብ ሲነሳ የወላጆች ድጋፍ እና ኃላፊነት አብሮ ይነሳል፡፡ ለምን መሰላችሁ ልጆች? እናንተ እንድታጠኑ፣ ክትትል እና ድጋፍ ማድረግ እንዲሁም አመቺ ሁኔታዎችን መፍጠር ከወላጆች የሚጠበቅ ተግባር በመሆኑ ነው፡፡ እነርሱ ይህንን ማድረጋቸው ጥቅሙ ለእናንተ ብቻ ሳይሆን ለወላጆችም ጭምር ነው፡፡ እንዴት? ካላችሁ፤ ምላሹም የትኛውም ወላጅ ልጁቹ ውጤታማ ሆኖ ማየት ስለሚፈልግ ነው፡፡ ልጆችዬ ታዲያ እናንተም ቤተሰቦቻችሁ በተለያየ ምክንያት ድጋፍ እያደረጉላችሁ ካልሆነ ድጋፉቸው እንደሚያስፈልጋችሁ በግልጽ መናገርም ይኖርባችኋል፡፡

ልጆችዬ ከዚህ ቀደም ፈተና ስትቀበሉ የመጀመሪያ ሥራችሁ መሆን አለበት ያልናችሁ ምን ነበር? «ራሳችሁን መመዘን፡፡» ብላችሁ መለሳችሁ? በጣም ጎበዞች፡፡ አሁንም ቢሆን የዓመቱን ማጠናቀቂያ ውጤታችሁን ከተቀበላችሁ በኋላ ምን ትምህርት ላይ ደካማ እና ጠንካራ እንደነበራችሁ፣ የአጠናን ስልታችሁ ምን ይመስል እንደነበር መፈተሽ ፣ በክፍል ውስጥ ያላችሁ ተሳትፎ እስከምን እንደነበር ፣ ለፈተና የምታደርጉት ዝግጅት እና ሌሎች ነገሮች በማጤን ጥሩ ውጤት ያመጣችሁ በዛው መቀጠል ይኖርባችኋል፡፡ ጥሩ ውጤት ላላመጣችሁ ተማሪዎች ደግሞ ውጤታችሁን እንድታሻሽሉ በሚገባ ያግዛችኋልና እነዚህን ተግባራዊ ማድረግ ይኖርባችኋል፡፡

ልጆችዬ በቀጣይ ሳምንታት የስድስተኛ ክፍል እና የስምንተኛ ክፍል ከተማ አቀፍ ፈተና እንደሚሰጥ ሰምታችኋል አይደል? ተፈታኝ የሆናችሁ በፈተና ወቅት መያዝ ያለባችሁን እና መያዝ የሌለባችሁን ነገር በየትምህርት ቤቶቻችሁ መመሪያ እንደተሰጣችሁ ተስፋ እናደርጋለን፡፡ የዘንድሮ ተፈታኝ የሆናችሁም ተማሪዎች ያለምንም ጭንቀት እና ፍርሀት ፈተናውን መውሰዳችሁ፤ ጥሩ ውጤት እንድታመጡ በሚገባ የሚያግዛችሁ መሆኑን በመረዳት በጥንቃቄ ፈተናችሁን መሥራት ይኖርባችኋል፡፡ በእኛ በኩል ከወዲሁ መልካም ፈተና እንዲሆንላችሁ ተመኝተናል፡፡ ልጆችዬ የትምህርት ዓመቱን ጥሩ ውጤት እንደምታመጡ ተስፋ እናደርጋለን፡፡ ለዛሬ በዚሁ አበቃን፡

